## የወልቃይት ጠገዴ መሬቱን እንጂ...!

ሳምሶን ኃይሌ

በገፅ 8



## ሕዝብን የቀሰቀሰው የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር

አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)



በገፅ 5





## እሳትን በጋቢ "ማዳፈን"

በገፅ 4



# የቀለም ቀንድ

ቅጽ 3 ቁጥር 24 ታህሳስ 26 ቀን 2008ዓ.ም ዋጋው ብር 10.00


# ተቃውሞውን ለመግታት ሚዲያውን መድፈቅ




2

## በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች ተቃውሞው እንደቀጠለ ነው ተባለ

• የኦፌኮ ዋና ጸሐፊ አቶ በቀለ ነጋ እስካሁን በቤታቸው እንደታገቱ ነው

መንግሥት በአብዛኛው የኦሮሚያ አካባቢዎች ተቀስቅሶ የነበረውን ተቃውሞ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሬዋለሁ ቢልም በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች አሁንም ተቃውሞው እንደቀጠለ መሆኑ እየተነገረ ነው:: በምዕራብ ሐረርጌ ዳሮ ለቡ ወረዳ መቻራ ከተማ ታኅሣሥ 21 ቀን በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተነሳው ተቃውሞ መከላከያ ሠራዊት ከገባ በኋላ ቢቀዘቅዝም ይህ ዜና እስከ ተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ መደበኛ ትምህርት ተቋርጦ እንደነበር ከቦታው የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ:: በዕለቱ ከፍተኛ ተኩስ የነበረ ሲሆን ቁጥራቸው ያልታወቁ ተማሪዎች ቆስለዋል፤ በሰው ሕይወት ላይ ግን የደረሰ ጥፋት የለም ተብሏል:: በዚሁ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ምጨታ አካባቢ አነስተኛ ተቃውሞ እንደነበር ተገልጿል:: በአርሲ ዩኒቨርሲቲ አሰላ ግቢና በሻሸመኔ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዘንድም ተቃውሞ እንደነበር ከቦታው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል::

በተያያዘ ዜና ወለጋ በደንቢ ዶሎ፣ በሆሮ ጉድሩና በቶንጋ የተማሪዎች ተቃውሞ መቀስቀሱን ከቦታው ያገኘናቸው መረጃዎች ያስረዳሉ:: በሆሮ ጉድሩ የኦሮሚያ ክልል ርእሰ መስተዳደር ልዩ አማካሪ ወንድም በመንግሥት

በገፅ 3


ዲላ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተወረወረ ቦምብ ተማሪዎች ተገደሉ

በሕዳሴው ግድብ ላይ የተደረገው ስምምነት እያነጋገረ ነው

አሜሪካ በኢትዮጵያ ያላትን የሰው አልባ የጦር አውሮፕላን ጣቢያ ዘጋች

በገፅ 3

## ርእሰ አንቀፅ

# ተቃውሞውን ለመግታት ሚዲያውን መድፈቅ

ኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት ነገሮችን የሚያያቸው በሁለት ጽንፎች ክፍሎ ነው፡፡ በአንድ በኩል ኢሕአዴግ እና የኢሕአዴግ ርዕዮት ደጋፊዎች አሉ፡፡ በሌላው ማዶ የኢሕአዴግን አካሄድ የሚቃወሙ ወይም ይቃወማሉ የሚባሉት ኃይሎች ይገኛሉ፡፡ ኢሕአዴግና የኢሕአዴግ ደጋፊዎች ልማታዊ ዴሞክራሲያውያን፤ የአገሪቱን እድገት፣ ሰላምና መረጋጋት የሚፈልጉ፤ ለዚህ ዓላማ ሌት ተቀን የሚተጉ አካላት ሲሆኑ፤ አገዛዙን የሚቃዎሙት ወይም የማይደግፉት ኢትዮጵያውያን በአንጻሩ የሁለተኛው ማለትም የጸረ ዴሞክራሲ፣ ጸረ ሰላምና ጸረ ልማት ካምፕ ምድብተኞች ናቸው፡፡ በሜዳው ላይ ከሁለቱ ተጻራሪ ኃይሎች ውጪ የሚታይ የለም፡፡ ወይ ወዳጅ ነው፤ ወዳጅ ካልሆነ ደግሞ ከጠላት ውጪ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ አመካይ ቦታ ብሎ ነገር የለም፡፡

ላለፉት 25 ዓመታት የተመራነው በዚህ መሠረታዊ የጫካ የሽምቅ ተዋጊ ሥነ ልቦና እና የአገዛዝ ዘይቤ ነው፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በወዳጅና ጠላት ምድብ ተከፍለው፤ ወዳጅ የተባለው ሲደገፍና ሲሸለም ጠላት ናቸው የሚባሉት በአንጻሩ (ጠላት ናቸውና) ሲሳደዱ ከርመዋል፡፡ በአገራችን የነገሰው የለየለት የመሬት ዘረፋና ቅሚያ፣ ታይቶ የማይታወቅና የሚያስፈራ ሌብነት፣ መፍትሔ ያጣው የመልካም አስተዳደር ችግር፣ ዘረኝነትና ጥላቻው ወዘተ. ሁሉ የሚቀረፈው ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ሲገነባ መሆኑን ስንሰማ ከርመናል፡፡ ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ እንዳይገነባ እንቅፋት ከሚፈጥሩት አካላት መካከል አንዱ የግሉ መገናኛ ብዙሃን ነው ሲባልም ሰምተናል፡፡ ስለሆነም በኢሕአዴግ እምነት የግሉ መገናኛ ብዙሃን ወይ የኢሕአዴግን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተቀብሎ የተጀመረውን የሕዳሴ ጉዞ ያስቀጥላል ወይ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒው ተሰልፎ የጸረ ሰላምና ጸረ ልማት ኃይሎች ልሳን ሆኖ በተያዘው የግስጋሴ ጎዳና ላይ ደንቀራ ይሆናል፡፡ የሕዳሴው ጉዞ የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ደግሞ በጎዳናው ላይ ደንቀራ የሚሆኑትን ኃይሎች መታገስ አይቻልም፡፡

እንግዲህ፤ በዚህ መርህ ነው ባለፉት ዓመታት አያሌ ጋዜጦችና መጽሔቶች የተዘጉት፤ በዚህ መርህ ምክንያት ነው በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ለእስር፣ ለስደት ብሎም ለሞት የተዳረጉት፤ በዚህ መርህ መሠረት ነው የኢትዮጵያ የግል ሚዲያ እድገት የኋሊት የሆነው፡፡ ሕወሓት አሁንም በሽምቅ ተዋጊ ሥነ ልቦና የሚመራ ድርጅት ነውና የዜጎችን ሰላማዊ የመብት ጥያቄ ሁሉ በጥይት መመለስ ልማዱ ነው፡፡ በጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ ሥርዓት መፍጠር ተችሏል በተባለ በማግስቱ አነስተኛ ሰልፍ ሲደረግ መደንገጥና መርበትበት ግብር ነው፡፡ ሀብቱም ጠብመንጃውም በእጃቸው ሆኖ ሳለ ይፈራሉ፡፡ ይባንናሉ፡፡ አገዛዙንና የአገዛዙን ያልተገባ አካሄድ የሚተቹት ጋዜጦች ከቁጥር የማይገቡ፤ ሥርጭታቸውም ከአንድ ቀጠና የማያልፍ መሆኑ እውነት ቢሆንም ሁልጊዜም የአገዛዙ ሰለባዎች ከመሆን አያመልጡም፡፡ ሁልጊዜም ማስፈራራትና ዛቻ አለ፤ ሁልጊዜም የ‹‹ለምን አትሄዱም?›› ‹‹ምክር›› አለ፡፡

በዓመቱ መጀመሪያ አካባቢ ፕ/ት ባራክ ኦባማ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ከፕሬዘዳንቱ ጋር ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ፤ ኢትዮጵያ ጋዜጠኞችን በማሰርና በማሳደድ በዓለም ሁለተኛ ደረጃ መያዟን ጠቅሳ የአሶሼትድ ፕሬስ ጋዜጠኛ ላቀረበችላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፤ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ችግር የጋዜጠኝነት ዕውቀትና ክህሎት ችግር መሆኑን ገልጸው ጋዜጠኞቻችን የሚያሰለጥንልንና የሚደግፍልን እንፈልጋለን ማለታቸውን እናስታውሳለን፡፡ ጋዜጠኞቻችን የዕውቀትና የክህሎት ችግር ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ ችግሩ የሚፈታውና የአገራችን መገናኛ ብዙሃን ሊያድግ የሚችለው ግን በተግባር እንደሚታየው ጋዜጠኞችን በማስፈራራት፣ በማሳደድና በማሰር አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም፡፡

በቅርቡ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች የተቀሰቀሱትን ተቃውሞዎች ተከትሎ ብዙዎች መሞታቸው፣ መቁሰላቸውና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን መታሰራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ አገዛዙ ችግሩን በሰከነ ሁኔታ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ የተለመደውን የጫካ አካሄዱን መርጦ ዋጋ የሚያስከፍል እርምጃ ወስዷል፡፡ ስለሁኔታው የሚዘግቡትን ጋዜጦች በማስፈራራት፣ በማሸማቀቅና በመድፈቅ ስለተቃውሞው እንዳይጽፉም ከፍተኛ ጫና እየተደረገ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህም ሌላ የጥፋት አዙሪት ካልሆነ በስተቀር ችግሩን ከሥረ መሠረቱ የሚፈታው አይሆንም፡፡



## ትዝብት

በውቀቱ ስዩም

# የሕዳሴው ገደል እምን ላይ ደረሰ?

አውሮፕላን መጣ እየገሰገሰ በዘፈን አንደኛ ሙሉቀን መለሰ (እስከመቸ ድረስ ጥላሁን ገሰሰ) የሕዳሴው ገደል እምን ላይ ደረሰ?

የሕዳሴውን ግድብ ወደ ‹‹ሕዳሴው ገደል›› ያሸጋገረውን ስምምነት የፈረመው ሰውየ ‹‹እጁን ለቁርጥማት፤ ደረቱን ለውጋት›› እንዲዳርገው በመመረቅ ወደ ሰላምታየ እገባለሁ፡፡ እንዴት ናችሁ፤ ያልታደላችሁ? እኔ በሕይወቴ በተለያየ ጊዜ ተስፋ ቆርጫለሁ፡፡ እንደ ዘንድሮ ተስፋን፤ ከሻኛውና ከፍሪምባው አፈራርቄ የቆረጥሁበት ጊዜ አልገጠመኝም፡፡

መንግሥትም ሃያ ዓመት ሙሉ አጥሮ፤ ሃያ ዓመት ሙሉ ቆፍሮ የተሳካለት አይመስልም፡፡ ‹‹በየቦታው እንምሳለን፡፡ ለመጭው ትውልድ ነዳጅ ሳይሆን ጉዱጓድ እናወርሳለን›› የሚል ነው የሚመስለው፡፡ የዛሬ ዐሥራ አምስት ዓመት ገደማ ውኃ ማቆር የተባለ ፕሮጀክት ነድፎ ነበር፡፡ እናም ኅብረተሰቡ በየጓሮው ሮቶ ሮቶ የሚያክል ጉድጓድ እየቆፈረ የዝናብ ውኃ እንዲያቁር ትእዛዝ ተላልፎለት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ውጤቱ ምንድን ነበር? የየሰፈሩ ሰካራም በየጉድጓዱ እየገባ አለቀ፡፡ ይሁን እንጂ መንግሥት፤ ስንት ሰካራም አጥንቱን የከሰከሰበትን፤ ደሙን ያፈሰሰበትን ፕሮጀክት ድንገት ሰረዘ፡፡ በጊዜው የተወሰኑ ሰዎች ለዶማና ላካፋ መግዣ በሚል ወፍራም በጀት አስለቅቀው ከድህነት ተላቀቁ፡፡ አገሪቱ ግን የግዜር ገበጣ መጫወቻ መስላ ቀጠለች፡፡ የውኃ ማቆር ፕሮጀክቱ ቢቀጥል ኖሮ ዛሬ የሕዳሴውን ገደል ለመሙላት ግብጽን አንለማመጥም ነበር፡፡

መንግሥት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የማይፈጽመውን እያቀደ፤ አዲስ አበቤም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በችግሩ እየቀለደ፤ ሃያ አምስት ዓመት ተገባደደ፡፡ በውቄም ስኮላርሺፕ በሚል ሰበብ፤ ማንነታቸው ያልታወቀ ፌዴራል ፖሊሶች የሚወረውሩት ቦምብ ወደማይደርስበት ቦታ ተሰደደ፡፡ በግንቦት ወር ወደ አገሩ ሲመለስ ችግር ይገጠመው ይሆን? ወይስ በእጃችን እንዳይጠፋብን ብለው ይተውት ይሆን? ቀጣዩን ክፍል በመጭው ግንቦት ይጠብቁ፡፡ ግን መንግሥትን መተቸት ሕገ መንግሥታዊ መብቴ መሆኑ ይሰመርበት፡፡ በርግጥ ሕገ መንግሥቱ እንደ አዲስ አበባ ምግብ ቤቶች ሜኑ ነው፡፡ የተጻፈውን በተግባር ስትፈልገው አታገኘውም፡፡

በነገራችን ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ የሆነ መጽሔት ላይ ‹‹ያመቱ ሰው›› ተብለው መሸለማቸውን ሰምቼ ተደስቻለሁ፤ ሲያንሳቸው ነው፡፡ ይኼን ያክል እየተተረበ፤ ይኼን ያክል እየተሰደበ፤ ይኼን ያክል ከታችም ከላይም ንቀት እየተከናነበ ቆሞ መሄድ የቻለ ሰው፤ ሽልማት አነሰው? እኔም እንሆ፤ ሰሜን አሜሪካ ጫፍ አርፌ በጀርባየ የካናዳን የጉም ግድግዳ ተደግፌ ከጢሜ ላይ የኮካ ኮላ ጤዛ፤ ከኪቦርዴ ላይ በረዶየን አራግፌ፤ ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ተባብረህ ተነስተህ ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ አምባገነኑን ሥርዓት ገርስስ›› እያልሁ ነጋሪት ስደልቅ፤ አዲስ አበቤም ‹‹ወይ ኦን ላይን ላይ ያለ ሰው!›› እያለ በኔ ላይ ሲስቅ፤ ጀምበር ‹‹ሎግ አውት›› አድርጋ ጥልቅ፡፡

ባለፈው 53 የፖለቲካና የሃይማኖት ድርጅቶች መግለጫ አውጡ ሲባል ስቁ ልሞት፡፡ ያሁላ ፓርቲ ቢሮ አለው? ወይስ ህልሙን ባሮጌ ሳምሶናዊት ሸክፎ የሚዞረው ሁሉ ተቆጥሮ ነው? ግሩም ነው መቸም፡፡ ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት አንደኛ ሆና ወተት ይርባታል፤ አምሳ ሦስት የፖለቲካ ፓርቲ ኖሯት ፖለቲካው ይቸግራታል፤ እንዲያው ምን ይሻላታል?

ድሮ የኔ ቢጤ ባይተዋር ሰው ሲጨንቀው ሰላም ፍለጋ ወደቤተክርስቲያን ነበር የሚሄደው፡፡ አሁን በየቤተክርስቲያኑ ድብድብ ነው፡፡ እዚያ ዲሲ ቤተክርስቲያን ልትስሚ ከሄድሽ በነጠላሽ ላይ የጥይት መከላከያ መደረብ አለብሽ፡፡ እነ አባባ ቆባቸው በሮ እስኪሄድ ሲከታከቱ ታዝበሽ፤ ከተወረወረ መቋሚያ በመትረፍሽ አንድየን አመስግነሽ፤ ወደ ቤትሽ ትመለሻለሽ፡፡ ባገር ቤት፤ ቤተክርስትያን ውስጥ አንድ ቄስ በዲያቆናት ሲታጀብ፤ የዲሲ ሐበሻ ቄሶች ግን በፖሊስ ታጅበው ነው የሚቀድሱ፡፡ እንዲያውም የፈረንጅ ፖሊሶች ለግልግል እየተጠሩ ቤተክርስቲያኑን ከማዘውተራቸው የተነሳ ቅዳሴውን ለምደው ተሰጥኦ ሁሉ መቀበል ጀምረዋል፡፡

በነገራችን ላይ ላገራችን የገጠር ቄስ ክብር አለኝ፡፡ ዳዋ ጥሶ፤ ጤዛ ልሶ፤ ድንጋይ ተንተርሶ፤ ግርማ ሌሊትን፤ ጸብአ አጋንንትን ታግሶ፤ የሚኖር ነው፡፡ የዲሲ ቄስ በበኩሉ ሙዳየ ምጽዋት አፍሶ፤ አይስክሬሙን ልሶ፤ የንስሐ ልጁን ጡት ተንተርሶ፤ በቴስታ ተከሳክሶ ይኖራል የሚል ሐሜት አለ፡፡

የዛሬውን የሕትመት ዳሰሳየን የምቋጨው በመሬት ‹‹ትንታኔ›› ነው፡፡ ያዲስ አበባ የመሬት ችግር የመነጨው ከዘጠና ሰባት በኋላ ይመስለኛል፡፡ ጌቶች በነዋሪው ተስፋ ስለቆረጡ፤ በሥልጣናቸውም ዋስትና ስላጡ፤ ‹‹ኪስህ ነው የቅርብ ወዳጅህ›› የሚለውን ዘፈን ማንጎራጎር መረጡ፡፡ ይህንን ዝንባሌ እኔና ቢጤዎቼ ‹‹የቀኝ አዝማች ሰውነቴ ሲንድረም›› ብለን እንጠራዋለን፡፡

ቀኛማች ሰውነቴ ከደብረማርቆስ ባላባቶች አንዱ ነበሩ፡፡ እና በስድሳ ስድስቱ አብዮት ዋዜማ የጭሰኞቻቸውን መሬት ጆሮ ጆሮውን ብለው ካቲካላ ጠጡበት፡፡ ባላባት ጓደኞቻቸው ለምን እንዲያ እንደሚያረጉ ሲጠይቋቸው ‹‹መሬት ሳትበላኝ ልብላት ብየ ነው›› አሉ ይባላል፡፡

በዲኦንሔር ፐብሊሺንግ ሚዲያ እና ኮምኒኬሽን ኃላ.የተ.የግ. ማኅበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ ሳምንታዊ ጋዜጣ

ሥራ አስኪያጅ
አበበ ውቤ

ዋና አዘጋጅ
ሙሉቀን ተስፋው
0910159783
mulukentesfaw@gmail.com
የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 09/297


ሪፖርተር
ትሑት ጥላሁን

አምደኞች
መስከረም አበራ
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)
አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)
ሩት አማኑኤል
መብራቱ በላቸው
በሪሁን አዳነ
ታዲዮስ ታንቱ
ነብዩ ሲራክ (ከሳውዲ አረቢያ)

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08
ቤ/ቁጥር 471
ስልክ፡ 0910159783
0919396240

ግራፊክስ ዲዛይን
ስልክ፤ 0911 18 09 33


አታሚ
‹‹ሶፍ ሚክ ማታሚያ ቤት
ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 04
የቤት ቁጥር 64




# ሳውዲ ዐረቢያና ኢራን ተፋጠዋል

ነብዩ ሲራክ

ከሳውዲ ዐረቢያ የአገር ውስጥ ሚኒስቴር የተሰጠውን መግለጫ ይዞ የወጣው የሳውዲ ፕሬስ ኤጀንሲ እንዳስታወቀው እ.ኤ.አ. ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም. በ12 የሳውዲ የተለያዩ ከተሞች ንጹሐንን ዒላማው ባደረገ የአልቃኢዳ የሽብር ጥቃት ላይ መሰማራታቸው የተረጋገጠ 47 ሰዎች የተላለፈባቸው የሞት ቅጣት መተግበሩን አስታውቋል:: አንገታቸው ከተቀላው 47 ሰዎች መካከል አብዛኞቹ 45ቱ ከሳውዲ ዐረቢያ ሲሆኑ 1 ግብጻዊና 1 ቻዳዊ ዜጎች እንደሚገኙባቸውም የሳውዲ ፕሬስ ኤጀንሲ በስምና በፎቶ ባሰራጭው መረጃ ይፋ አድርጓል:: በሰይፍ ከተቀሉት 45 ሳውዲዎች መካከል በምሥራቅ ሳውዲ ዐረቢያ ክፍል በሚገኙ የሽዓ እስልምና ተከታዮችና በአጎራባች አገራት በኢራንና በባህሬን ሽአዎች ዘንድ ታዋቂ የነበሩት የሃይማኖት መሪ ኒማር አል ኒማር አንዱ ናቸው:: በተመሳሳይ ሁኔታ በአሸባሪነት የተመዘገበው በሸህ ኦሳማ ቢ ላዲን የተመሠረተው የአልቃኢዳ ከፍተኛ አመራር ፋሪስ አል





ሹዌል እንደሚገኙበትም ታውቋል::

የሳውዲ ዐረቢያን እርምጃ ተከትሎ የሽአው የሃይማኖት መሪ የሸህ ኒማር ኒማርን ጉዳይ አይጥና ድመት የሆኑትን ሳውዲ ዐረቢያና ኢራን ማጋጨት የጀመረ ሲሆን በኢራንና በጎረቤት አገር ባህሬን የሚገኙ የሽአ እስልምና እምነት ተከታዮች የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸው ተዘግቧል:: የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆሴን ጃብር አንሳሪ የሳውዲ ዐረቢያን እርምጃ አጥብቀው ሲኮንኑ የኢራን ፖርላማ አፈ ጉባኤ አሊ ላርጃኒና አያቶላህ አሕመድ ካተሚ የተባሉት የኢራን ሃይማኖት አባት የሸህ ኒማር ግድያን አጥብቀው አውግዘውታል:: በኢራን ዋና ከተማ በቴህራንም የሳውዲ ዐረቢያን መንግሥት እርምጃ በመቃውም ሰላማዊ ሰልፍ የተደረገ ሲሆን በሰሜን ምሥራቅ ኢራን በመሽሃድ (Mashhad) የተካሄደው ተቃውሞ የሳውዲ ቆንስል እስከማቃጠል የደረሰም ነበር::

ዘግየት ብሎ በደረሰን ዜና የኢራን የውጪ ጉዳይ ሚ/ር እንዳስታወቀው የኢራን ዲፕሎማቶች እና ዲፕሎማቲክ መስሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ሳኡዲን በ48 ሰዓት ለቀው እንዲወጡ አስታውቋል::

በሳውዲ ቆንስል መቃጠል የሳውዲ ዐረቢያ መንግሥት የኢራን መንግሥትን ተጠያቂ ሲያደርግ ኢራን በበኩሏ ‹‹ለተፈጸመው በድል ሳውዲ ዐረቢያ የእጇን ታገኛለች›› ስትል ያሰራጨችው መረጃ ሳውዲዎችን አስቆጥቷል:: የሳውዲ ዐረቢያ ቆንስላን በማቃጠል የተወሰደው እርምጃ ኢራን ከሳውዲ ዐረቢያ አልፎ በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ጣልቃ ለማስገባቷ ግልጽ ማረጋገጫ ነው በማለት የሳውዲ ዐረቢያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ አውጥቷል:: የውጭ ጉዳዩ የኢራንን አምባሳደር አስጠርተው የኢራን መንግሥት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት አሳውቀዋቸዋል:: የሳውዲ ዐረቢያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በማከልም የኢራን መንግሥት በአገሪቱ ዋና ከተማ በቴህራን የሚገኘውን ኢምባሲ ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፤ በሰሜን ምሥራቅ የኢራን ክፍል በመሽሃድ የሳውዲ ዐረቢያ ቆንስል ቃጠሎም ተጠያቂው የኢራን መንግሥት ነው በማለት አስታውቋል::

በሳውዲ ዐረቢያ መንግሥት ‹‹የሽብርተኛ›› በሚል ከቀናት በፊት አንገታቸው ከቀላቸው መካከል አንዱ የሆኑት የሽአው የሃይማኖት አባት የ56 ዓመቱ ሽህ ኒማር በምሥራቅ ከጢፍ አካባቢ እ.አ.አ. በ2011 ዓ.ም. የተነሳውን አመጽ ከጀርባ በመሆን አቀናጅተዋል የሚባሉት እኚሁ ግለሰብ አዋሚያ በተባለች መንደር በሳውዲ ዐረቢያ ጸጥታ አስከባሪዎች ቆስለው መያዛቸው ይጠቀሳል::

## ዲላ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተወረወረ ቦምብ ተማሪዎች ተገደሉ

ዲላ ዩኒቨርሲቲ ታኅሣሥ 21 ቀን 2008 ዓ.ም. ምሽት ባልታወቀ ግለሰብ በተወረወረ ቦምብ የሁለት ተማሪዎች ሕይወት ማለፉ ተጠቆመ:: ምሽት ሦስት ሰዓት አካባቢ ሰብሰብ ብለው ቤተ መጻሕፍት አካባቢ በነበሩ ልጆች ላይ የተጣለው ቦምብ የሦስት ተማሪዎችን ሕይወት ሲቀጥፍ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ተማሪዎችን አቁስሏል:: ሮይተርስ ተባለው የዜና ወኪል ከአዲስ አበባ 350 ኪሎ ሜትር ርቀት በሚገኘው ዲላ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተወረወረ ቦምብ ሁለት ተማሪዎች መሞታቸውና ሌሎች ስድስት ተማሪዎች መቁሰላቸውን ዘግቧል:: ከቆሰሉት ስድስት ተማሪዎች መካከል አራቱ በአደገኛ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የገለጸው የዜና ወኪሉ ባለፉት ሦስት ሳምንታት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ በአገሪቱ ያልታሰበ የቦምብ ፍንዳታ መከሰቱን አስታውሷል::

በተያያዘም በዚኸው ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ ሌሎች ሁለት ተማሪዎች ምንነቱ ባልታወቀ ምክንያት ተገድለው መገኘታቸው የተገለጸ ሲሆን፤ ተማሪዎቹ በምን ምክንያትና እንዴት እንደተገሉ ግን የተባለ ነገር የለም:: ሕይታቸው ካለፈው አራት ተማሪዎች ውስጥ ሦስቱ የአንድ አካባቢ ተወላጆች መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል::

## "ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረትና የአገርን ሉዓላዊነት መጠበቅ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ነው"

ሰማያዊ ፓርቲ

ሰማያዊ ፓርቲ ታኅሣሥ 20 ቀን 2008 ዓ.ም. ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ መንግሥት የመመሥረትና የአገርን ሉዓላዊነት መጠብቅ እንዳለባቸው አሳስቧል:: ፓርቲው በመግለጫው አገራችን ከምንጊዜውም በላይ በከፋ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅል ውስጥ ትገኛለች፤ በአገራችን ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል የማስቆም ብሎም ሕዝባዊ መንግሥት የመመሥረት፣ የአገር ብሔራዊ ክብርን የማስጠበቅ ኃላፊነት የጥቂት ቡድኖችና ግለሰቦች ድርሻ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያውያን ኃላፊነት ነው የሚለው የፓርቲው መግለጫ፤ ፋና ወጊና የነቁ ዜጎች የእሳት እራት እየሆኑ አርአያዎቻችን እያስበላን ዝም ማለታችን አገዛዙ ዕድሜውን ለማራዘም ተጠቅሞበታል፤ ሁሉም ዜጎች አርአያቸው የሆኑትን የቁርጥ ቀን ልጆች የቁርጥ ቀን ልጆች የመስዋዕትነት ጥሪ በመቀበል ቆርጠው በመነሳት የድርሻቸውን እንዲወጡ እናሳስባለን ሲል ጥሪ አስተላልፏል::

የአገር ድንበርንና ሉዓላዊነትን የሚጠብቁ ዜጎች መንግሥት ‹‹ሽፍቶች›› በማለት መጥራቱ ታሪካዊ የክህደት ምስክርነት መስጠት ነው ሲል የሚያትተው መግለጫው ድርጅቱ የመንግሥትን አካሄድ በጽኑ እንደሚቃወም ገልጿል::

# በሕዳሴው ግድብ ላይ የተደረገው ስምምነት እያነጋገረ ነው

ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳን አደረጉት የተባለው ስምምነት ብዙዎችን እያነጋገረ ነው:: በሦስቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ እና የውኃ ሀብት ሚኒስትሮች አማካይነት ሲካሄድ የቆየው ድርድር ተጠናቆ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ስምምነት መደረሱ ተዘግቧል:: የኢትዮጵያ መንግሥትና የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ስለስምምነቱ መልካምነት ሲገልጹ የቆዩ ቢሆንም፤ ኢትዮጵያ ያለ ግብጽና ሱዳን ስምምነት የሕዳሴውን ግድብ ውኃ መሙላት እንደማትችል ተስማምታለች ሲሉ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሰፊው አተትዋል::

ባሳለፍነው ሳምንት በተደረገው ስምምነት ሦስቱም አገራት መደሰታቸውን የየአገራቱ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ሲገልጹ መቆየታቸውም አይዘነጋም:: የግብጹ መሪ ፕ/ት አልሲሲ የአገራቸውን ሕዝብ በግድቡ ዙሪያ ስጋት እንዳይገባቸው መግለጻቸው የተዘገበ ሲሆን አልሞኒተር የተባለው ግብጽ የተባለ ድረ ገጽ ‹‹ኢትዮጵያ ሦስቱ አገሮች ስምምነት ላይ ሳይደርሱ አንዳችም ውኃ ወደ ግድቡ ላለመሙላት ተስማምታለች›› ሲል አስነብቧል:: የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ስምምነቱን አስመልክቶ በአንዳንድ በመገናኛ ብዙሃን የሚዘገበው ከእውነት የራቀ መሆኑን ገልጿል::

አሶሼትድ ፕሬስ እንደዘገበው በሦስቱ አገሮች ጥናቱን እንዲያከናውኑ የተመረጡት ‹‹ቢ.አር.ኤል›› እና ‹‹አርቴሊያ›› የተባሉ የፈረንሳይ ኩባንያዎች ናቸው:: አዲስ ስምምነት ያስፈለገበት ምክንያት ቀደም ሲል ከቢ.አር.ኤል ጋር አብሮ እንዲያጠና የተመረጠው የኔዘርላንዱ ዴልታሪስ የተባለው አማካሪ ራሱን በማግለሉ ነው የተገለጸ ቢሆንም ድርጅቱ በምን ምክንያት ከጥናቱ እንዳፈገፈገ የተባለ ነገር የለም::

## በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች . . .

ታጣቂዎች መገደሉም ታውቋል:: ሟቹ ግለሰብ በትምህርት ቤት ተማሪዎችና በመንግሥት ታጣቂዎች መካከል የተነሳውን ግጭት ለመዳኘት መሐል በገባበት ጊዜ ተመቶ እንደወደቀ ነው የተገለጸው:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ በየቦታው የሚፈነዱ ቦምቦች ለደህንነተ አስቸጋሪ መሆናቸው እየተነገረ ነው:: ከተቃውሞው ጋር በተያያዘ የሞቱ ሰዎች ብዛት ከ100 እንደሚበልጥ የተገለጸ ሲሆን፤ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ አመራሮች በበኩላቸው የታሰሩ ሰዎችም ቁጥር ጨምሯል ብለዋል::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች መድረክ ሊቀመንበር ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ እንደገለጹት የኦፌኮ ዋና ጸሐፊ አቶ በቀለ ነጋ በቁም እስር ናቸው:: አቶ በቀለ ከተወሰኑ ቀናት ወዲህ ሲቪል በለበሱ ደህንነቶች ቁጥጥር ሥር የዋሉ ሲሆን ‹‹አንተን ወስደን የምናስርበት ቦታም የለንም፤ ብትወጣም ልንገልህ እንችላለን›› መባላቸውን እና ስልካቸውን ተቀምተው በቤቱ ውስጥ ለመዋል መገደዳቸውን ለማወቅ ተችሏል::

## ወደ ደቡብ አፍሪካ በመጓዝ ላይ የነበሩ 137 ኢትዮጵያውያን ዛምቢያ ውስጥ መታሰራቸው ተገለጸ

በስደተኛነት ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ ሲጓዙ ዛምቢያ ድምበር ውስጥ የተያዙት 137 ኢትዮጵያውያን ዜጎች በዛምቢያ ፖሊሶች ቁጥጥር ሥር ውለው መታሰራቸውን የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እየዘገቡ ነው:: ቀደም ባሉት ጊዜያት ከደርዘን በላይ የሚሆኑ የአገራችን ዜጎች ተይዘው የ15 ዓመት እስር ተፈርዶባቸው ያሉም እንዳሉ ነው የተጣሰው::

የታሰሩት 137 ኢትዮጵያውያኑ ከፍተኛ ቁጥጥርና ጥበቃ በሚደረግበት የ‹‹ካምቦይ›› እስር ቤት እንደሚገኙ የተዘገበ ሲሆን ዛምቢያ ውስጥ የሚገኝ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ባለመኖሩ የታሰሩ ዜጎችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንደሌለ እና ከዚህ ቀደም የተያዙት ኢትዮጵያውያንም ከፍተኛ በደልና ስቃይ ሲደርስባቸው ቢቆይም የደረሰላቸው መንግሥታዊ ተቋም እንዳልነበረ ተመልክቷል:: ፈጣን እድገት እያስመሰገበች ነው የምትባለው ኢትዮጵያ ዜጎቿ በተገኘው መንገድ ሁሉ አገራቸውን ጥለውም የሚሰደዱባት አገር መሆኗ ብዙዎችን የሚያነጋገር ጉዳይ ሆኗል::

## አሜሪካ በኢትዮጵያ ያላትን የሰው አልባ የጦር አውሮፕላን ጣቢያ ዘጋች

የአሜሪካ አየር ኃይል አልሸባብን ለመዋጋት በሚል በአርባ ምንጭ ከተማ አደራጅቶት የነበረውን የሰው አልባ የጦር ጀት (ድሮን) መዝጋቱን ገለጸ:: የአሜሪካ መንግሥት አልሸባብን ለመዋጋት በሚል እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2009 ጀምሮ በአርባ ምንጭ በብዙ ሚሊዮን ዶላር አቋቁሞ ከአርባ ምንጭ ሶማሊያ እየተመላለሰ ጥቃት ሲያደርስ እንደነበር የተዘገበ ሲሆን፤ ይኸው ማዕከል ሙሉ በሙሉ መዘጋቱ ተጠቁሟል:: በአርባ ምንጭ የነበረው የአሜሪካ ‹‹ድሮን ቤዝ›› ሩብ ሔክታር መሬት ላይ ያረፈ ጠንካራ አጥር፣ ከፍተኛ ጥበቃና በደህንነት ካሜራዎች የሚጠበቅ ማዕከል እንደነበር ይታወቃል::

ማዕከሉ የተቋቋመው በቀጠናው ሽብርተኝነትን ለመዋጋት መሆኑ ሲታወቅ፤ የተቋሙ የተዘጋው የሽብርተኝነት ስጋቱ በመቀነሱ ይሁን ወይስ የአካባቢው አገሮች የአሜሪካን ሚና በመረከባቸው የሚታወቅ ነገር የለም::



## ወቅታዊ

መስከረም አበራ

# እሳትን በጋቢ "ማዳፈን"

የአገራችን ሰሞንኛ ፖለቲካዊ ትኩሳት ንጹሐንን ለሞት እና መንግሥትን ለከፍተኛ ድንግርግሮሽ የዳረገ እንደሆነ የሚታይ ነው። የፖለቲካው ግመት በዋናነት ከሁለቱ ሰፋፊ ክልሎች የሚነሳ ግን ደግሞ በክፉ ውጤቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዳር እስከዳር እያሳዘነ እና እያሳሰበ ያለ ሁነት ነው። በንጹሐን ሞትና በወጣቶች ጅምላ እስር የታጀበው ጥፋት የማያስከፋው ኢትዮጵያዊ የለም። የጥፋቱ መጠንና ፖለቲካዊ ተጽዕኖም መንግሥት እንደሚያለባብሰው ቀላል አይደለም።

መንግሥት በአዲስ አበባ እና በአጎራባች ወረዳዎች መካከል የተቀናጀ ልማት ያመጣል እያለ በልማት ማማነቱ የሚዘምርለት መርሐ ግብር ሕዝብን አስከፍቶ ለአደባባይ እምቢተኝነት ያበቃ እንደሆነ የሚታወቅ ነው። ሕዝቡ መርሐ ግብሩን ከልማቱ ይልቅ ጥፋቱ ይበዛል ብሎ ነገሩ እንዲቀር የቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው። በተመሳሳይ በአማራ ክልል በተለይ በጎንደር አካባቢ ከኢትዮ-ሱዳን ድንበር ማካለል እና ከቅማንት የማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ እየተጋጋመ ላለው ፖለቲካዊ ጥያቄ ሕዝብ ጥቅሙን የሚያስከብርለት መፍትሔ ከመንግሥት ይፈልጋል። ይህ ይሆን ዘንድ ሕዝቡ ከአንድ ወር ዘለግ ላለ ጊዜ ጥያቄውን በማሰማቱ ቀጥሏል። ነገር ግን ከአፈሙዝ ጋር በአንድ እርምጃ ርቀት እየተያየም ሞትን ወደ አለመፍራት ምሬት የደረሰው የሕዝብ አቋም በመንግሥት ዘንድ የተሰጠው ትርጉም ሌላ ነው።

ለኢሕአዴግ ምሬት ያረገዘው የሕዝብ ጥያቄ ከሕዝቡ ከራሱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የመነጨ ሳይሆን በጥፋት ኃይሎች የተቀነባበረ ሕዝብን ለጥይት ከመማገድ ብርቱ ፍላጎት የተነሳ ነው። እዚህ ላይ ብዙ ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል። ሰሞኑን በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች የተነሱት ጥያቄዎች ዕውን ኢሕአዴግ እንደሚያወራው ሕዝቡን በምንም መልኩ አይጎዱትም? ሕዝቡ ዕቅዶቹን በተመለከተ የራሱ ጥያቄ ከሌለውስ ለምን ብሎ ነው ‹‹ለጥፋት ኃይሎች ድብቅ አጀንዳ›› ሲል በገዳዮች አፈሙዝ ትይዩ ደረቱን ሰጥቶ የሚቆመው? የኢትዮጵያ ሕዝብስ የሚባሉትን የጥፋት ኃይሎች (የጥፋት ኃይሎች ካሉ) አጀንዳ ተሸክሞ ወደ ሞት መንደር የሚያቀናው ምን ዓይነት ፖለቲካዊ የዋህነት ቢቆራኘው ነው? የጥፋት ኃይሎችስ ምን ያለ ምተሃት ቢኖራቸው ነው ይኼ ሁሉ ሕዝብ ያለ ምንም ዓላማ (ኢሕአዴግ እንደሚለው ለጥፋት አጀንዳ መሳካት) መተኪያ የሌላትን ሕይወቱን በምህረት የለሹ አፈሙዝ ፊት እንዲያስቀምጥ ያደረጉት? ኢሕአዴግ አመጣሁት እያለ ዘወትር የሚዘምርለት ልማት እንዴት ሕዝብ የጥፋት ኃይሎችን ምክር እንዳይሰማ አላገዘም? የጥፋት ኃይሎች የሚለው አገላለጽስ ከሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ማንነት ጋር እንዴት ይዛመዳል? ሰው የሆነ ፍጡር እንዴት የጥፋት አጀንዳ አንግቦ ለጥፋት ብቻ ይኳኋል ተብሎ ለሰሚ ይነገራል? የአገር ልማት ጸር፣ የወጡበት ሕዝብ ጠላት ሆኖ ጸረ ሕዝብ መሆንስ እንዴት ይቻላል?

እነዚህ ጸረ ልማት፣ ጸረ ሕዝብ አለያም የጥፋት ኃይሎች እየተባሉ በኢሕአዴግ መንደር የሚብጠለጠሉ አካላት ከኢሕአዴግ ጋር የአመለካከት ልዩነት ያላቸው፣ ከሰላማዊ እስከ ትጥቅ ትግል የደረሰ መንገድ ተጠቅመው ኢሕአዴግን ለመቀየር የሚታገሉትን ተቃዋሚዎች ለማለት እንደሆነ ኢሕአዴግን የሚያውቅ ሁሉ የሚረዳው ነው። ግር የሚለው ነገር ግን ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ‹‹የጥፋት ኃይሎችን›› ተከትሎ ‹‹የልማት አባት›› ነው ሲባል የኖረውን የኢሕአዴግን መንግሥት ሊንድ ተነሳ የሚለው አሰልቺ ፕሮፖጋንዳ ከራሱ ልማታዊ ነኝ ከሚለው መንግሥት መወሳቱ ነው።

ኢሕአዴግ አብዛኛውን ጊዜ ሕዝብ በራሱ ሕሊና አስቦ፣ ጥቅም ጉዳቱን መዝኖ የመንግስትን አካሄድ ተቃወመ ሲል አያጋጥምም። ይልቅ ሕዝብ የኢሕአዴግን መንግሥት ሲጠይቅና ሲቃወም በጥፋት ኃይሎች ተገፍቶ ነው ማለትን ይመርጣል። ‹‹ሕዝብ በራሱ አስቦ፣ የሚጠቅመውን ለይቶ፣ልማቱን የሚያስቀጥልለትን የመምረጥ ፖለቲካዊ ውሳኔ ሰጠ' የሚባለው ኢህአዴግ እንደምንም አድርጎ ተመረጥኩ በሚልበት የምርጫ ውጤት ላይ ብቻ ነው። የምርጫ ውጤቱ ትክክለኛ የሕዝብ ውሳኔ የሚሆነው ኢሕአዴግን መልሶ በመንበሩ የሚያስቀምጥ ከሆነ ነው። ይህ ኢሕአዴግ እስከዛሬ ያዘገመበት ፖለቲካዊ ዘይቤ ቢሆንም ሁልጊዜ ይሠራል ማለት ግን አይደለም። በተለይ ሕዝብን በሆነ አካል እየተነዳ አደገኛ የፖለቲካ ስህተት የሚሠራ የዋህ አካል አድርጎ ማቅረብ ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም። ከዚህ ይልቅ የሕዝብን ትክክለኛ የቅሬታ ምንጭ መርምሮ ወደ ትክክለኛው የመፍትሔ መንገድ መጓዙ ራስን ከማታለል ያድናል፤ ከአጉል አወዳደቅም ይታደጋል። በተረፈ መንግሥት የተያያዘው የጥፋት ኃይሎች እኩይ ተግባር በቁጥጥር ሥር ዋለ የሚለው አውጋዥ እና በፉከራ የታጀበ የፕሮፖጋንዳ አካሄድ ጋላቢ እሳትን በጋቢ ለማዳፈን እንደመሞከር ያለ አደገኛ መንገድ ነው።

የአገራችንን ፖለቲካዊ ትኩሳት ያናረው ወቅታዊው የሕዝብ ጥያቄ ከተለመደው የመንግሥት አውጋዥ ፕሮፖጋንዳ አለፍ ያለ ብስለትን የሚጠይቅ ፖለቲካዊ ውሳኔ ይሻል። ለዚህ ደግሞ በመንግሥት በኩል በድሮ በሬ ማረስን መተው አማራጭ የለውም። በድሮ በሬ ማረስን ለመተው ደግሞ ትክክለኛውን የሕዝብ ጥያቄ ከማድበስበስ ይልቅ በቅሬታውን ትክክለኛ ምንጭ ላይ ለመነጋገር የመድፈርን ብልህነት መልመድ ግድ ነው። ሰሞኑን በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች የተነሱት የሕዝብ ጥያቄዎች የአገሪቱን የመሬት ፖሊሲ፣ በተግባር አሐዳዊ መንግሥትን የሚያስንቀውን የይስሙላ ፌደራሊዝም፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን የአገርን ጥቅም የማስከበር አቅም፣ የዘር ፖለቲካን ብቻ ሙጥኝ የማለትን ትርፍና ኪሳራ ወዘተ. መፈተሽን ይጠይቃል።




---

ሩት አማኑኤል

# ዳያስፖራ ፎቢያ?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ እንደሚያሳየው አገሪቱ ከወጭ ንግድ ከምታገኘው ገቢ ይልቅ ከዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን የሚላከው ገንዘብ ይበልጣል። የትኛውም መንግሥት ቢሆን ይኼን ያህል አቅም ያለውን ኃይል ወደ ጎን ገፍቶ ደጋግሞ እንደሚናገረው ስኬታማ መሆን አዳጋች ይሆንበታል። በእርግጥ ዳያስፖራው መንግሥት ቢንከባከበውም ባይንከባከበውም ለወዳጅ ዘመድ ገንዘብ ከመላክ አይቆጠብም። አገሪቱ የባዕድ አገራትን ኢንቨስተሮች በእግር በፈረስ በምትፈልግበት በአሁኑ ወቅት፣ አቅም ያለው ኢትዮጵያዊ ወደ አገሩ ገብቶ መዋዕለነዋዩን እንዲያፈስ ቢደረግ አዋጭነቱ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም።

ይሁን እንጂ በመንግሥት በኩል አፍአዊ በሆነ መልኩ ከሚነገረው ባሻገር፣ አሁንም አብዛኛው ዳያስፖራ በጥርጣሬ ዓይን እየታየ ለመሆኑ ‹‹በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በምርጫ አይሳተፉም›› የሚለው ሕግ በቂ ማሳያ ነው። መመረጥም መምረጥም አይችሉም። እንዲያውም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው መኪናም ተከልክሏል። በአንዳንድ ደካማ ሰዎች ምክንያት ሁሉም ዳያስፖራ እንደ አጭበርባሪና ሌባ እየተቆጠረ ያለም ይመስላል። የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ጨምሮ የኢሕአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ወደ አሜሪካና አውሮፓ ጎራ ባሉ ቁጥር ከፍተኛ ተቃውሞና ውርጅብኝ እየደረሰባቸው ይመስላሉ እንጂ የአገሪቱን ዘላቂ ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ በሰከነ ሁኔታ ለውይይት ተጋብዘውም አያውቁም። በአገራችን ጠንከር ያሉ ተቃውሞዎች በተነሱ ቁጥር ከተቃውሞው ጀርባ ዲያስፖራው አለ የሚለው አደገኛ አካሄድ እየተለመደ መጥቷል። የአገዛዙ ሰዎች ዳያስፖራውን በጽንፈኛነት ይከሱታል፤ የመምረጥ መብቱን ይከለክሉታል ወዘተ. ዳያስፖራው ደግሞ በተራው እነሱን መድረክ ይከለክላቸዋል፤ ያዋርዳቸዋል። መደማመጥ ብሎ ነገር የለም።

በእርግጥ ከገዥው ቡድን ጋር የጠበቀ ቅርርብ ያላቸው ሰዎች ወደ አገር ቤት ተመልሰው የተለያዩ ሥራዎች በመሥራት ላይ ናቸው። አብዛኛው ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ግን አሁንም ከአገዛዙ ጋር ጥርስ እንደተናከሰና ለአገሩ ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅኦ ማበርከት ያልቻለ ነው። በፖለቲካው ድህነት ምክንያት አያሌ ምሁራንና ባለሀብቶች አገራቸውን ማገልገል አልቻሉም።

ዳያስፖራውን እንደ ጽንፈኛና አደገኛ ኃይል የማየቱ አዝማሚያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተቃዋሚው ጎራም መታየት ጀምሯል። በእርግጥ በዚህ ጉዳይ ላይ ከፖለቲካ ድርጅቶች በተጨማሪ ምሁራንም ጽፈውበታል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር የሆኑት ዶ/ር አስናቀ ከፍያለ ለምሳሌ ‹‹The (Un)making of Opposition Coalitions and the Challenge of Democratization in Ethiopia, 1991-2011›› በሚለው ጽሑፋቸው ዳያስፖራው በተለይ በውጭ የሚኖሩት የፖለቲካ ኃይሎች በተለያዩ ወቅቶች የተፈጠሩትን ትብብሮችና ቅንጅቶች በከፍተኛ ደረጃ እንዳዳከሟቸው ገልጸዋል። ብዙ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ዳያስፖራው በአገር ቤቱ ፖለቲካ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያደረሰ እንደሆነ መግለጽ ጀምረዋል።

‹ዳያስፖራው በአገር ቤቱ ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለው መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ግን በእኛ ግምት እንደሚባለው ከዳያስፖራው ጽንፈኛ መሆን አለመሆን ጋር የተያያዘ አይደለም። ለምሳሌ የእስራኤልንና የሜክሲኮን ዳያስፖራ ካየን፤ በዚህ ረገድ ከኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ጋር በጣም ተመሳሳይ ናቸው። ለሚፈልጉት ወይም ለሚያምኑበት ድርጅት ገንዘብ ይሰጣሉ፤ ገንዘባቸውን ከሰጡ በኋላ እነሱ የሚፈልጉትን አጀንዳ እንዲያስፈጽም ጫና ያደርጉበታል። ይህ ደግሞ በየትኛውም ዓለም ያለ አካሄድ ነው። የአገር ቤቱ ፖለቲካ እስካልተስተካከለና ተቃዋሚዎችን የሚደግፉ አካላት በአገዛዙ በልዩ ልዩ መንገድ መቀጣታቸው እስካልቆመ ድረስ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከአገር ቤቱ ሕዝብ ጨርሶ ገንዘብ አያገኙም፤ ስለዚህም የዳያስፖራውን ድጋፍ የግድ ይፈልጋሉ። ገንዘብ ከተቀበሉ ደግሞ ተጽዕኖው ይኖራል፤ የሚጠበቅ ነው።

ገንዘቡን አምጡ ተጽዕኗችሁን አቁሙ ማለት የሚያስኬድ አይመስለንም። ይልቁንስ ስለሥራ ክፍፍል እና ከተለመደው ልብ አውልቅ አካሄድ ተምሮ አዲስ ዘይቤ ለመቀየስ መወያየቱ የተሻለ ይሆናል። ለምሳሌ ያህል ዲያስፖራው ከእስካሁኑ የተበታተነ፣ በገንዘብና በድርጅታዊ አቋሙ የተውሸለሸና በደራሽ አጀንዳዎች ተጠምዶ የሚፍገመገም አፍራሽ አካሄዱ ትምህርት ወስዶ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በሰው ኃይልና በድርጅታዊ ጥንካሬው የደረጀና የሚያስመካ የመብት ተሟጋች ድርጅት ወይም ድርጅቶች የሚያቋቁምበትንና ጠንካራና ቀጣይነት ያለው የዲፕሎማሲና የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል፤ ይገባልም።

አገዛዙ የሚቃወሙትን ኃይሎች የገንዘብ ምንጭ ለማድረቅ ሌት ከቀን እንደሚሠራ ይታወቃል። ዲያስፖራው ተቃዋሚ ድርጅቶችን እንዳይደግፍ የማይደረግ ጥረት የለም። ብዙ ወገኖች የአገዛዙን መጠነ ሰፊ የእመቃ እርምጃ ተቋቁመው ተቃዋሚ ድርጅቶችን ለመደገፍ ጥረት የሚያደርጉትን ወገኖች በጽንፈኛነት መክሰስ ዋጋ የሚያስከፍል አካሄድ ነው።

## ነጻ አስተያየት



አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)

# ሕዝብን የቀሰቀሰው የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር

ኢትዮጵያዊያን በዓለም የምንታወቅበት ዐቢይ ጉዳይ ኢትዮጵያ እንደ አገር ከተመሠረተችበት ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ፤ ዕውቅና ያላቸው ተከታታይ መንግሥታት ሕዝባቸውን በማስተባበር፤ ግዛታዊ አንድነቷን፤ ሉዓላዊነቷንና ነጻነቷን ለመታደግ ያልተቆጠበ ትግልና ጥረት ማድረጋቸው ነው:: የኢትዮጵያ ታላቅነት መሠረት ይኼው ነው:: ተከታታይ የውጭ አደጋ ሲከሰት፤ ኢትዮጵያዊያን ጎሳ፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ ሀብትና ዕድሜ ሳይለዩ በጋራ ሆነው ንብረታቸውንና ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገውላታል:: ኢትዮጵያ ከቅኝ ገዢዎች ቀንበር ነጻ ሆና ለመላው የጥቁር ዓለም ምሳሌ መሆኗን የታሪክ ባለሞያዎች ዘግበውታል:: ይኼ ዓለም ያደነቀው ተከታታይ ታሪክና ዕውቅና የሁሉም ኢትዮጵያዊያን አገር ወዳድነትና መስዋዕት ከፋይነት ውጤት ነው:: እንደማንኛውም አገር፤ በዚህ ሒደት የተገለለና የተበደለ የለም ማለት አይደለም:: በውጭ ጠላቶች የተከበበ አገር ከእርስ በርስ ንትርክ፣ ግድያ፣ የበላይነት ወዘተ. ራሱን ንጹሕ ሊያደርግ አይችልም::

በአብዛኛው ኢትዮጵያን ለማጥቃት የሚመኙ የውጭ ኃይሎች መግቢያ ያደረጉት በሰሜን ቀይ ባሕርን፤ በምዕራብ የአባይ ሸለቆ አካባቢዎችን፤ በተለይ ኢትዮጵያን ከሱዳን የሚያዋስኑትን ከጋምቤላ ጀምሮ እስከ ኤርትራ የሚያዋስናትን ቦታዎች ነው:: ይኼ አደጋ አሁንም ዓይኑን አፍጥጦ ይታያል:: ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዳይኖራት፤ አባይን ለመቆጣጠርና ለማልማት እንዳትችል ለማቀብ በተከታታይ ጦርነቶች ተካሂደዋል:: ዝነኞቹ አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ መስዋዕት የሆኑትም በዚህ ምክንያት ነው:: አፄ ቴዎድሮስ እንኳን የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለውጭ ጠላት ወይም ወዳጅ መስጠት ቀርቶ አፈሯንም ፈረንጆች በጫማቸው ይዘው እንዳያወጡ ይከለክሉ ነበር የሚል ብሂል አለ:: ቱርኮች ባሕረ ነጋሽንና የቀይ ባሕርን ይቆጣጠሩ በነበረበት ዘመን ለማስለቀቅ ያላቸውን ፍላጎትና ውሳኔ በ1855 ዓ.ም. ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ብለዋል:: ‹‹ቱርኮች ግን ያባቶቼን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ፤ በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነው::›› የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢተባበር ኖሩ ምኞታቸው ታሪክን ይለውጥ ነበር:: መከፋፈሉ ሁሌም የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያስጠቃው ቆይቷል::

የታወቁት ደራሲ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ‹‹አፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት›› በተባለው መጽሐፋቸው ችግሩን በሚገባ አስምረውበታል:: ‹‹ኢትዮጵያ ረዥም የነጻነት ዘመንና የራሷ ባህልና የታሪክ ቅርስ ቢኖራትም፤ በሕግ አስተዳደርና በመንግሥታዊ አቋም ያልደረጀች በመሆኗ፤ በሆነ ባልሆነው በሰላም ሊወገድ በሚችለው በቀላል ምክንያት በነገሥታት፤ በመሳፍንትና በባላባት የግል ፍላጎትና የገዥነት ምኞት፤ በተሳሳተ ሰበብ አስባብ በሚቀሰቀሰው ጦርነት የዋሁ ወታደር ይሞታል:: ባላገሩም ይዘረፋል:: ባላገር ገብር ያሉትን እንደሚገብር፤ ጸሐፊም ጻፍ ያሉትን እንደሚጽፍ፤ ወታደርም ከነጦር መኮንኑ እሰር፤ ዝረፍ፤ ግደል ያሉትን ያለመንም ማመንታትና ጥያቄ ይዘርፋል፤ ይገድላል::›› ደሞዝ የከፈለ ሁሉ የሚፈልገውን አፈናና ግድያ ያደርጋል ማለት ነው:: ሆኖም፤ አገርን ለንግድ ማቅረብ የኢትዮጵያዊያን ባህል፤ እሴትና ልምድ አይደለም:: በሆነው ባልሆነው መነታረኩ የኢትዮጵያ ድንበሮች ለጣላቶቿ በር ሆነው እንዲከፈቱ ሁኔታዎችን ሲያመቻች ኖሯል:: ዛሬም እንደ ትላንቱ፤ ሁኔታው ተለውጧል ለማለት አይቻልም:: ኢትዮጵያ የባሕር በር የላትም:: ጥገኛ ናት:: ከሱዳን ጋር ያላት ድንበር አግባብ በሌለው ሁኔታ እየተቀየረ መሆኑን በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎችና ተቆርቋሪ የሆኑ በአገር ቤትና ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሲሚገቱበት ቆይተዋል::

ኢትዮጵያና ኤርትራ ብዙ የሚጋሯቸው ጉዳዮች አሏቸው፤ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ልማድ፣ የኢኮኖሚ ግንኙነት፣ ስትራቴጅክ የሆነ የጅኦግራፊ አቀማመጥ፣ ተደጋጋፊ የሆነ ጥሪት ወዘተ:: በሁለቱ ወንድማማች፤ እህትማማች ሕዝቦች መካከል ያለውን ጠቃሚ ግንኙነት የሥልጣን ጥመኞች ስለበከሉት ዛሬ አካባቢው በሙሉ፤ በተለይ ቀይ ባሕር የዐረቦች ምሽግ እየሆነ ነው:: ይኼን በሚመለከት ሌሎች ባለሞያዎች ትንተና ስላቀረቡበት፤ አሜሪካኖች ጭምር፤ ለጊዜው ወደጎን እተወዋለሁ:: የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ለራሱ የወደፊት ዕድልና ሕይወት ሲል በአንክሮ እንዲመለከተው የግል ምክሬን አቀርባለሁ::

የኢትዮጵያን ዳር ድንበር፤ ግዛታዊ አንድነት፤ ነጻነት፤ ክብር፤ ዘላቂ ጥቅም፤ ደህንነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር የሞቱት ኢትዮጵያዊያን ብዛትና የወደመው ሀብት ሊተመን አይችልም:: የሞቱት ተመልሰው መጥተው ለምን መስዋዕት ሆናችሁ? ብየ ብጠይቃቸው ምን መልስ ይሰጡኝ ይሆን እያልኩ እራሴን እጠይቃለሁ:: ልጆቸም የተከፈለውን ግዙፍ መስዋዕት እንዲያውቁ ጥረት አደርጋለሁ:: አፄ ዮሐንስ የአፄ ቴዎድሮስን ፈለግ ተከትለው በ1863 ዓ.ም. ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ የኢትዮጵያ መሪዎች ለአገራቸው ዳር ድንበርና የባሕር በር ተቆርቋሪ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል:: ‹‹በቅርብ ቀን ቀርቶ ነው እንጂ እንኳን እርስዎ የአውሮፓ ነገሥታት መላው ያውቃሉ:: የምጽዋ በር የአባቶቸ የነገሥታት ኢትዮጵያ ነው፤ አሁንም እንበለበር ቤተመንግሥት አይቀርምና በርስዎ ወኪልነት የምጽዋን በር እንድይዝ ያድርጉልኝ ዘንድ እለምናለሁ::›› የእንግሊዞች ሴረኛነትና ምስጢረኛነት እንዳለ ሆኖ ቁም ነገሩ ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት የኢትዮጵያን የባሕር በርና ዳር ድንበር ለመታደግ ያላደረጉት ጥረት የለም:: መስዋዕት የሆነው ግዙፍ ሕዝብ ከሁሉም ኢትዮጵያዊያን ጎሳዎችና ሃይማኖቶች የተወጣጣው፤ በተለይ የአገር መከላከያ ክፍሉ ነው ለማለት እደፍራለሁ:: አወዛጋቢ የሆነውን የኢትዮጵያንና የሱዳን ደንበር ጉዳይ የምመለከተው ከተከታታይ ታሪካችን አንጻር ነው::

የሥራ አስኪያጁ ቡድን አባል ሆኘ የማገለግለው የኢትዮጵያ የድንበሮች ኮሚቴ ከተቋቋመ ስምንት ዓመት ሆኖታል:: ኮሚቴው የተቋቋመበት ዋና ምክንያት ሕወሓት ከባለውለታው ከሱዳን መንግሥት ጋር በምስጢር ተደራድሮ በእርዝመቱ 1,600 ኪሎ ሜትር፤ በስፋቱ ከ20-60 ኪሎሜትር የሆነ፤ ከጎንደር ጀምሮ ጎጃምን፤ ወለጋን፤ ከፋን፤ ጋሙ ጎፋንና ወደ ደበቡ እስከ ጋምቤላ የሚደርስ ለም መሬት ለሱዳን ለመስጠት መወሰኑ በማያሻማ መረጃ ስለተደረሰበት ነው:: በወቅቱ ፈላጭ ቆራጭ የነበረው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፤ ለኢትዮጵያዊያን ጥቅምና ሕይወት ከማሰብ ይልቅ ለሱዳን መንግሥት ጠበቃ ሆኖ ተከራክሯል:: ስለ ሱዳኖች ይገባኛልነት ሲከራከር፤ ከአፄ ቴዎድሮስ፤ ከአፄ ዮሐንስ፤ ከአፄ ምኒልክ፤ ከአፄ ኃይለ ሥላሴና ከደርግ መንግሥት በተቃረነ አንደበት ‹‹ሱዳኖች የኢትዮጵያን ግፊትና ጫና ሲታገሱ ቆይተዋል›› በማለት የኢትዮጵያን መሬት ለወዳጁና ለባለውለታው መንግሥት ለማሸጋገር ሁኔታውን አመቻችቶ ነበር:: በዓለም ታሪክ ውስጥ፤ አንድ የመንግሥት መሪ ለራሱ ሕዝብ በመከራከር ፋንታ ለውጭ አገር ጠበቃ ሆኖ ሲሟገት የመጀመሪያው መሆኑ ነው::

የምንከራከርበትን ድንበር በሚመለከት በማስረጃና በዕውቀት ያልተደገፉ ነገሮች ሲወሩ

> **የሕወሓት መሪዎች በዚህ የአገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በሚያክል ትልቅ ጉዳይ ላይ ከዋናው የጉዳዩ ባለቤት ከሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የጀመሩትን ድብቅ ድርድር አጠናቀው ዛሬ አፋቸውን ሞልተው በቅርቡ ወደ ተግባር ለመተርጎም ቀነ ቀጠሮ መያዛቸውን ከራሳቸው አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ አንደበት እየሰማን ነው**

ቆይተዋል:: የዛሬው የጎሳ ፖለቲካ ብዙዎቻችን በመንደር ደረጃ እንድናስብ አድርጎናል:: የሚሰጠው መሬት ‹‹የጎንደሪዎች ወይም የአማሮች ነው›› የሚል ከእውነቱ የራቀ ፕሮፓጋንዳ ይሰማል:: ጥልቀት ያለው ጥናት ያሳየውና በቦታው የሚኖሩ፤ የሚሠሩ ኢትዮጵያዊያንና አካባቢውን የሚያውቁ ግለሰቦች ካርታ ተጠቅመው የሚከራከሩት የሚሰጠው መሬት ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ሌሎችን የሚመለከት ግዙፍ መሬት ነው::

ይኼ እንዳለ ሆኖ፤ ሱዳኖች በኢትዮጵያ ሕዝብ ግፊት ተጎድተዋል የሚለው የባለሥልጣናት አነጋገር ተከታታይ ድጋፍ አግኝቷል:: የድንበር ኮሚቴው ይኼን የአገሪቱን ደህንነትና ኢኮኖሚ የሚጎዳ አባባል ፈለግ በመከተል፤ ‹‹በቅርቡ የሕወሓትን ቡድን በሚወክል፤ ለሱዳን ቃል አቀባይነትን በሚያንጸባርቅ መልክ፤ የሱዳን መንግሥት ሳይጠይቅ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የሱዳንን ምክትል ፕሬዚዳንት ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት በሰጡት መግለጫ በያዝነው ወር ውስጥ የኢትዮጵያ የሱዳን ድንበር በመሬት ላይ የመካለሉ ሥራ እንደሚጀመር በድፍረት የሰጡት ቃል የኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴን ጨምሮ መላው የኢትዮጵያን ሕዝብ በእጅጉ ያሳዘነና ያሳፈረ ከፍተኛ የአገር ክህደት ወንጀል ነው›› የሚል መግለጫ በትኗል:: የኮምቴው መግለጫ ቀጥሎ ‹‹በሟቹ አቶ መለስ ዜናዊ ሥር የተተኩት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የተረከቡት የመንግሥት ሥልጣን ብቻ ሳይሆን፤ እሳቸውም እንደ አቶ መለስ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ማፍረስና የአገሪቷን ህልውና ማናጋት ነው›› ይላል:: እኔ እስከማውቀው ድረስ ኮሚቴው ከማንም የፖለቲካ ቡድን ጋር ልዩ የሆነ ግንኙነት የለውም:: ስለሌለው ጉዳዩ ብሔራዊ መሆኑን የተገነዘቡ፤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ወደ ስድሳ የሚሆኑ የመገናኛ፤ የወጣቶች፤ የሴቶች፤ የሃይማኖት፤ የሲቪክ ማኅበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች በመተባበር ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ለክቡር ባን ኪ ሙን የሚላከውን አቤቱታ ፈርመዋል:: በኋላ ሆኖ የገፋቸው ኃይል የለም:: በሃይማኖት፤ በጎሳ ወዘተ. ልዩነቶች ያሏቸው ስብስቦች በጋራ ሆነው ሰነዱን የፈረሙበትና ብዙ ሺህ ሕዝብ እንዲፈርም የሚቀሰቅሱበት ዋና ምክንያት ጉዳዩ የሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የወደፊት ሕይወትና ኑሮ፤ የአገሪቱን ግዛታዊ አንድነት፤ ክብር፤ ነጻነትና ሉዓላዊነት ስለሚመለከት ነው:: ‹‹ይኼ የአገር ጉዳይ ካልሰበሰበን ምንም ጉዳይ ሊሰበስበን አይችልም›› የሚሉ ብዙ ናቸው:: ገዥው ፓርቲ በረባ ባልረባው፤ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ሥልጣን ሲባል አገር እንደ ፍሪዳ እየሸራረፈ ለውጭ መንግሥታት የሚሰጥ ከሆነ ‹‹ዳሩ መሐል መሆኑ የማይቀር የአገዛዝ ውጤት ይሆናል›› የሚል እምነት ያላቸው ግዙፍ እንደሆኑ ይታወቃል::

አቤቱታውን የፈረሙት ስብስቦችና ግለሰቦች በኢትዮጵያ የሱዳን አምባሳደር ኦስማን ናፊ (November 23, 2015) ‹‹Assayha›› ለተሰኘው የዐረብ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ መጠይቅ፤ ‹‹የድንበሩ ጉዳይ አዲስ አይደለም፤ የቆየ ነው:: ኢትዮጵያና ሱዳን በወዳጅነት የሚኖሩ አገሮች ናቸው…የኢትዮጵያ ዜጎች የሆኑ በአካባቢው የሚኖሩ አማራዎች ድንበር እየጣሱ መሬታችን ያርሳሉ ዜጎቻችን ገድለዋል… አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ጎሳ ከትግራይ ነው … እኛ የምንቀበለው ድንበር ቻርለስ ግዌን የቸከለውን ነው›› ወዘተ. ያለውን ሁሉ በጽሞና አዳምጠውታል፤ ተወያተውበታል:: ‹‹የግዌንን ችካል አልቀበልም ያለ ማነው? የፌደራሉ መንግሥት ወይስ የአማራው ክልል?›› ለሚለው ጥያቄ ልክ ሁለት መንግሥታት እንዳሉ ተቀብሎ፤ ናፊ የአማራው ክልል የሚል መልስ ሰጥቷል:: የሕወሓት መሪዎች ልዩ ውለታ አለባቸው የሚለውን መሰረታዊ ጉዳይ ያጠናከረው፤ አምባሳደር ናፊ የተናገረው እንዲህ ይላል:: ‹‹The regime currently governing Ethiopia came out of the womb of Khartoum, Sudan››

በጠቃላይ ሲታይ ከላይ አምባሳደሩ የተናገረው አከራካሪ ሊሆን ይችላል:: በእኔ ግምት የኢትዮጵያ ሕዝብ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ለሚከተለው ነው:: ‹‹በአሁኑ ጊዜ የድንበሩ ጉዳዩ ስትራተጂክና ትኩረት የምንሰጠው አይደለም፤ የእኛን አስተሳሰብ አይበክለውም:: እኛ ለድንበሩ ብለን የኢትዮጵያን ወዳጅነት ለማጣት አንፈልግም::›› በዋሽንግቶን የሚገኘው የሱዳን አምባሳደርም የነገረን ተመሳሳይ ነው:: ‹‹ችግሩ የመንግሥታችሁ ስለሆነ ሰልፉን ማድረግ ያለባቸው በኢትዮጵያ ኤምባሲ ነው፤ እኛ ስለ ድንበሩ ያነሳነው ጉዳይ የለም›› ብሏል:: ታዲያ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ማንን ወክሎ ነው ድርድር ለማድረግ የፈለገው? የሚለውን ጥያቄ መልስ ለአንባቢ እተወዋለሁ::

የድንበር ኮሚቴው መግለጫ እንዳሳሰበው፤ ኮሚቴው ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ፤ ለበርካታ ዓመታት ባደረገው ‹‹የተቀነባበረ ክትትል የሕወሓት ገዢ ቡድን ከሱዳን መንግሥት ጋር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በሚዳፈርና ዘለቄታዊ ጥቅማችንን ለባዕዳን አሳልፎ በሚሰጥ መልኩ በድብቅ እየተሸረበ ያለውን ደባና አሳፋሪ ተግባር በተገቢ ጥናትና በመረጃ ላይ ተመስርቶ በተከታታይ ሲያጋልጥ ቆይቷል:: ይሁን እንጂ የሕወሓት መሪዎች በዚህ የአገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በሚያክል ትልቅ ጉዳይ ላይ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# ነጻ አስተያየት

ብሩክ ከበደ

# በአፈርና ብሶት የተቦካ አብዮት

ወደ ጽሑፌ ከመግባቴ በፊት ሰሞኑን በመንግሥት ወታደሮችና የጸጥታ ኃይሎች ጥይትና ዱላ የተገደሉ ቁጥራቸው ወደ 90 የሚጠጉ እንዲሁም የቆሰሉና አድራሻቸው የጠፋው ከ2 ሺህ በላይ የሆኑ ወገኖችን ጨምሮ በሥነ ልቦናቸውና ንብረታቸው ላይ ከፍተኛ አደጋ ለደረሰባቸው ወገኖች የተሰማኝን ጥልቅ ሀዘን እገልጻለሁ፡፡

ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ ሕዝብ በሚከፍለው ታክስና ግብር ለክፉ ቀን ተብሎ እንዲደራጅ የሚደረገው የመከላከያው አካል አንድ ክንፍ የሆነ ክፍል ከሂሊኮፍተር ላይ በገመድ እየወረደ ቢያንስ በነፍስ ወከፍ የሚወረውረው ድንጋይ ብቻ በያዘ ወገን ላይ የጠላት ምሽግ የማስለቀቅ ዓይነት ጀብዱ ሲፈጽም ከመስማት በቀር የሚያም ምን ነገር ከቶ ይፈጠር ይሆን? በዚህ በሰሞኑ ጥፋት አመያ ላይ ቤት ንብረታቸውና ሕይወታቸው እንዲጠፋ ሆን ተብሎ በአገር አልባዎቹ ፖለቲከኞች በተደረገው ዘመቻ የሴራው ሰለባ ለሆኑ ወገኖቻችንም የተሰማንን ሀዘን ስንገልጽ በምሬት ነው፡፡ በክልሉ ብቻ ታጥሮ እንዲቀርና በመላው ኦሮሚያ ተበትኖ ለሚገኘው አማራ ድምጽ ለመሆን ያልቻለው ድምጽ አልባው ብአዴንም በ35ኛ በዓሉ ዋዜማ ዳግም ወደ ከርሰምድር የገባበትን ፖለቲካዊ ኪሳራ ነው፡፡

አሁን ወደ ዛሬ ጽሑፌ ልመለስ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ አገራት ለመነሣታቸው ቀዳሚ የሆኑ ምክንያቶችን አይረሴ ስም መስጠት በመላው ዓለም የተለመደ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ መጠሪያውን እንደሌላው ስያሜ ሁሉ እንዲህ በቀላሉ የማይረሳ ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ ሥር ነቀል ስያሜ መሆኑ ደግሞ ብቸኛ ያደርገዋል፡፡ ይኸን ብቸኝነቱን በሁለት እግሩ ለማቆም ደምና ላብ ተዋሕደው የሚበጠብጡት ቀለም በሞት ጀርባ ላይ በደማቁ አስፍረው ሕያውነትን የሚያሰፍሩበት መሆኑ ትልቅ ድጋፍ ሆኖታል፡፡

ለዋቢነትም የሰሜን አፍሪካንና መካከለኛ ምሥራቅ አገራትን የናጠውና ለአምባገነኖች ውድቀት የነበረው ምስኪኑና ሰማዕቱ መሐመድ ቡአዚዝ የቀሰቀሰው የአረቡ ፀደይ አብዮት የዩክሬኑ ብርቱካናማው አብዮት፣ ማህተመ ጋንዲ የመሩት ‹‹ሶልት ማራች›› (ምንም እንኳን በቅኝ ገዥዎች ላይ የተነሳ ቢሆንም) ወዘተ. ማንሳት ይቻላል፡፡ ወደ አገራችን ስንመለስ ወታደር ከሲቪሉ ጋር በማበር ያቀጣጠለው የወርሐ ታኅሣሥ 1953 ዓ.ም የለውጥ እንቅስቃሴ የታኅሣሥ ግርግር፣ ታላቁ 1966 ዓ.ም ሕዝባዊው ማዕበል ግብታዊ አብዮት፣ በ1997 ዓ.ም. ድምፄ ይከበር የሚለውን ጨምሮ በዚህ ታኅሣሥ ወር የመሬት ወረራ ያስነሳው ሕዝባዊ አመጽ የበርካታ ዜጎችንና ንብረት ቀጥፏል፡፡ ይኸው መሬት መሠረት ያደረገው ንቅናቄ ከዛሬ አንድ ዓመት ከስምንት ወር በፊት በለውጥ ምድሯ አምቦ ተከስቶ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡፡ ከጥፋት ማስጠንቀቂያው በኋላ በምን ይመጣል ይሁን አሊያም የሕዝብ ጥያቄን መቀበል እንደሽንፈት በሚቆጥሩ ትምክህተኞች ወይም ሥርአቱን የፊጥኝ ይዘው በሚዘውሩ ሙሰኞች ሴራ ምላሽ ባለማግኘቱ ዳግመኛ ሌሎች የተዳፈኑና የተዘለሉ ነገር ግን የጋሙ (የበሰሉ) አብዮቶችን ይዞ ተመልሷል፡፡

የመሬት ዘረፋና ቅሚያን በመቃወም የተጀመረው አብዮት ከመቀጣጠሉ በፊት የጐንደር ወህኒ ቤት በእሳት መያያዙን ተከትሎ በርካታ ቁጥር ያላቸው እሥረኞች በመንግሥት ጸጥታ ኃይሎች ሕይወታቸውን እንዲያጡ መደረጋቸው የሕዝቡን ልብ በማድቁና ሕዝቡ ውስጡ ከታመቀው ፍትሕ እጦት፣ በልማት ሰበብ ከቀዬ መፈናቀል፣ የሃይማኖት ተቋማት ዝቅጠት፣ ረኀብ፣ ስደት ወዘተ. ያንገሸገሻቸው ነገን የማይናፍቁ የትየለሌ ቁጥር ያላቸው ዜጐች የመሬት ወረራን አብዮት የራሳቸው አብዮት አድርገው ቢቀበሉት ታዓምር አይሆንም፡፡

ዜጐች በዕውቀታቸው፣ በታማኝነታቸው፣ ሕዝባዊና አገራዊ ፍቅራቸው፣ አመለካከታቸው የሚመዘኑበት ሁኔታ አክትሞ የመንግሥቱንም ሆነ የግሉ ዘርፍ ሥራ ሁሉ ጐጥና ዘር፣ ፖለቲካንና ገባርነትን ተኮር ማድረጉና በዚህ ሥር የሚሰባሰቡት ደግሞ እጅግ ኢምንቶች ሆነው ሳለና አብዛኛው በገዛ አገሩ ባይተዋር ከመሆኑ አልፎ የባሕር አውሬዎች ሲሳይና የአረመኔዎች ካራ መለማመጃ፤ የዐረብ መጫወቻ ሲሆን ለምን ያላሉ ዛሬ ተራቸውን እንቅልፍ ቢያጡም የሚገርም አይደለም፡፡

በአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ ከጉልት ቸርቻሪነት ሊስትሮነትና እስከ ሰላም አስከባሪነት ኮሪያና ኮንጐ በመዝመት በዓለም ላይ አኩሪ ስም ያስመዘገቡ ወታደሮቻችን፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ከዕውቀት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቀው ለትውልድ ሻማ የለኮሱ መምህራን፣ የተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት ሠራተኞች ወዘተ. ካለቻቸው ጥሪት እየቀነሱ ወይም ፋሺስትን የተፋለሙ አርበኞች መንግሥት በሰጣቸው መሬት ላይ እዚህ ግባ የማይባሉ ለራሳቸው መኖሪያና ከ2 ብር ጀምሮ ደግሞ የሚከራዩ ቤቶችን አገራዊ መብታቸውን ተንተርሰው ሲገለገሉ ቆይተው በ1966 ወር ተረኛ የነበረው ኮምኒስታዊና ወታደራዊው አገዛዝ ዜጐች ያከራዩዋቸውን ቤቶች በትርፍነት ሲረከብ እንደ አቅማቸው አበል በየወሩ እንዲቀበሉ ቆራርጦ ባዶ መሬት ካላቸው መሬታቸውን ሳይወርስ ነበር፡፡ ጨፍጫፊና ጨቋኝ ነበር እያለ የሚያብጠለጥለው ኢሕአዴግ የወር ደመወዛቸው 50 ብር ጀምሮ የሚያገኙ ወገኖች በማኅበር ተደራጅተው የብድር አገልግሎት እንዲያገኙና የቤት ባለቤት እንዲሆኑ ሲያደርጋቸው ነጻ መሬት ከ250- 500 ካሬ መሬት በነጻ እያቀረበ አገርኛው ባሕር ዛፍ፣ ጤና አዳምና ዳማ ከሴ፣ ኮባ፣ ጎመን ወዘተ. በመትከል ለአካባቢ ጥበቃና ለጤና ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያደርግ ታስቦ የታለመውን ኢኮኖሚያዊ፣ ሶሻላዊና ጤናማዊነት መብትን ኢሕአዴግ እያንዳንድሽ ከጣራና ግድግዳ በላይ መብት የለሽም በማለት እጅግ ሰቅጣጭ በሆነ የመሬት ስሪት ፖሊሲ መሬትን በልማትና በሊዝ ስም እየቀማ ጥቂቶችን ሲያደልብ ዋንጫውን በደምና በእንባ እየሞላ መሆኑን ልብ አለማለቱ አመራሩን የያዙት ጥቂቶችን እውቀት ግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ ጥቂቶች በቦታ ካርታ ቁማር እስከመጫዎት ሲደርሱና በመሬት ሽያጭ መልቲ ሚሊየነር ሲሆኑ ዜጎች ግን ያልተመለሰላቸውን የመሬት ጥያቄ ይዘው እንደሚዞሩ የማውቀው ነገር የለም የሚል ከፍተኛ ሹም ዛሬ ድንገት ብቅ ቢል የሚገርም ላይሆን ይችላል፡፡ ለምን ቢሉ ኢሕአዴግና ሕዝብ ከተለያዩ ከርመዋል፡፡ ኢሕአዴግ ያለው በሪፖርትና በአበልተኞች አባል ፕሮፖጋንዳ ነውና፡፡

ኢሕአዴግ አዲስ አበባ የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎችን ሳይቀር ቸብቸቦ እግር ኳስ ተጫዋቾችና የሌላ መስክ ስፖርተኛን ማምከኑ አንሶ አሁን አሁን ደግሞ ወደ ታቦት ማደሪያ ስፍራዎች ላይ ቀልቡን አዙሯል፡፡ ገዥው ፓርቲ አቅመ ቢስ መሬቶች ላይ እንቅልፉን ለምን እንደሚያጣ የማይታወቅ መስሎት ከሆነ ቀሽም እሳቤ ነው፡፡ በተለይ ኢሕአዴግ ከልቡ ላልሆነውና በመቶዎች የሚቆጠሩ ሚሊዮኖችን ዶጋ አመድ አድርጎ የሚያካሂደው ምርጫ ሲቃረብ በከተማዋ የሚገኙ ባዶና ኪስ መሬቶች ቀድመው ለምን እንደሚታጠሩም ሆነ እንደሚቆፈሩ ሕዝቡ አያውቅም የሚል ኢሕአዴጋዊ ሆነ ነፋስ አመጣሽ ባለጸጋ የሰሞኑ አብዮት ማወቁን እንዲያውቅ በቂ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ነው፡፡ ቻይና የምትሰጠው እስከሆነ ድረስ፡፡

ቀደም ሲል የርዕዮተ ዓለምና የመደበኛ ትምህርት አስተማሪና የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር ዲኤታ አጨቃጫቂው የጸረ ሽብር ሕግ ሲወጣ ለመጀመሪያ ጊዜ በቴሌቪዥን መስኮት ቀርቦ ማብራሪያ የሰጠውና በአሁኑ ጊዜ ኢሕአዴግን ከድቶ በስደት የሚገኘው ግለሰብ ‹‹የመለስ ትሩፋቶች›› በሚለው መጽሐፉ ባለቤት አልባ የሆነችው አዲስ አበባ የሚገኘውን መሬት ከሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ጀምሮ መሬት እንዳሻቸው እንዴት እንደሚያከፋፍሉ በሚገባ ተንትኖታል፡፡ ጦር ሜዳ የሚገኙ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች በሄሊኮፍትር ሳይቀር እየመጡ መሬት ተረክበው ሸጠው እንደሚሄዱ ሲነግረን የመኮንኖች አገር የት እንደሆነ ለማወቅ ተቸግሬያለሁ፡፡

ኢሕአዴግ በ1997 ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ ሕዝቡ ድምጽ ሲነፍገውና ለገና ከተማዋን ላስረክብ ነው በሚል ከተማዋ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሶሻላዊ ጠቀሜታዋ ሽባ እንዲሆን በርካታ ዘግናኝና ከአንድ አገር ሊመራ ቤተ መንግሥት ማረፊያውን ካደረገ መንግሥት የማይጠበቅ ተግባር ባሻገር የአዲስ አበባ ወርድና ስፋት በማጥበብ የቀራኒዮ መድሐኒዓለምን ቤተክርስቲያን የመቃብር ይዞታ ለሁለት በመግመስ ከወዲያ ያለው የኦሮሚያ ይዞታ ነው ሲል ችካል ማኖሩን ረሳና ዛሬ አዲስ አበባ መቶ ኪሎ ሜትር ራዲየስ ካልተለጠጠች በሚል የሕዝቧን ጥያቄ በአፈሙዝ ለመደፍጠጥ መነሳቱ ምን ያክል የመሬት ሱሰኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

እነ ዋለልኝ መኮንን፣ ጥላሁን ግዛው፣ እሸቱ ጮሌ፣ ኢብሳ ጉተማን የመሳሰሉ የተሟገቱለት፣ የሞቱለት፣ የተሰደዱለት የመሬት ጥያቄ በ1966 ዓ.ም. አቢዮት አንድ ደርዝ የያዘ ቢመስልም ከ1983 ዓ.ም. በኋላ እንደገና በሌላ ጭርሱንም ባዕዳንን ሁሉ ያካተተ ዝርፊያና ወረራ የሚፈጸምበት ሆኖ መምጣቱ ያ ትውልድ ቢኖር ኖሮ ምን ይል ነበር! የሚያሰኝ መላሽ አልባ ጥያቄን ያጭራል፡፡ በውርስ ኢሕአዴግ የግል ይዞታ የክብርና የአገራዊ ስሜት መጠበቂያ መሆኑ ቀርቶ ቁማርተኞቹ በየካዝናው ጠረንጴዛ ላይ የሚጥሉት፣ በደምና በውርስ የሚገኝ የትውልድ መብት መሆኑ ቀርቶ በሩካቤ የሚገኝ የፍትወት መለኪያ፣ በዘርና በፖለቲካ ቀረቤታነትና ምስለኔነት ድረስ እንዲወርድ መደረጉ መሬት ለሰፊው ሕዝብ ለተሰኘው ለውጥ ነፍሳቸውን ላልሳሉ ንጹሀን ተላላዎች በክብር እንዲያርፉ ሳይሆን በግልባጩ ነፍሳቸውን አይማረው ከሚል እርግማን እንዳይወጡ መደረጉ ለቋሚው ጸጸት ነው፡፡

> **ይኸው የአማራ ክልል ሙሉ ለሙሉ ከሱዳን ጋር ያለውን ተጎራባችነት የሚያጠፋውን መስመር ለማስመር ኢሕአዴግ እጁን ሲዘረጋ የቅኝ ግዛት ውል መሠረት አድርጎ ሲሆን አባይን ለመገደብ ሲነሳ ግን ግብጽና ሱዳን ኢትዮጵያን ሳይጨምሩ በተናጠል ከእንግሊዝ ጋር ያደረጉትን ያረጀና ያፈጀ የቅኝ ግዛት ውል አልቀበልም በሚል አቋም ነበር**

ለኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወደብ አሰብ፣ ቀይ ባሕር ለምትገኘው ሀኒሽ ደሴት (ከ1983 ዓ.ም. በኋላ ለየመን ተሰጧል) መሄድ ቁብ ያልሰጠው ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት ሱዳን ታስተዳድረው የነበረችው እንግሊዝ ሻለቃ ብቻውን የከለለውን መስመር የሱዳን መሬት ነው በሚል ከጎንደር እስከ ጋንቤላ ከአንድ ሽህ ኪሎ ሜትር በላይ እርዝመት ያለውና ወደ ውስጥ በአማካይ እስከ 50 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ለም መሬት በህጋዊ መልኩ ለማስረከብ ውይይቶች እየተጀመሩ መሆኑን እሰማን ነው፡፡ ይኸው የአማራ ክልል ሙሉ ለሙሉ ከሱዳን ጋር ያለውን ተጎራባችነት የሚያጠፋውን መስመር ለማስመር ኢሕአዴግ እጁን ሲዘረጋ የቅኝ ግዛት ውል መሠረት አድርጎ ሲሆን አባይን ለመገደብ ሲነሳ ግን ግብጽና ሱዳን ኢትዮጵያን ሳይጨምሩ በተናጠል ከእንግሊዝ ጋር ያደረጉትን ያረጀና ያፈጀ የቅኝ ግዛት ውል አልቀበልም በሚል አቋም ነበር፡፡ ከሻዕብያም ወረራ በኋላ ከሻቢያ ጋር ስለ ኢትዮ-ኤርትራ ድንበር አልጀርስ ላይ ሲወያዩና ውይይቱንም ተቀብሎ ፊርማውን ሲያኖር የተቀበለው የ1890ዎቹ የቅኝ ግዛት ውል ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ክስተቶች የሚጠቁሙት ኢሕአዴግ መሬትን እንደፋሽን ሾው የሚመለከተው እንጂ ቋሚ መርህ የሌለው ለመሆኑ በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ኢሕአዴግ ዛሬ እንደልቡ የሚምነሸነሽበትን መሬትን እነዚያ የነገዋን ኢትዮጵያ በአርበኝነቱም፣ በዘመናዊ ሥልጣኔም በሁለት እግሯ እንድትቆም ያስቻሏት በደም በአጥንታቸውና በበሳል ዲፕሎማሲያዊ ጥበባቸው ነው፡፡ ለአብነት ያክል ዕውቁ ዲፕሎማት አክሊሉ ሀብተወልድ አገር በሰፋች ቁጥር በተፈጥሮ ሀብቷና በሰው ኃይሏ ፈርጣማ እንደምትሆን በማወቃቸው ጋምቤላንና ኦጋዴንን ከእንግሊዝ፣ ኤርትራን ከጣሊያን አገዛዝ አላቀው ከአገራቸው ጋር የቀላቀሏቸው ከሁለቱም ወገን አንዲት ጥይት ሳትተኮስ ነው፡፡ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያን የሚያውቋትና ከአንድ ጎጥ የተሰባሰቡት ገዥዎቻችን ኢትዮጵያ ሰፍታባቸው ካልጠበበች እንደማይቆጣጠሯት በመገመት ዙሪያዋን እየሸራረፏት ይገኛሉ፡፡ ሰሞኑን ከጋምቤላ የደረሰኝ አንድ ታሪክም በዚሁ መስመር የሚፈስ ይመስላል፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ ጋምቤላ መሐል ከተማ የምትገኘውና በ1978 ዓ.ም. ደርግ ባካሄደው ሕዝብና ቤት ቆጠራ ጋምቤላዊው ከሚሞላው መጠይቅ መሐል ሃይማኖት በሚለው ሥር ‹‹ኪዳነ ምህረት›› የሚልለት አጥቢያው ጊቢ ዛሬ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ይገኛል፡፡ ‹‹…. በደቡብ ሱዳን ክልል አገረ ስብከት የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን…›› ጎበዝ! ይህ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የምታውቅ ካለህ ወዲህ በለን፡፡

ኢሕአዴግ ከ1983 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ በሕዝብና በአገር ላይ ታሪክ ይቅር የማይለውን ዘርፈ ብዙ ግፍ ሲፈጽም መቆየቱ አንሶ ከወዳጁ ሻዕብያ ጋር ዓይንና ናጫ ሲሆን ያዋረደውን ወታደር፣ ነጋዴ፣ አርቲስት፣ የሕክምና ባለሙያ ወዘተ. ሰብስቦ አስጥሉኝን ድሉ እንደተቀለበሰ በክፉና መሰሪ አገዛዙ ሥር ዙሪያ ለማጧጧፍ ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ ኢህአዴግ ቆዳውን እንደ እስስት እየለዋወጠ የመከራ ዘመኑን ማርዘሙ በድጋሚ ያስከፋው ሕዝብ ኢሕአዴግ እንዴት እንዳመለጠው እስከዛሬም ባልገባው ምርጫ ሒደት ሕዝብ በቃኸኝ፣ አንገሸገሽከኝ፣ ሲል በሰላማዊ ካርድ ቢቀጣውም እንደ እባብ አፈር ልሶ በመነሳት ጮሌው ፖለቲከኛና መሠሪ የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ መስቀል አደባባይ ለተሰበሰበው ለአበልተኛና ለአውርቶ አዳሪ ‹‹…ሕዝቡ ድምጹን የነፈገን ጠልቶን ሳይሆን ሊያስተምረንና ሊነግረን ፈልጎ ነው…›› ሲሉ ከምርጫ ሳይንስ መስፈርት ውጭ ሲናገሩ ተጨበጨበላቸው እንጂ ተው ያለ ባለመኖሩ ብሶቶች ዘረፋቸውን እንደአምባሰል አባዙ፡፡ መብቱንና ጥያቄውን በጥይት ሳይሆን በምርጫ ካርድ ለማግኘት የጠየቀን ሕዝብ አንተ አታውቅም እኛ መቶ በመቶ አሸንፈንሃል አርፈህ ቁጭ በል ማለት ብሶቱን የሚነግሩለትን ተወካዮች ከጨዋታ ውጭ አደረጉለት፡፡

የቀድሞው የአገሪቱ ፕሬዝዳንት የነበሩትና አሁን ከሠፊው ሕዝብ አንዱ የሆኑት ዶ/ር ነጋሶ ገና ጎህ ሳይቀድ ከፓርቲያቸው ከኦሕዴድ ለመለየታቸው ምክንያት የሆናቸውን ሲያስቀምጡ በየቦታው ያሉ የኦሕዴድ ሰዎች ትላልቅ ወርቅ እያጠለቁ፣ የቆዳ ጃኬት እየለበሱ አርፈው ተርፈው ባለትዳር ሴት ሲያማግጡ ውሎ አዳራቸው ባንኮኒ መደገፍ መሆኑን በቀጥታ አስፍረውታል፡፡ ዶክተሩ ቀጥታ ይህንን ሲሉ በተዘዋዋሪ ግን አቻቸው ካልሆኑ መደዴዎች የገጠሙ መሆናቸውን ክፉኛ እንደጸጸታቸው መግለጻቸው ነው፡፡

መሬቱ ይቅለላቸውና (እሱም ተቸብችቦ ካልጠበቃቸው) የብርቱካን አቢዮትን የፍራፍሬና የቅጠላቅጠል እያሉ ሲያስቁበት የነበረው የአመጽ ዓይነት አገራቸው ላይ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም. ድንገት ሲግም የደነገጠና የተቆሳቆለ ገጻቸውን በቴሌቪዥን መስኮት ይዘው በመቅረብ ‹‹ማርሻል ሎው›› ካወጁና ከ70 ሽህ በላይ የከተማዋን ጤነኛና በሽተኛ ነዋሪ ሁሉ ሳይለይ በሌሊት በር እየተሰበረ እንዲታፈስ ካደረጉ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ በአልሞ ተኳሾቻቸው ጥይት እንዲረግፉ ካደረጉ አስር ዓመት በኋላ አሁንም ማርሻል ሎው ታኅሣሥ 5 ቀን 2008 ዓ.ም. ማታ በዚያው የቴሌቪዥን መስኮት አላንቀላፋውም ሲል ነግሮናል፡፡ ‹‹ማርሻል ሎው›› እንደ አገራችን የከፋው ድርቅ በየዐሥር ዓመቱ እየተከሰተ ነው፡፡

አፍ እንጂ ጆሮ የለውም የሚባለው ኢሕአዴግ ከድፍረቱ የተነሳ አምስት ብሔሮችን ቋንቋ በአንድ ላይ ጨፍልቆ አንድ ቋንቋ ለማውጣት ያደረገው ጥረት ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣባቸው ተዘጋጁ የተባሉ መጽሐፍትን ለእሳት ደርጎ በሽንፈት ድል ሲጠናቀቅ ያልቆጨውና ይቅርታ እንዲጠይቅ ያላስገደደው ድርጅት መሆኑን አሁንም የሕዝቡን ጥያቄ አዳምጦ መልስ ከመስጠት ይልቅ ችግሮቹን ሁሉ ‹‹ጥቂት ጸረ ሰላም ኃይሎች፣ የውስጥና የውጭ ተላላኪዎች›› የሚላቸው ላይ ማላከኩን ቀጥሏል፡፡ ይህ ማላከክ የት ድረስ እንደሚያስጉዘው ከራርመን የምናየው ይሆናል፡፡

## ነጻ አስተያየት



ግዛቸው አበበ

(gizachewabe@gmail.com)

# የኦፌኮ አዲስ ድምጽ!

እንደተለመደው በየአምስት ዓመቱ ብሔራዊ ምርጫ መጣ ሲባል የግሉን መገናኛ ብዙሃን የሚያሞቁትና ወደ ውጭ አገር ወጣ ገባ እያሉ የሚተረማመሱት ተቃዋሚዎች ሳያስቡት ያለ ጊዜው ከጥልቅ እንቅልፋቸው ነቅተዋል:: በድንገት በርግገው የተነሱት ተቃዋሚዎች ዓይናቸውን በደንብ ሳይከፍቱና ምን በመካሄድ ላይ መሆኑን በቅጡ ለማሰብ ጊዜ ሳይገዙ ‹‹ሕገ መንግሥቱ ይከበር!›› እያሉ ሲጮኹ እየሰማን ነው:: በውጭ ያሉ የሐበሻ ሚዲያዎችም ይህንኑ የ‹‹ሕገ መንግሥቱ ይከበር›› ጩኸት ሲያስተጋቡ ተስተውለዋል:: አስገራሚው ነገር ሕገ መንግሥቱ ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ይልቅ ዘራቸውንና ጎሳቸውን ከፍ አድርገው እንዲያዩ የሚያደርግ፣ ኢትዮጵያን የሚያፈራርስ፣ ሕዝቦችን የሚለያይ ነው እያሉ አምርረው ሲቃወሙ የነበሩ ወገኖች ሁሉ ‹‹ሕገ መንግሥቱ ይከበር!›› እያሉ በመጯጯህ ላይ መሆናቸው ነው::

አንዳንድ መገናኛ ብዙሃን ይህ ጭፍን ግርግር አስመልክተው ‹‹ሆድና ጀርባ የነበሩት የአማራና የኦሮሞ ሊሂቃንን በአንድነት ያቆመ አመጽ›› ሲሉ ለመወሸከት አብቅቷቸዋል:: በአመጹ ዋዜማ ላይ የተነበበ አንድ ጋዜጣም ‹‹የሕዳሴ አብዮት›› በሚል ተረት ሥር ‹‹ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ ያስቆጠረው የጸረ-ወያኔ ትግል ዛሬ ድል በራፍ ላይ መድረሱ በግላጭ የሚታይ እውነታ ሆኗል... ትግሉ... ከሑመራ እስከ ባሌ፣ ከሽሬ እስከ ጎዴ ተቀጣጥሏል...›› ብሏል:: ይህ ጋዜጣ ኦነግና ኦብነግ፣ ግንቦት ሰባትና ሌሎች ግንባሮች ተጣምረው ጸረ-ወያኔ ትግል በማካሄድ ላይ ያሉ የሚያስመስል ወሬ አናፍሷል::

ሐቁ ግን ሌላ ነው:: የኦፌኮው አቶ በቀለ ነጋ፣ የሰማያዊው አቶ ይልቃል ጌትነት፣ አቶ ልደቱ አያሌው፣ የኦነጉ አቶ ቃሲም አባነሻ፣ የተገነጠለው የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አመራሮች እና ሌሎች ተቃዋሚ ፖለቲከኞች በተለያዩ በሚዲያዎች ላይ በቀረቡበት ጊዜ ከተናገሩት በመነሳት አመጹ በሕወሓት መራሹን መንግሥት ላይ የተቃጣ ነው በማለት የተመሳሰለ ድምጽ ቢያሰሙም የወቅቱን ችግር በሚመለከት ልዩነት እንደታየባቸው መገንዘብ ይቻላል::

ገዥው ቡድን ከአገሪቱ ህልውና ይልቅ ሥልጣኑ የሚያሳስበው መሆኑ ይታወቃል:: ተቃዋሚዎቹም ‹‹አመጾች ሁሉ ወደ ሥልጣን ያመራሉ›› የሚል አመለካከት ያላቸው መሆኑ እየታየ ነው:: ከኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ይልቅ ለሥልጣን የቋመጡ መሆናቸውን አንድ እንዳይሆኑ እንዳደረጋቸው ሁሉ ለኢትዮጵያ አንድነት ብቻ ሳይሆን ለህልውናዋም ጸር እየሆነ ነው:: ተቃዋሚዎች ውሳኔ ስጡ ተብለው አብረው ቢቀመጡ ወይም አገሪቱን ተረከቡ ተብለው ቢጋበዙ እርስ በርሳቸው ሊናቆሩ እንደሚችሉ የሚያሳብቅ አቋም እንደታየባቸው መካድ አይቻልም::

አቶ በቀለ ነጋና አሜሪካ የመሸገው አቶ ጃዋር መሐመድ ስለኦሮሚያው አመጽ ተመሳሳይ ነገሮችን ሲናገሩ ሰምተናል:: አቶ በቀለ ነጋ ይኸ ሰው በዘር ልዩነት ቆንጨራ ያነሳ እንደነበረ የተናገረው ነገር ነገ ደግሞ በሃይማኖት ልዩነትና በዘር ጥራት (ንጹሕ ኦሮሞና ክልስ ኦሮሞ ብሎ) ሊያነሳው የሚችል መሆኑን መጠራጠር የለባቸውም:: በኦሮሚያ ክልል የተቀሰቀሰው ተቃውሞ በአንዳንድ አካባቢዎች ኦሮሞዎች ሰበብ ተፈጥሮ የተጠቁበት መሆኑንም ልብ ማለት ይግባል::

በየቦታው የሚታየው ተቃውሞ በሕወሓት መራሹ ገዥ ቡድን ሥልጣን ላይ ያነጣጠረ ተደርጎ በብዙ ወገኖች ቢገለጽም ጉዳዩ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የተደቀነውን አደጋ የሚያመላክት መሆኑን ልብ ማለትም ያስፈልጋል:: በሌላ በኩል በአገር ቤትና በውጭ አገር በተበጣጠሰ ሁኔታ በጎበዝ አለቃ ተቧድኖ የሚፍገመገም የሚመስለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ እርባና ቢስ መሆኑ የተጋለጠበት ሁኔታም ተፈጥሯል:: ወቅቱና ሁኔታው ተቃዋሚዎች የሚቧርቁበት ወይም ጥቅማ-ጥቅም ጠብ ይልልናል ብለው የሚፈነጥዙበት ጊዜ አይመስለንም:: ይልቁንም ኅብረት ፈጥረው መቆም ባለመቻላቸው ማዘንና ማፈር እንዳለባቸው የሚያስጠነቅቅ ጊዜ ነው::

ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት ሰባት፣ ኦፌኮ፣ ሰማያዊ፣ ኢዴፓ፣ መኢአድ ወዘተ. ወያኔ በሌለበት በወንበሯ ዙሪያ ቢገናኙ ምን ይፈጠራል ብሎ በመጠየቅ የአዘቅቱን ጥልቀት መገመት ይቻላል:: በኤርትራ በረሐ ውስጥ ሻዕቢያ፣ ጀብሐ፣ የነጻነት ሰልፍ፣ የኦቤል ቡድን፣ አልዋሕዳ፣ የሌሊት ወፍ እንቅስቃሴ ወዘተ. የተባሉ ቡድኖች በነበሩባቸው ጊዜያት ሳህልና ባርካ ውስጥ ምን ተከናወነ ብሎ ዞር ብሎ ማየት ይገባል:: ችግራቸውን የፈቱት በመጠፋፋት ነው::

ካልጠነከሩም ከጣራ በላይ እያወሩ መክረም:: ለሥልጣን ቢቃረቡ አቶ ሌንጮና ዶ/ር ብርሃኑ ብቻ ሳይሆኑ አቶ ግርማ ሰይፉና አቶ ይልቃልም ከመናቆር አይቦዝኑም:: አሁን አብረው እንዲቆሙ ያላደረጋቸው አስተሳሰብ ከዙፋኑ ጥግ ሲደርሱ ለቡጢ እንጂ ለሰላማዊ ውይይት አይጋብዛቸውም:: አይቀሬ እውነታን በደመ ነፍሳዊ መወራጨት መሸፋፈን፣ ችግሩንም በስሜታዊነት እንዳይኖር ማድረግ አይቻልም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባበሩ ወይም ተስባበሩ ሲል ቢከርምም ተቃዋሚዎች በየሰበቡ መሰባበርን መርጠዋል:: በአሁኑ ወቅት ስብርብሩ የወጣው ተቃውሞ አሳፋሪ አቋም ይዞ እየታየ ነው::

በመሠረቱ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ፣ በአማራና በትግራይ ወዘተ. መካከል መሬት የመከለልንና ክልል የማስፋፋት እንቅስቃሴ ተከትሎ የተነሳው ግጭት ሕገ መንግሥቱ ያስከተለው ችግር መሆኑ ግልጽ ነው:: ችግሩ ከሥረ መሠረቱ የሚቀረፈው ሕገ መንግሥቱን ለኢትዮጵያ በሚበጅ መልኩ በማሻሻል ነው:: በሌላ በኩል መሬት የመከለልንና ክልል የማስፋፋት እንቅስቃሴ ስጋት ላይ የጣላቸውን ወገኖች ሐሳብም ሆነ ተቃውሞ ማቃለል ወይም በማስፈራራት ለማፈን መሞከሩ የትም የማያደርስ አይደለም:: ይህ ዘዴ ሊያመጣ የሚችለው ጊዜያዊና አስመሳይ መፍትሔን ብቻ ነው::

የተነሳው የሕዝብ ቅሬታና ተቃውሞ ትክክለኛ መሆኑን የሚያሳየን ሕወሓት አሸናፊ እንደሆነ የተከናነወነው የትግራይ መስፋፋት ያስከተለው ችግር ነው:: ከጎንደርና ከወሎ ተቆርሰው ወደ ትግራይ በተካተቱት አካባቢዎች የሚኖሩ አማሮች ማንነታቸው ተጨፍልቆ፣ በቋንቋቸው የመማርና የመገልገል መብት ተነፍገው፣ የመብት ጥያቄ ሲያቀርቡም ለእንግልትና ለሰቆቃ እየተዳረጉ ኖረዋል:: በአማራ ክልል ውስጥ በአዊ፣ ለኦሮሞ፣ ለአርጎባ ብሔረሰቦች የተሰጡት ሁለገብ መብቶች ወደ ትግራይ ክልል በተጠቃለሉ መሬቶች ለሚኖሩ ሕዝቦች አልተሰጡም:: እነዚህ ሰዎች ያለማንነታቸ ትግሬዎች እንዲሆኑ ወይም አካባቢውን ለቅቀው እንዲወጡ ነው የተፈረደባቸው:: ለነገሩ ኩናማዎችና ኢሮቦችም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይተው አንዳንድ መብቶቻቸው መከበር የጀመሩት በቅርቡ ነው:: እነሱም ትግሬ እንዲሆኑ ጫና እየተደረገባቸው ነው የኖሩት::

ከዚህ አንጻር የአዲስ አበባ ወደ ኦሮሚያ መስፋፋት፣ የአማራና ትግራይ ችግር ወዘተ. ማንነትን ከማጥፋት ጋር ተመሳስሎ ቅሬታ መቀስቀሱ የሚጠበቅ ነው:: ግልጽነት የማያውቀው ገዥ ቡድን እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ ከዓመት በላይ ለሚሆን ጊዜ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ብዙ ነገሮችን ሲያስደምጡ ዝምታን መምረጡ ያበጠው ቅሬታ እንዲፈነዳ አድርጓል::

አሁንም የገዥው ቡድን ዋና ትኩረት የሚዲያ ላይ ድራማ መሥራት ሆኗል:: በአንድ በኩል ለማስፈራራት በሌላ በኩል የሕዝብን የልብ ትርታ አዳማጭ መስሎ ለመታየት ይጠቅማል ያለውን ድራማ በሚዲያዎቹ ላይ በመስራት ላይ ነው:: ገዥው ቡድን ጋዜጠኞቹን በማሰማራት ጎዳና ላይ የተገኙ የሚሏቸውን ሰዎች በማናገርና ራሱ ገዥው በድን በጠራው ስብስባ ላይ የተገኙ ሰዎች የተናገሩትን የተመረጠ ወሬ በማስተጋባት ነገሩን ለማድበስበስ እየሞከረ ነው:: ገዥው ቡድን ይኸ ዘላቂ መፍትሔ እንደማይሆን ማወቅ ይገባዋል::

2007 ዓ.ም. ላይ አንድነት ፓርቲ በገጠመው ችግር ብቻ ሳይሆን አውራዎቹ ባሳዩት የማን አለብኝነትና ማስተዋል ማጣት በአንጄ ሲፈራርስና አውራዎቹን ‹‹ፖለቲካዊ የቤት እመቤት›› አድርጓቸው ሲያርፍ አይተናል

60ሺህ ታጋዮች ተሰውተውለት መጣ የታባለው ዴሞክራሲ ራበኝ፣ ጠማኝ ብሎ ለመናገር እንኳ መብት እንዳልሰጠ በቅርቡ ታይቷል:: የተራቡ ወገኖች ከውጭ ሚዲያዎች ጋር ቃለ ምልልስ አድርገው ስማቸው እንዲደበቅላቸው፣ ማንነታቸው ከታወቀ ለችግር እንደሚዳረጉ ሲናገሩ ሰምተናል:: የረኀብተኞችን ድምጽ የሚያሰማ የአገር ውስጥ ሚዲያ በታጣበት ጊዜ የገዥው ቡድን ሚዲያዎች በሚሊዮኖች የሚቆጠረውን ወገናቸውን ችግር ችላ ብለው ስለ ጆሴ ሞሪንሆና ስለ ቸልሲ ውጤት ማጣት ከጣራ በላይ እየጮኹ ጭንቀታቸውን ያራግቡ ነበር:: ምሁርና ተመራማሪ ተብየዎች በገዥው ቡድን ሚዲያ ላይ እየቀረቡ ሐሳብን በነጻነት መግለጽ በሚቻልበት ጊዜ ላይ መሆናችንን ደጋግመው የነገሩንን እንርሳውና ገዥው ቡድን ሆነ ሚዲያዎቹ አሳምሮ የሚያውቃቸውን ሕዝብ ማታለል እንደማይችሉ ሊያውቁት ይገባል::

ወደ ኦፌኮ ስንመለስ የቀድሞው የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) የአሁኑ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ሲነጻጸር ትልቅና ጠንካራ ፓርቲ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵዊነትን በሚመለከት የጠራ አቋም ያለው ፓርቲ መሆኑ የታወቀ ነው::

ኦፌኮ የኢትዮጵያን ህልውና በሚመለከት ግልጽ አቋም ያለው ድርጅት ነው:: አንዳንድ ፓርቲዎች በአገር ቤት ካሉ የግል ጋዜጦች (መጽሔቶች)፣ ቪኦኤንና ኢሳትን ከመሳሰሉ በውጭ ካሉ ሚዲያዎች ጋር በእከክልኝ ልከክልህ መወዳደስና አንዱ የሌላውን ስህተትን ያላዩ መስሎ በማተላለፍ ስለሚተሻሹ በወሬ ብዛት ትልቅ መስለው ቢታዩም ይህ ትልቅነት የውሸትና ከፕላስቲክ ፊኛ የተሠራ ትልቅ ዝሆን መስሎ ከመታየት ያልዘለለ መሆኑን ከአንድነት ፓርቲ አነሳስና አወዳደቅ መረዳት ይቻላል::

2007 ዓ.ም. ላይ አንድነት ፓርቲ በገጠመው ችግር ብቻ ሳይሆን አውራዎቹ ባሳዩት የማን አለብኝነትና ማስተዋል ማጣት በአንጄ ሲፈራርስና አውራዎቹን ‹‹ፖለቲካዊ የቤት እመቤት›› አድርጓቸው ሲያርፍ አይተናል:: ኦብኮ-ኦፌኮ ግን ምርጫ 1997ትን ተከትሎ የከፋ ችግር ሲጥመው በጊዜው ከነበሩት 120ሺህ አባላቱ ውስጥ ከሃያ የማይበልጡት ብቻ ከድተውት፣ ቤት ንብረቱንና ኦብኮ የሚል ስሙን ቢያጣም ኦፌኮ ሆኖ እስከ አሁኑ ጊዜ ለመዝለቅ የቻለ ድርጅት ነው::

የኦብኮ-ኦፌኮ መሥራችና የረዥም ጊዜ መሪ ዶ/ር መረራ ጉዲና ኦሮሚያ ኢትዮጵያዊ አይደለችም በሚሉ የኦሮሞ ፖለቲከኞች ዳግማዊ ጎበና እየተባሉ ሲጠሩ ኦሮሞ የሚል የዘር ስም የተለጠፈለት ፓርቲ ለምን ይመሠርታሉ በማለት ቅር ወገኖች ደግሞ ጠባብ ብለው ዘልፈዋቸዋል:: ቢሆንም ዶ/ር መረራ ጉዲና ሁልጊዜም ኢትዮጵያዊ ሆነው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው የሚያምኑበትን ትግል ከፊት ለፊት ሆነው እየመሩ (በተግባር እየተሳተፉ) የሚኖሩበትን መንገድ መርጠው በመታገል ላይ ናቸው:: ዶ/ር መረራ እንደ ሌሎቹ ፖለቲከኞች ዜግነታቸውን ቀይረው በድልላና በማስመሰል የሚሰበስቡ መሪ አይደሉም:: ለገዥ ቡድንም ይሁን ለስደተኛው ሚዲያ፣ ለግል ሚዲያዎች ይሁን ሐበሾችን ለቀጠሩ የፈረንጅ ሚዲያዎች አካፋውን አካፋ ብለው ለመናገር ድፍረት ያላቸውና የማይጎናበሱ በሳል ሰው ናቸው::

ዶ/ር መረራ የኢትዮጵያ የተቃውሞ ኃይል ወደ አንድነት ለመምጣት ያልቻለበትንና ጠንካራ ክንድ ፈጥሮ ገዥው ቡድን ለመፋለም ብቁ ያልሆነበትን ምክንያት ለማሳየት ‹‹ኢትዮጵያ የምትባል አገር አያሳየን›› በሚሉና ‹‹የኢትዮጵያዊነት ምስክር ወረቀት ሰጭዎች እኛ ነን›› በሚሉ ወገኖች መካከል መፋጠጥ መኖሩን፣ የሁለቱም ጎራ ሰዎች ግማሽ መንገድ ተጉዘው ወደ መካከለኛው አቋም ለመምጣት ትሕትና የጎደላቸው መሆኑን ይገልጻሉ:: በነዚህ ሁለት ጎራዎች ውስጥ በኢትዮጵያዊነት የማያምኑ እና በኢትዮጵያዊነታቸው ቢያምኑም ዜግነታቸውን አክብረው የመያዝ ችግር ያለባቸው ሰዎች በብዛት መኖራቸው መፋጠጡን የተካረረና አውዳሚ አድርጎታል::

ኦፌኮ በኢትዮጵያ ህልውና ላይ የማይደራደር ድርጅት ቢሆንም በቅርቡ ኦሮሚያ ውስጥ የተቀሰቀሰውን አመጽ ተከትሎ ግን ፓርቲው ኦሮሚያን ለመገንጠል ይታገላል የሚል ሐሳብ እንዲሰነዘር በር ከፍቷል:: ይህ አባባል በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮና በሌሎች መገናኛ ብዙሃን ላይም ሲሰነዘር ተሰምቷል:: ይኸ የሆነው የወቅቱ የኦፌኮ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ በቀለ ነጋ አዲስ ዓይነት አነጋገር በመናገራቸው ነው:: አቶ በቀለ ነጋ ማንነትን ስለመጠበቅ ሲናገሩ ከሌላው ጋር አብሮ መኖርን ግምት ውስጥ የማስገባት ችግር በግልጽ ታይቶባቸዋል:: በአመጹ ስተታሰሩትና ስለ ተገደሉት የኦሮሞ ተወላጆች ሲያወሱ ኦሮሚያ ውስጥ በደል ስለተጸመባቸው አማሮችና ሌሎች ሕዝቦች ምንም ደንታ አልነበራቸውም:: አዲስ አበባ ወይም ኢትዮጵያ ስለምትቀጠቀምበት መሬት፣ ውኃ፣ ማዕድን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ወዘተ. ሲያወሱ ‹‹የኦሮሚያ ሀብት እኮ ነው›› ሲሉ ተደምጠዋል:: አቶ በቀለ ነጋ ያለ ጥንቃቄ ስለሚናገሩ ንግግራቸው የኦነግን ወይም የነ ጆሐር መሐመድን መስሎ ይሰማ ነበር::

አቶ በቀለ ነጋ ‹‹ሚኒልክ ኦሮሚያን ወረረ›› የሚለውን መንፈስ ተከትለው ስለሚናገሩ የኦሮሞን ከደቡብ ጫፍ ተነሰቶ ወደ ሲዳማው፣ ወደ ወላይታው፣ ወደ ጉራጌው፣ ወደ አማራው፣ ወደ ትግሬው፣ ወደ አኝዋኩ ምድር ወዘተ. መስፋፋቱንና አብሮ በመኖር የመዋሐዱን ታሪክ ቆም ብለው ለማስታዎስ አልሞከሩም:: የአቶ በቀለ ሌላው አስተያየት ሕዝብ ኦሮሞ ሲስፋፋ ወይም ኦሮሞ ሲሰደድ የያዘብኛን መሬት ይልቀቅ ብሎ እንዲጠይቅ የሚያነሳሳ አፍራሽ አባባል ነው::

የአቶ በቀለ ነጋ አነጋገር የጉራጌ ጭፍራ የኦሮሞ ነው የሚሉትን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብቅ ብቅ ያሉ አንዳንድ የኦሮምኛ ዘፋኞች አስተሳሰብ የወረሰ ነው:: ይህ ጭፈራ ኦሮሞዎች ወደ መሐል አገር ሲስፋፉ ከጉራጌው ምድር ጋር አብረው የተጋሩትና አንድ ሕዝብ ሆነው የኖሩበት፣ ኢትዮጵያዊነት የተገመደበትን አንዱን ፈትል የሚያሳይ ነው እንጂ ሌላ አይደለም:: ለሌላው አካባቢም እንደዚያው:: የአቶ በቀለ አነጋገር በኦሮሚያ በኩል የውጭ ጠላት ቢመጣ የተወረረው የኦሮሞ ምድርና ሀብት ነውና ኦሮሞ ብቻ ነው የሚዋጋው ብለው ሌላውን ሕዝብ የማግለል አስተሳሰብ ይኖራቸው ይሆን?

## ዘገባ

ሳምሶን ኃይሌ

# የወልቃይት ጠገዴ መሬቱን እንጂ...!



**ሱዳን ድንበር ከገቡ በኋላ በጥይት ተደብድበው ይገደላሉ። ትልልቅ ከተማዎች አደባባይ ላይ ይሰቀላሉ። ከተማ አደባባይ ላይ የሚሰቀሉትን በተመለከተ ሱዳኖቹ የሚሉት “ሐበሻ ራሱን አጠፋ” ነው**

ከአንድ ሳምንት በፊት የወልቃይት አማሮች የማንነት ጥያቄ አስተባባሪዎቹ ሊያገኙኝ እንደሚፈልጉ ገልጸውልኝ በቀጠሯችን መሠረት ተገናኘን:: ለኢፌዴሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት ያስገቡትን የማንነት ጥያቄ ማመልከቻ እንዲሁም 116 የት እንደደረሱ የማይታወቁ ወገኖቻቸውን ስም ዝርዝር የያዘ ሰነድ ፎቶ ኮፒ ሰጡኝ:: ሰነዱ በራሱ ገላጭ ቢሆንም የአካባቢውን ተወላጆች መሠረታዊ ጥያቄ በሚገባ ለመረዳት በዕድሜና በተመክሮ በሳል የሆኑ ሰዎችን ማነጋገሩ የተሻለ መስሎ ስለተሰማኝ ሐሳቤን ገለጽኩላቸው:: እነሱም ጥያቄየን ተቀብለው ከአንድ የ70 ዓመት አዛውንት ጋር አገናኙኝ::

ያገኘዋኋቸው አባት ታሪክን ጠንቅቀው የሚያውቁ የቤተ ክህነት ሊቅ ናቸው:: እኚህ አዛውንት ስለወልቃት ጠገዴ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵና ሱዳን ጉዳይ ላይ ያላቸው ዕውቀት ከፍተኛ ነው:: ይህ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው የዕድሜ ባለጸጋው የወልቃይት ተወላጅ የነገሩን ነው::

የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ወንዱም ሴቱም ጅግና ነው:: በጣሊያን ወረራ ዘመን እናቶቻችን ልጆቻቸውንና ባሎቻቸውን አልጋ ሥር ጠመንጃ አቀባብለው እንዲደበቁ ያደርጋሉ:: እነርሱ ደግሞ በርበሬ (ሚጥሚጣ) ድቁሱን በውኃ በጥብጠው ያስቀምጣሉ:: ከዚያም የጠላት ወታደር በውበታቸው ማርከው ወደ ቤት ያስገቡታል:: የወልቃይቷን ሴት ውበት ዓይቶ በስስት የሚገባው ፈረንጅ ፊትና ዓይን ላይ ያን የተበጠበጠ በርበሬ ይደፉበታል:: ያ ወታደር ሲደናበር አልጋ ሥር የተደበቀው ባለነፍጥ አናቱን ብሎ እየሸለለ የጠላትን ትጥቅ ቀምቶ ጫካ ይገባል::

ኢሕአፓና ሕወሓት ታኅሣሥ 21 ቀን 1972 ዓ.ም. በወልቃይት ደጀና ከተባለ ቦታ ላይ ጦርነት ገጠሙ:: ‹‹ግንብ›› የተባለ ጎድጓዳ ቦታ አለ:: ግንብ ውስጥ ሰው ቢጮህ ማንም አይደርስለትም:: ጥይት ቢተኮስም ርቀት ቦታ አይሰማም:: ደጀና ላይ ሲዋጉ የነበሩ የኢሕአፓ ወታደሮች ሁሉ ግንብ ውስጥ ዶግ አመድ ሆኑ:: አስከሬን ቀባሪ አጥቶ ለአሞራ ቀለብ ሆነ:: የሰው ልጅ ለካ ያን ያክል ስብ ይሸከማል? ስቡ ቀልጦ የሚፈሰው መሬቱን ሁሉ አጥቁሮት ነበር:: የጥይት ድምጽ አፍኖ የሚይዘው ግንብ አስከሬኖቹ የሚተፉትን መጥፎ ጠረን ግን አፍኖ መያዝ ተሳነው:: ድፍን ወልቃይትን በመጥፎ ጠረን አሰከረው::

ከሞት ያመለጡት የኢሕአፓ ሠራዊት አባላት ወደ ሱዳን ተሰደዱ:: የወልቃይት ጠገዴ ጣዕር ከዚህ ጊዜ ይጀምራል:: ሕወሓቶች ወልቃይት ጠገዴን ዙረው ሲመለከቱ በመሬቱ ለምነት ጎመዡ:: በዚህ ምክንያት መሬቱን ለመውሰድ ሕዝቡን በልዩ ልዩ መንገድ ማሰቃየትና ከአካባቢው ማፈናቀልን ሥራዬ ብለው ተያያዙት:: በዚህ መንገድ ሕወሓት ‹‹ኢሕአፓን አስጠልላችኋል›› በማለት በወልቃይት ሕዝብ ላይ መከራውን አንድ ብሎ ጀመረ:: ያኔ የተጀመረው መከራ አሁንም ይበልጥ ተጠናክሮ ቀጠለ እንጂ አልቆመም:: ኢሕአፓን አስጠግተዋል ያላቸውን አማሮችን ቤትና ንብረት ማቃጠል የጀመረው ሕወሓት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የወልቃይት ወጣቶችን ሰበብ እየፈለገ መግደል ሥራው ሆነ፤ የግፍ አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ተጫነ:: ለዚህ ደግሞ የሱዳን መንግሥት ታላቅ ሚና ተጫውቷል:: አሁንም ቢሆን የሱዳን መንግሥት የጥፋት እጆች አልተሰበሰቡም::

የወልቃይት ጠገዴ አማሮች የተከፈተባቸው ጥቃት ሁለንተናዊና ከብዙ አቅጣጫ ነው:: የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የሥነ ልቦናዊ ጦርነት ሰላባ ናቸው:: በመንግሥት መሥሪያ ቤት ቅድሚያ የሚሰጥ ከመሐል አገር ለሚመጣ የትግራይ ተወላጅ ነው:: የወልቃይት ልጆች ትምህርት በአማርኛ መማር አይችሉም፤ ትምህርት ቤት ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ማውራትም አይችሉም:: ክልክል ነው:: ሕወሓት በዚያ አካባቢ መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከሰላሳ በላይ ለሚሆኑ ዓመታት የኢትዮጵያም ሆነ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ያላወቀ ብዙ በደል ደርሷል:: አያሌ የወልቃይት ተወላጆች ተገድለዋል፤ ተሰደዋል:: ቁጥራቸውን የማናውቀው ልጆቻችን የት እንደወደቁ ሳይታወቅ ደብዛቸው ጠፍቷል::

የሕወሓቶች ግፍ ወልቃይት ጠገዴ አማሮች የተፈጥሮ ስሜታቸውን እንኳ በወዱ እንዳይገልጹ ነው የሚያስገድዷቸው:: የዳንሻ ከተማ ከንቲባ ሕዝቡን ሰብስቦ ‹‹ልጆቻችሁ ስለምን አማርኛ ያወራሉ!›› በማለት በአደባባይ ሕዝቡን ማስፈራራቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው:: አማርኛ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች ‹‹የኢሕአፓ ቅሪቶች›› በመባል ይታወቃሉ:: አማርኛ የሚናገሩ ሰዎች ምንም ዓይነት መብት የላቸውም:: የሕግ አካላት የአማራ ተወላጆችን አያስተናግዱም:: የወልቃይት ተወላጆች ከትግራይ ብሔረሰብ አባላት ጋር ተጋጭተው ወይም ሌላ በደል ደርሶባቸው ለሚመለከተው የፍትሕ አካል ቢያመለክቱ የፍትሕ አካሉ ለትግራዩ እንደሚያዳላ ማንም ያውቃል:: የተለመደ ነው::

ትግርኛ በአግባቡ ባለመናገራቸው በደል የሚደርስባቸው የወልቃይት አማሮች ብዙ ናቸው:: ለናሙና አንድ እናንሳ:: የአካባቢው ሕዝብ ባህሉም ሥነ ልቦናውም ምርጫው አማራነት ነው:: ሕዝቡ ለትግራይና ኤርትራ ቅርብ በመሆኑ እንደሌሎች በአዋሳኝ አካባቢዎች እንደሚኖሩ ሕዝቦች የተለያየ ቋንቋ ይናገራል:: የዚህ ዓይነት ሁኔታ በየትም አካባቢ ያለና ተፈጥሯዊ ነገር ነው:: የድሬዳዋ ሕዝብ ከአማርኛ ሌላ ሶማሊኛም ኦሮምኛም እንደሚናገር ይታወቃል:: ኢትዮጵያውያን በሌሎች የአገራችን ጥአካባቢዎችም እንዲሁ ነው:: የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብም ከአማርኛ ሌላ ትግርኛ ይናገራል:: ዐረብኛ ቋንቋ የሚናገሩም ብዙዎች ናቸው:: ሕዝቡ ትግርኛ ይናገር እንጂ የአካባቢው ትግርኛ የተለየ ነው:: ወደ አማርኛ በእጅጉ ይቀርባል:: የትግራይ ብሔረሰብ አባላት ይህን በሚገባ ያውቃሉ:: በዚህ ምክንያትም ብዙ በደል አለ:: ትምህርት ቤት ሞክሼ የአማርኛ ፊደላትን የሚጽፉ ተማሪዎች ካሉ በጣም ይወገዛሉ:: ለምሳሌ ኀ፣ ሠና ፀ የአማርኛ ፊደላት ናቸው ተብለው ስለሚታሰቡ መምህራን ለፊደላቱ ያላቸው ጥላቻ የበዛ ነው:: እንደሚታወቀው ጉራጌ ዞን ውስጥ ለምሳሌ ለኦሮሚያ ክልል ቅርብ በሆነው ሶዶ ወረዳ ውስጥ ብዙዎች ኦሮምኛ ቋንቋ ይችላሉ:: ኦሮምኛ ስለሚናገሩ ኦሮሞ ናቸው በሚል ወደኦሮሚያ ክልል ለመጠቅለል ጥረት ቢደረግም ሕዝቡ ማንነቱን አሳልፎ አልሰጠም::

መታወቅ ያለበት የብሔረሰቦች መብት ተከብሯል እየተባለ ድቢ በሚመታበት ዘመን የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ያለታሪኩና ፍላጎቱ ወደትግራይ ክልል እንዲጠቃለል የተደረገው በሕወሓት ውሳኔ በመሣሪያ አፈሙዝ ነው:: ሕዝቡ ፈጽሞ አልተጠየቀም፤ ሐሳቡን እንዲገልጽ ዕድልም አልተሰጠውም:: አካባቢው በትግራይ ክልል ሥር እንዲሆን ከተወሰነ ጀምሮ የመብት ጥያቄ የሚያነሱ ልጆቻችንን ስንቀብር ኖረናል:: ጥያቄው ወደፊት እንዳይቀርብና ለአንዴና ፋይሉን ለመጨረሻ ጊዜ ለመዝጋት ሲባል በሺህዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችን በአያት ቅድመ አያቶቻችን ርስት ላይ በማስፈር የትግራይን የበላይነት ለመፍጠር ያልተሞከረ ነገር የለም:: የሕዝባችን በደል ድርብ ድርብርብ ነው የምንልበት ምክንያት በደሉ በባለመሣሪያው ሕወሓት የሚፈጸም በመሆኑ እንደሌሎች ሕዝቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ እስካሁን ጎልቶ ባለመውጣቱ ነው:: ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የተሻለ ሁኔታ ቢኖርም ከደረሰብን በደል ጋር ስናወዳድረው በጣም የሚያሳዝን ነው::

### የሱዳን መንግሥት ከኢትዮጵያ የአጥንት ቲቢ ነው!


የሱዳን መንግሥት እኮ ለአገራችን የአጥንት ቲቪ ነው:: የሱዳን መንግሥት የወልቃይትን አማሮች ከሕወሓት ጋር እንዴት አድርገው እንደፈጇው በሚገባ እናውቃለን:: ከ1972 ጀምሮ ሕወሓቶች አስቀድመው የሚያጠና ሰው ይልካሉ:: ሰላይ መሆኑ ነው:: አስቀድመው የሚመጡት ሰላዮች በራሱ መተማመን ያለውንና ቆይቶም ለሕወሓቶች ተቃውሞ ያነሳል የሚሉትን ወጣት በስም ዝርዝር ይልካል:: ሕወሓቶች ለሱዳኖች ይናገራሉ:: ሱዳኖች መኪና ይዘው ይገባሉ:: ወጣቶቹን ይይዙና ወደ ግዛታቸው ይወስዷዋል:: ‹‹ዛሬ እከሌ ጠፋ! ዛሬ እከሌ በሱዳኖች ተወሰደ!›› ሁልጊዜም የሚሰማ እሮሮ ነው:: ይህ እሮሮ በሕወሓቶች የሽፍትነት ዘመን ብቻም ያቆመ አይደለም:: እስካሁን ድረስ የቀጠለ ደረቅ ሐቅ እንጂ:: ሱዳን ድንበር ከገቡ በኋላ በጥይት ተደብድበው ይገደላሉ:: ትልልቅ ከተማዎች አደባባይ ላይ ይሰቀላሉ:: ከተማ አደባባይ ላይ የሚሰቀሉትን በተመለከተ ሱዳኖቹ የሚሉት ‹‹ሐበሻ ራሱን አጠፋ›› ነው:: ሕወሓቶች ራሳቸው የወልቃይት አማራ ወጣቶችን ጉድጓድ እንዲቆፍር ካደረጉ በኋላ በቆፈሩት ጉድጓድ ይቀብሯቸዋል:: ‹‹የትግሬ እናት ሐዘን ተቀምጣ አንተ ጠግበህ ትበላለህ?›› በማለት ውኃ በቀጠነ ይገድሏቸዋል::

ሕወሓቶች እንዲህ ይላሉ:: መሬቱ እንጂ ሕዝቡ አያስፈልገንም:: የሱዳን ዜጎች ድንበር አካባቢ የሚያገኟቸውን ኢትዮጵያውያን ሳይጠይቁ የማያልፉት ነገር አለ:: ይኸውም ‹‹አማራ ነህ ትግሬ!›› የሚል ነው:: ለሱዳኖች ሰው ማለት ትግሬ ነው:: አማራ የሱዳን ጠላት አድርገው ይቆጥሩታል:: የሱዳን ደህንነቶች የፈለጉትን የወልቃይት ተወላጅ በፈለጉት ጊዜ መጥተው መውሰድ ይችላሉ:: የህወሓትም ደህንነቶች እንዲሁ:: የወልቃይት ተወላጆች ወደ ሱዳንም ቢገቡ እዚህ ቢቀመጡ ያው ነው:: የወልቃይት ተወላጆችን ግፍ ሊያስረዳ የሚችል አንድ ምሳሌ እንጥቀስ:: ቄስ ተገን እንየው የሚባል ካርቱም እስጢፋኖስ የሚያገለግል የወልቃይት አማራ አለ:: ቄስ ተገን በቤተ ክህነት ትምህርት ከዚህ ቀረህ የማይባል ምሁር ነው:: በግዕዝ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በዐረብኛ ደግሞ ከግብጥ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያኖች ይቀድሳል:: ቄስ ተገን ያለውን ለአገሩ ልጆች አካፍሎ ይበላል:: ሕወሓቶች ቄስ መስፍን አገር ውስጥ ላሉ ለሚማሩ ልጆች ገንዘብ እንደሚረዳ ደረሰቡት:: ለተቸገረ ገንዘብ መለገስ የሚያስመሰግን እንጅ የሚያስወቅስ ሆኖ አልነበረም:: ባለፈው መጋቢት ወር 2007 ዓ.ም. ካርቱም የተላከ የወያኔ ደህንነት ይዞት መጣ:: ማዕከላዊ እስከ ጥቅምት 2008 ዓ.ም. ከማንም ከምንም ጋር ሳይገናኝ ጨለማ ቤት አቆይተው ‹‹ለማንም እንዳትናገር›› ብለው ለቀቁት:: ቄስ ተገን ምንም አማራጭ ስላልነበረው አሁን ወደ ካርቱም ተመልሷል::

የወልቃይት ልጃገረዶች በትምህርት ቤት የሚደርስባቸው አበሳም ከፍተኛ ነው:: ሐሙስ ሐሙስ ሴት ተማሪዎች የመምህራንን መኖሪያ ያጸዳሉ የሚባል ያልተጻፈ ሕግ ነበር:: ገና ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሕፃናት የመምህራኖቻቸውን ቤት ለማጽዳት በተራ ሁልጊዜ ሐሙስ ‹እነ ጋሽዬ› ቤት ይሄዳሉ:: ሕፃናቱ በመምህራኖቻቸው ይደፈራሉ:: ያረግዛሉ ይወልዳሉ:: በሕግ ሊያገቡ የታጩ ልጃገረዶች ሁሉ እየተደፈሩ ያገባሉ:: ምክንያቱ ደግሞ አማሮችን ትግራዊ ለማድረግ ብቻ ነው::

የወልቃይት አባቶች ተጨነቁ:: ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ላለመላክ ወሰኑ:: በዚህ ጊዜ ደግሞ ለትምህርት የደረሰ ልጁን እቤት ያስቀመጠ ሰው ይቀጣል የሚል ሕግ መጣባቸው:: ወላጆች አሁን ሌላ አማራጭ ፈለጉ:: ‹በመምህራን› ልጆቻቸው ከመደፈራቸው በፊት በልጅነታቸው መዳር:: መጨነቅ ነው:: ይህም ሌላ ጣጣ አስከተለ:: በሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ‹‹ያለ ዕድሜ ጋብቻ›› በሚል ክስ ይመሰረትባቸዋል:: ያለ ዕድሜያቸው በሚደፍሯቸው መምህራን ላይ ግን ማንም ምንም አይልም:: ይህ ሁሉ ችግር የሚደራረብባቸው ወልቃይቴዎች ያላቸው አማራጭ ሁለት ብቻ ነው:: አንደኛው ልጆቻቸውን ወደ ጎንደርና ሌሎች አካባቢዎች ወስዶ ማስተማር ሲሆን ሁለተኛው ግን የመምህሮቹን ‹‹ዲቃላ›› ማሳደግ::

መታወቅ ያለበት አንድ መሠረታዊ ነገር አለ:: የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ጥያቄ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ አይደለም:: ይህ ማለት ሕዝቡ የመልካም አስተዳደር ችግር የለበትም ማለት አይደለም:: በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች እንደሚታየው በእኛ አካባቢም የመልካም አስተዳደር ችግረ አለ:: የእኛ ዐቢይ እና የሕወሓት ሰዎች የቱንም ያህል ቢገድሉንና ቢያሳድዱን የማንተኛለት፤ እኛ መፈጸም ባንችል ጉዳዩን ለልጅ ልጆቻችን የምናወርሰው ጥያቄ የማንነታችን ጉዳይ ነው:: አማሮች ነን:: ትግራይ አይደለንም:: የደረሰብንና እየደረሰብን ያለውን ያልተነገረለት በደል ኢትዮጵያውያንና የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲገነዘብልን እንፈልጋለን::



ማስታወሻ

ነብዩ ሲራክ

# የዲፕሎማሲያችን ክሽፈት

የታኅሣሥ ወር ከገባ ወዲህ የጅዳና የቀረው ሳውዲ ዐረቢያ የሚያቃጥል የበረሐ ሐሩር በረድ ማለት ይዟል። የገና ጀንበር በጊዜ ከመግባቷ ሌሊቱም አጭር መሆኑን ያስታዎስኩት ዘንድሮ ነው። ታኅሣሥ 19 ቀን 2008 ዓ.ም. ማለዳ ‹‹የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዲሱን የውጭ አገራት የሥራ ስምሪት ዐዋጅ አጸደቀ›› በሚል የተሰራጨው መረጃ እንዳበገነኝ አጭሩ ሌሊት ተገፋና ማለዳው ከተፍ አለ። ታኅሣሥ 19 ቀን 2008 ዓ.ም. ማምሻውን የሳውዲ ሜትሮሎጅ ጅዳና አካባቢው ከበድ ያለ ዝናብ ስለሚጥል ትምህርት ቤት የመዘጋቱ መረጃ ደርሶኝ ነበርና ተፍ ተፍ ብየ ከእንቅልፍ ተነሰቸ በመስኮት ሰማዩን አየሁት። ደመና አለ፤ ዝናብም ያካፋ ይዟል ... ማለዳ የጀመረው ካፊያ ግን ወዲያው አቆመና በነፋሻ አየር ተተካ፤ እንዲህ እያለም ሳምንቱ ተገፋ።

ያ ቃጠሎ ሙቀት አልፎ በቅዝቃዛ አየር ተንፈስ ማለታችንን ብወደውም የዝናቡ ኃይል እያየለ ተፋሰስ ያልተሠራላትን የዐረቦች ቅምጥል ጅዳን ከማመስ አልፎ የሰው ሕይወት ቀጥፎና ንብረት አውድሞ ስለማውቀው ቅዝቃዜውን እንጂ ሰበበኛውን ዶፍ ዝናብ አልወደውም። ባንዱ ማለዳ እንደለመድኩት ማልጀ ተነስቸ ከቤቴ ሳሎን ባንዱ ወንበር ላይ ቁጭ ብየ በመስኮት የሚካፋውን ዝናብ በቆረጣ እያየሁ የሳውዲ ጋዜጦችን የማለዳ ዜና መቃኘት ያዝኩ። ዐረብ ኒውስ ጋዜጣ የሲሪላንካ መንግሥት ሳውዲ ውስጥ ሞት የተፈረደባትን ዜጋቸውን ሕይወት ተከራክረው ማትረፋቸውን የሚያትተው ዝርዝር መረጃ ይዞ ተመለከትኩ። ቀልቤን ጨምድዶ ያዘውና ሙሉውን ካነበብኩት። ብዙም ሳልቆይ በቁጭት እየደበንኩ ከቀናት በፊት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቀውን የውጭ አገራት የሥራ ስምሪት ዐዋጅን አስታዎስኩ። በዚህ ዙሪያ አዲስ መረጃ ባልጠብቅም ያነበብኩት የሲሪላንካ መንግሥትና ዲፕሎማቶቹ የመብት ጥበቃ ትጋት ወንዝ ከማያሻግሩት የእኛ አገር ዲፕሎማቶች ጋር እያገናኘሁ ‹‹ምን ብንረገም ነው ለእኛ መብት አስከባሪ ያጣነው? ምንስ ብናጠፋ ነው ተቆርቋሪ መንግሥት ያጣነው?›› ስል ራሴን በራሴ ጠይቄ አጉተመተምኩ። ሳውዲ ዐረቢያ ሪያድ ውስጥ የኢትዮጵያ ኢምባሲ፣ በጅዳ ቆንስልና በቀሩት ዐረብ አገራት ያሉት የዲፕሎማቲክ መሥሪያ ቤቶች ክህሎት ባላቸው በቂ የሰው ኃይል ሳይደራጁ በአዲሱ ስምምነት ወደ ዐረብ አገራት የሚመጡት ዜጎች ፈታኝ ጊዜያት ከፊቴ ድቅን አለብኝ። ሕጉ ጸድቆ ወደ ተግባር ሲገባም የሚመጡትን በሽዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞችን ቀርቶ በቆየው ነዋሪ ላይ የመብት ገፈፋ ሲፈጸምም ሆነ በተላያየ ወንጀል ስንወነጀልና ስንከሰስ ጠያቂ ስለሌለን ዜጎች ጥቂት ማሳያ የሚሆን መረጃ ከማስታዎሻየ መፈታተሽ ጀመርኩ። መረጃውን አላጣሁም። የሩቁን ሳይሆን የቀረበውን ጉዳይ እያሳየሁ ስለመብታችን ስለ ማይተጉ ዲፕሎማቶቻችን ከሌሎች አገራት የዜጎች ጋር በንጽጽር የሚሆን ሁለት ሦስት ጉዳዮችን ላነሳ ወደድኩ። በአንጻሩ ባሳለፍናቸው ጥቂት ወራት በታዋቂ የሳውዲ ዐረቢያ ጋዜጦች የወጡ መረጃዎችን የሌላ አገር ዲፕሎማቶች ሳውዲ ዐረቢያ ላይ ለተገፉት ሳይሆን የሳውዲን ሕግ መጣሳቸው ተረጋግጦ የተፈረደባቸውን ዜጎቻቸውን መብት ለማስከበር ስለሚሄዱት ርቀት ያለው መብት ማስከበር ሁለት ጥሩ ማሳያዎችን ላሳያችሁ ፈቅጃለሁ።

## ሲሪላንካዋ ከሞት ቅጣት ሲታደጓት

ባሳለፍነው ሳምንት የወጣው ዐረብ ኒውስ በፊት ገጹ ካቀረበው መረጃ መካከል የሲሪላንካ መንግሥት ሳውዲ ዐረቢያ ውስጥ ሞት የተፈረደባትን ዜጋቸውን ሕይወት ተከራክረው ማትረፋቸውን በዝርዝር አትቷል። በሁነኛ የአገሯ ዲፕሎማቶች ከሞት ብይኑ የተረፈችው ስሟ በአደባባይ ያልተገለጸው ሲሪላንካዊት እመቤት የ45 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ የቤት ሠራተኛ ስትሆን ወደ ሳውዲ ዐረቢያ በኮንትራት ሥራ መጥታ በአንድ የሳውዲ ቤተሰብ ተደፍራ እንደነበር ተጠቁሟል። በሳውዲ ዐረቢያ መዲና ሪያድ የሚገኙት የሲሪላንካ ዲፕሎማቶችና በሲሪካንላካ መዲና ኮሎምቦ የውጭ ጉዳይ ኃላፊዎች ዜጋቸው ሳውዲ ዐረቢያ ውስጥ በዝሙት ተወንጅላ ከተፈረደባት የሞት ፍርድ በአጭር እስር እንዲተካ ማድረጋቸውን ባሳልፍነው ሳምንት በሰጧቸው መግለጫዎች አስታውቀዋል። ሐይሻ ዲ ሲልቫ (Harsha de Silva) የተባሉት የሲሪላንካ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በዋና ከተማዋ ኮሎምቦ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ የሁለት ልጆች እናት እንደሆነች የተገለጸቸው ፍርደኛ ባሳለፍነው ነሐሴ ወር 2015 የተያዘችው በዝሙት መሆኑን ጠቁመው በድንጋይ ተወግራ እንድትገደል ተፈርዶባት ነበር። የብይኑ መረጃ ይፋ እንደሆነ ከዜጋቸው ጎን ሆነው በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ በማቅረብ በማማከርና ጠበቃ በማቆም የተወሰነውን በድንጋይ ተወቅሮ የመገደል ብይን ተከራክረው ወደ አነስተኛ እስር ማስቀየራቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ሐይሻ ዲ ሲልቫ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ በኩራት መናገራቸው በሮይተር ዘገባ ላይ ሰፍሯል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የሞት ፍርዱን በማሻር ስለተሠራው አኩሪ የዜጋን መብት የማስጠበቅ ሥራ አስመልክቶ ለዐረብ ኒውስ መግለጫ የሰጡት የሲሪላንካ አምባሳደር አዚም ታሲም በበኩላቸው በዜጋቸው ላይ የተላለፈው የሞት ብይን ወደ እስር ያስቀየሩት በይቅርታ ልመና ሳይሆን በሕጉ መሠረት ጠበቃ ቀጥረው ባሳለጡት ክርክርና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሆኑን ጠቁመዋል።

## ብሪታንያዊውን ከ350 ጅራፍ ግርፊያና እስራት ሲታደጉት

ካርል አንደሪ (Karl Andree) ላለፉት 25 ዓመታት ሳውዲ ዐረቢያ ውስጥ በአንድ ኩባንያ ተቀጥሮ የኖረ ብሪታንያዊ የ74 ዓመት አዛውንት ነው። ካርል ከበርካታ ወራት በፊት መንገድ ላይ መኪና ሲያሽከረክር ፍተሻ አጋጥሞት በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ በባህላዊ መንገድ የተሠራ ወይን ተያዘበትና ዘብጥያ ወረደ። ምርመራው ቀጥሎ ካርል ከነመጥመቂያው ተያዘና ፍርድ ቀረበ። ፍርዱ ደግሞ እስራትና 350 ጅራፍ ግርፊያ ነበር። የታሳሪ ቤተሰቦች እና የብሪታንያ ፖለቲከኞች ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን ጨምሮ የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣናት ካርል አንደሪ እንዲፈታ ጫና ይፈጥሩ ዘንድ ግፊት አይሉባቸው ባጅቷል። ጠቅላይ ሚኒስትሩና በተዋረድ የሚገኙ ባለሥልጣናት ከሳውዲ ኢምባሲያቸው ጋር በመገናኘት ‹‹ካርል አቅመ ደካማ በሽተኛ ነው። ግርፋት፣ እስራቱን አይችልም!›› የሚል የካርል ቤተሰብ አቤቱታን በመያዝ ለወራት ጉትጎታውን ቢቀጥሉም የተሳካው ሰሞኑን ነበር።

የብሪታንያ ኢምባሲና ከፍተኛ ባለሥልጣናት ወንጀሉ ተረጋግጦበት የ350 ጅራፍ ግርፋትና እስራት የተበየበት ዜጋቸው ካርል ወህኒ መውረድ አሳስቧቸው የሳውዲ ዐረቢያን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ዜጋቸው ነጻ እንዲደረግ ያደረጉት ግፊትና ሙከራ ውዝግብ አስነስቶ እንደነበር የሚታወስ ነው። የብሪታንያ ዜጋው ፊሊፕ መታሰር ተከትሎ በቅርቡ አንድ ከፍተኛ የፖርላማ አባል የፊሊፕን መታሰር ተከትሎ የሳውዲ ዐረቢያ የሰብአዊ መብት አያያዝን እስከ መንቀፍ መድረሳቸው የሳውዲ ዲፕሎማቶችን ቁጣ አስከትሎ ነበር። በብሪታንያ ባለሥልጣናት በአደባባይ የተሰነዘረውን ነቀፋ በብሪታንያ የሳውዲ አምባሳደር ቁጣ የተሞላበት ምላሽ እንዲሰጡም አስገድዷቸው እንደነበር በዐረብ ኒውስ የተስየናገደው ዘገባ ይጠቀሳል። ወቀሳውን ‹‹ትንኮሳ ነው!›› በማለት የተቃወሙት የሳውዲው አምባሳደር የባለሥልጣኑ አስተያየት በሁለቱ አገራት መካከል ግንኙነት የሚያሻክር እንደሆነ በአንድ ታዋቂ ጋዜጣ የሰላ ሂስ እስከ መጻፍ አድርሷቸው ነበር።

ካርል አንደሪ ከተበየነበት 350 ጅራፍ ግርፋትና እስር ነጻ እንደሚሆን በሳውዲ የስራ ጉብኝት ያደረጉት የብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፊሊፕ ሃሞንድ (Philip Hammond) አረጋግጠዋል። ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፊሊፕ ሃሞንድ ወደ ሳውዲ ዐረቢያ መጥተው ከንጉሡ ሰልማን አብድልአዚዝ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አድል አል ጃብሪና ከከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር ባደረጉት ምክክር ዜጋቸው በቀጣይ ሳምንታት በነጻ እንደሚደረግ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡ በሳምንቱ ካርል ወደ አገሩ በሰላም ገብቷል።

የብሪታንያ መንግሥት በብሪታንያ ቆንስልና ኢምባሲዎች ቀስቃሽነት ዜጋቸውን ከወህኒ ለማውጣት ያደረጉትን ጥረት የሚደነቅ የብርቱ ዲፕሎማሲያው ጥረት ውጤት ነው ማለት ይቻላል። የተደረገው ግፊትና ያላሰረሰ ጥረት ተሳክቶ ወንጀል መስራቱ የተረጋገጠበት ፊሊፕ በቅርቡ ከቤተሰቡ ጋር እንደሚቀላቀል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፊሊፕ ጠቁመዋል። ይህንኑ መጃዎች ታዋቂ የሳውዲ ጋዜጦችና በርካታ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ዘግበውታል። አገር የሚያስከብር፣ ወገን የሚያኮራ ብርቱ ዲፕሎማሲ ማለት እንዲህ ነው ብለናል።

## የአገራችን ዲፕሎማሲ ክሽፈት - ሞት



## የተፈረደባት እህታችን ጉዳይ

የእኛ ዲፕሎማቶች በዚህ ረድፍ የሉም ማለቱ ይቀላል። አንድ ሁለት በቅርብ የማውቃቸውን ምሳሌዎች ልጠቁም። ከዓመታት በፊት አንዲት ኢትዮጵያዊት አሰሪዋን ገድላ ለፍርድ ቀርባ ውሳኔው ሲነገራት በቦታው የነበር ወዳጀ አስተርጉም ተብሎ ቀርቦ ያየውና የሆነውን አጫውቶኛል። ገድላለችና እንድትገደል ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ለምን እንደገደለች ስትጠየቅ ለዳኛው ጉዳዩን የሚያስረዳላት አልነበረም። በወቅቱ በፍርድ ቤቱ የነበሩትን ወዳጅና ጓደኛውን አንድ ፖሊስ ቀረብ ብሎ ‹‹ሐበሻ ከሆናችው እባካችሁ አስተርጉሙልን›› ብሎ ይጠይቃቸዋል። ወዳጀና ጓደኛው ፈቃደኝነታቸውን ገልጸው ወደ ዳኞቹ ክፍል ሲያመሩ አንዲት ልጅ እግር ሐበሻ ኢትዮጵያዊ ከፖሊስ አጠገብ ቆማ ያያሉ። የተጠሩት ይህችኑ እህት ለማስተርጎም መሆኑ ተነገራቸው። የመጨረሻው ፍርድ ሊሰጣት ተቃርቦ ነበርና የእምነት ክህደት ቃሏን ስጭ ተባለች በወዳጀ አስተርጓሚነት የሚጠይቁትን እየጠየቀ የምትለው ቃሏን እየተቀበለ ያስተረጉም ገባ፤ አገዳደሏን ሲጠይቃት ሚች ለዘጠኝ ወራት በር ዘግቶ ያሰቃያት እንደነበር፣ ወደ አገሬ ላከኝም ሆነ ወደ ኢምባሲዬ አድርሰኝ ብላ ብትማጸነው አሻፈረኝ ብሎ ይፈጽምባት የነበረውን አስነዋሪ ተግባር በዝርዝር አስረዳች። በመጨረሻም ጭንቀት ፈተናው ሲበዛባት በአንዱ ቀን ተበሳጭታና ራሷን ስታ በስለት እንደወጋችው ተናገረች። ይህን ካደረገች ከቀናት በኋላም ምን እንደሆነች ሳታውቅ ራሷን እስር ቤት እንዳገኘች እያለቀሰች ያስረዳችውን ሳይጨምር ሳይቀንስ ለዳኛው አስረዳ። ‹‹ይህን ሁሉ ጊዜ ስትመላለስ ይህን ለምን አልተናገረችም!›› በማለት የተቆጡት ዳኞች የሞት ፍርዱን ካሳለፉ በኋላ ኤምባሲዋ ቀርቦ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ መጠየቅ እንደሚችል አሳውቀውት ተለያዩ። ልጅቷም ባመጧት ፖሊሶች ታጅባ ሄደች።

ወዳጀ ከፍርድ ቤት እንደ ወጣ ሲደውልልኝ ጥልቅ ሀዘን እንደገባው ያስታውቅበታል። ለእኔ መረጃውን አቀብሎኝ ዝም አላለም። ወደ ጅዳ ቆንስል ሲበር ሄዶ ጉዳዩን ለዲፕሎማቶች በዝርዝር ማስረዳቱን ገልጾልኛል። ከዚያ ወዲህ ተገናኝተን ስናዎራ ጉዳዩ የት እንደደረሰ? ብየ ብጠይቀውም ለቆንስሉ ቢያሳውቅም ምንም ማድረግ ስላልቻሉ ጉዳዩን እንደተወው ነገረኝ። ይህ ሁሌም ያመኛል። ይታያችሁ ይሰማችሁ። እንደዚህች እህት ሁሉ በርካቶች በተለያዩ ጉዳዮች ተከሰው ጉዳያቸውን የሚከታተል፣ መብታቸውን የማስጠበቅላቸው የለም። ተበድለው ከሆነ ስለተበደሉበት፣ በድለው ከሆነ የበደሉበት ምክንያታቸውን የሚያስረዳላቸው የለምና ድምጻቸው ሳይሰማ ይጠፋሉ።

## ሚስቱን ላለማስደፈር ሲታገል ነፍስ ያጠፋው ኢትዮጵያዊ

ከአንድ ዓመት በፊት ጅዳ ውስጥ ፈይሰልያ በሚባል መንደር ሳውዲ ዐረቢያ ጎረምሶች የአንድ ሐበሻን ቤት ዘለው ገብተው ከዘረፉ በኋላ ወንዶችና ሴቶን ለየብቻ ያግቷቸዋል። ብዙም ሳይቆይ ሚስቱን አውጥተው ሊደፍሯት ሲታገሉ የድረሱልኝ ድምጽ የሰማው ወንድም የተዘጋበትን በር ሰበሮ በመውጣት ቀበቶውን ፈትቶ ሚስቱን ሊደፍር ከተዘጋጀው ወሮበላ ጋር ይተናነቃል። ባደረገው ግብግብ ቤት ዘራፊና ደፋሪው ወጣት ይዞት በመጣው ጩቤ ይወጋዋል። ደጋግመው ዘረፋ የፈጸሙትን፣ ቤቱንና ራሱን ለመከላከል ሲል በተፈጠረ ግጭት ሰው በእጁ የጠፋበት ወንድም ላለፉት ዓመታት በእስር ላይ ይገኛል። ራስን ለመከላከል ባደረገው ሙከራ በሠራው ጥፋት በእጁ ሕይወት ቢጠፋም ቅጣቱ ገድሏልና ይገደል ከሚለው ዝቅ ያለ ተመጣጣኝ ቅጣት ይሆን ዘንድ ገፊ መብት አስከባሪ አያስፈልግም ነበር። ግን

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# ሕዝብን የቀሰቀሰው . . .

ከዋናው የጉዳዩ ባለቤት ከሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የጀመሩትን ድብቅ ድርድር አጠናቀው ዛሬ አፋቸውን ሞልተው በቅርቡ ወደ ተግባር ለመተርጎም ቀነ ቀጠሮ መያዛቸውን ከራሳቸው አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ አንደበት እየሰማን ነው፡፡›› ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ ለፓርላማው ባቀረቡት ዘገባ መንግሥታቸው ምንም አይነት ኢትዮጵያን የሚጎዳ የድንበር ስምምነት እንዳላደረገ ገልጸዋል፡፡ በእርግጥ ይኼ ከሆነ ኢትዮጵያዊያን ይደሰታሉ እንጅ ወደ አቤቱታ አይሄዱም፡፡ ሆኖም፣ ግልጽነት የሌላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባስቸኳይ መገለጽ ያለባቸው አሳሳቢ ጉዳዮች አሁንም ተንጠልጥለው ስለሚገኙ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልስ እንዲሰጡባቸው አስኳሎቹን እጠቅሳቸዋለሁ፡፡

አንድ፣ በመለስ ዜናዊ አማክይነት ሕወሓት ከሱዳን መንግሥት ጋር የተዋዋለው የምስጢር ስምምነት ምንድን ነው? ምን ያህል መሬት ለሱዳን መንግሥት አስተላለፈ፣ ካላስተላለፈ መረጃው ምንድን ነው? ኢትዮጵያውያን ‹‹የኢትዮጵያን ድንበር አልፈው የሱዳንን መሬት ያርሳሉ›› ሲባል ምን ማለት ነው? የሚያርሱት መሬት የኢትዮጵያ ነው ወይስ የሱዳን? መረጃው ምንድን ነው? የኢትዮጵያ ገበሬዎች የሚያርሱት መሬት የኢትዮጵያ መሆን አለመሆኑ በምን መረጃ አስተማማኝ ይሆናል?

ሁለት፣ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት አጼ ምኒልክ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የተስማሙትንና በካርታው ላይ የፈረሙትን የ1902 ዓ.ም. ስምምነት ተቀብሎ ያስከብራል ወይስ አያስከብርም? ከአጼ ምኒልክ መንግሥት ጀምሮ እስከ ሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ድረስ ያሉት ተከታታይ መንግሥታት ሻለቃ ግዌን የተባለው የእንግሊዝ ተወካይ፣ በራሱ ወሳኝነት፣ የኢትዮጵያ ተወካዮች ባልተገኙበት የቸከለው የድንበር ችካል ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ ይኼን እኔም እጋራለሁ፡፡ መመለስ ያለበት ጉዳይ ስምምነት ላይ ደርሰን ድንበሩ ዕውቅና እንዲኖረው እናድርግ ሲባል የትኛውን ውል መሠረት አድርጎ የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ የግዌንን ችካል ማጽደቅ ወይስ አጼ ምኒልክ የፈረሙበትን ውል?

ሦስት፣ የኢትዮጵያና የሱዳን ሕዝብ በሰላም ለመኖር እንደሚፈልግ ይታወቃል፡፡ በ1902 ዓ.ም. በተደረገው ስምምነት መሠረት የሁለቱም አገሮች ተወካዮች በሚገኙበት ስምምነት ላይ ቢደረስ ችግሩ ይፈታል የሚል ግምት አለኝ፡፡ የሱዳን አምባሳደሮች እንዳሉት ጉዳዩ አስቸኳይ አይደለም፡፡ ከዚህ ተጻራሪ አቋም ካለ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ጉዳዩ ለምን አስቸኳይ እንደሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ የድንበር ጉዳዮች ኮሚቴ ያስተጋባው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹‹ከሕዝብ ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲበዛባቸው ከሱዳን ጋር የድንበር ስምምነት ለማድረግ እየተወያየን ነው፣ ሆኖም እስካሁን የተደረሰበት ስምምነት የለም ከሚል የተለመደ ቅጥፈት በቀር ሕወሓት ምንም ዓይነት ዝርዝር መረጃ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይገልጹ እንደግል ንብረታቸው ብቻቸውን ተወያይተው ብቻቸው ወስነው በመስዋዕትነት የተከበረው የድንበር መሬት እንደለመዱት ለባዕድ ሊያስረክቡ ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን አጥብቆ የሚጠላና ለማጥፋት የተነሳ ቡድን በተደጋጋሚ የአገር ሀብትን ሲሰጥ ለዓመታት ቁጭ ብለን አየን፡፡ ሕወሓት አገሪቱንና ሕዝቡን መጉዳት ሥራዬ ብሎ ሲቀጥልበት እኛ ደግሞ ዝምታውን አበዛነውና፣ እነሆ ዛሬ በለምነቱ፣ በውኃ ሀብቱ፣ በአዕዋፋትና በእንስሳት፣ በደንና በእጽዋት፣ የተከበበ ሰፊና ለም መሬት ለሱዳን ገጸ በረከት እያቀረበ ነው፡፡ ይኼ ከክህደቶች ሁሉ ትልቁ ክህደት የሆነው አገር የማጥፋት ሥራ ነገ ሳይሆን ዛሬ አንድ ሆነን ካላስቆምነው ‹ቁጭ ብለው የሰቀሉትን ቆመው ማውረድ ያዳግታል› እንደተባለው የሚያስከትለውን መዘዝ ከፍተኛ ነው›› የሚል ነው፡፡ ይኼን እሉታዊ ለማድረግ የሚቻለው በዘለፋና በዛቻ አይመስለኝም፡፡ እንደዚህ ግዙፍ በሆነ ብሔራዊ ጉዳይ ላይ አግባብ የሚኖረው መልስ ኃላፊነት፣ ግልጽነትና ለአገር ተቆርቋሪነት ነው፡፡ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ራሱ የፈጠረውን ችግር መፍታት ግዴታው ነው፡፡ የእኔ የግል እምነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ነው፡፡

የማይካደው አገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት አንድነቷንና ነጻነቷን በቀጣይነት ማስከበርና ማቆየት የቻለችው ተቀናቃኝ ጠላት ሳይኖራት ወይም በጎረቤቶቿ ፈቃድና እንዲሁ በታሪክ አጋጣሚ ሳይሆን ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብና በተለይም በድንበሩ አካባቢ የሚኖረው ወገናችን ለአገሩ አንድነትና ክብር ካለው ፍቅርና ቀናኢነት የተነሳ በከፈለው መሪርና ክቡር መስዋዕትነት ነው፡፡ የፖሊቲካ ርዕዮታቸውንም ይሁን እምነቶቻቸውን ተገን አድርገው የአገራችንን የውኃና የሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ሲቻል በቀጥታ ለመቆጣጠር አሊያም እንደልባቸው ለመበጥበጥ የፈለጉ የቅርብም ሆኑ የሩቅ ኃይሎች በተደጋጋሚ ያደረጉት ጥረት ምኞት ብቻ ሳይሆኑ ቅዠት ሆኖ እንዲቀር የተደረገው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጎሳ፣ የሃይማኖት፣የቋንቋም ይሁን የአካባቢ ልዩነት አጥር ሳያግደው ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች እንደ አንድ የአገር ዜጋ በጋራ በመቆምና የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል ነው፡፡ አጼ ቴዎድሮስ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት አጼ ዮሐንስን እና አጼ ምኒልክ የመሳሰሉ ታላላቅ መሪዎች ክቡር መስዋዕትነት እየከፈሉ አስከብረውት የቆየውንና በአካባቢው ጀግና ሕዝብ የመረረ ተጋድሎ ተጠብቆ የኖረውን የኢትዮጵያ ወሰን ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት የሚደረገው ሕገ ወጥ ውል ውሎ አድሮ የሚያስከተለው መዘዝ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ገበሬዎች የሱዳንን ድንበር ጥሰው የሱዳኖችን መሬት አርሰዋል የሚለው በማስረጃ ከተረጋገጠ ሁላችንም ይኼ ሕገ ወጥ እንደሆነ ማስተፍጋባት አለብን፡፡ በሰላም ለመኖር አንዱ የሌላውን ዳር ድንበት ማክበር አለበት፡፡

ወንድማማች፣ እህትማማች የሆኑትን አገራት ወደ አይቀሬ ጦርነት የሚወስድና ይህም ኢትዮጵያንና ሱዳንን በመልካም ጉርብትና ተከባብረው እንዳይኖሩ አልፎም ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ከፍተኛ ጠንቅ የሚሆን ድርጊት ተቀባይነት የለውም፡፡ ከገዢው ፓርቲም ሆነ ከሌላ ተቀባይነት የሌለውን ጎጅ ስራ ለማስፈጸም በመሯሯጥ ላይ ያሉ ሁሉ ድርጊቱን ማቆም ይኖርባቸዋል፡፡

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ባለሥልጣናት፣ በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በአገር ቤትና በውጭ የሚገኙ ስብስቦችና ግለሰቦች የሚያቀርቡትን የድንበር አቤቱታ በቀላሉ ማየት በታሪክ ፊት እንደሚያስጠይቃቸው አምናለሁ፡፡ ጉዳዩ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚጠቅም፣ ቢያንስ ባማይጎዳ ሁኔታ እንዲፈታ እመኛለሁ፡፡ ማስረጃዎችን በማያሻማ ደረጃ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማቅረብ መግባባትን እንደሚፈጥር አልጠራጠርም፡፡ ጉዳዩ የአንድ አካባቢ፣ የአንድ ጎሳ፣ የአንድ ሃይማኖት ወዘተ. አይደለም፡፡ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ተቀዳሚ ጉዳይ መሆኑን የሚካሄደው የአቤቱታ ዘመቻ አስምሮበታል፡፡

ለማጠቃለል፣ የኢትዮጵያ ገዥ ፓርቲ የቆየውንና ዕውቅና ያለውን ድንበር አፍርሶ ለሱዳን መንግሥት ከሰጠ ስምምነቱ ተቀባይነት እንደማይኖረው ብዙ የሕግ፣ የስምምነትና የይዞታ ባለሞያዎች አረጋግጠዋል፡፡ መሬቱ ከተሰጠ ተከታታይ ትውልድና ተቆርቋሪ የሆነ የወደፊት መንግሥት እንደሚከራከርበት እና እንደሚያስመልሰው አልጠራጠርም፡፡

# የዲፕሎማሲያችን ክሽፈት . . .

የለንም፡፡

ይህም ሁለት ዓመት ሆነው መሰል፣ ‹‹ሁልሰፋ›› በተባለ መንደር አንዲትን ኢትዮጵያዊ ከገደሉ በኋላ ጥቁር አበያና መነጽር ካለበሱ በኋላ በበሽተኛ ጋሪ አድርገው ወደ ቤቷ አምጥተው ጥለዋት ይሄዳሉ፡፡ ምን በሽተኛ አምጥተው ጣሉብን በማለት መነጽር ያደረገችውን ከጋሪው ላይ የተቀመጠች እህት ቢያናግሯት አይሰማም፡፡ ትንሽ ቆይተው ሞታ እያለ ልክ እንዳልሞተች ለማስመሰል ከጋሪው ጋር አስረው ነበር ያመጧት እህት ሬሳ መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ ወዲያው ቤቱን ጥለው ሲሄዱ ሬሳ እዚያ ቤት አምጥተው እንደተጣለባቸው ቤቱን የተከራየው ኢትዮጵያዊ ለፖሊስ ባሳወቀው መሠረት ሬሳው ተነሳ፡፡ ጉዳዩን ለቆንስል ኃላፊዎች አሳውቀን ነበር፡፡ እርግጥ ነው አንድ ሰሞን ይከታተሉት ነበር አሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ስለሆነው የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ ኢትዮጵያዊያቷ ሐና ገዳይዋ ማነው? የሚለው ጥያቄ በጣም የተወሳሰበ ወንጀል ድርጊትና የጉዳይ ማንነት ዛሬ መልስ ቢገኝለትም ጉዳዩን እስከ ጫፍ መከታተልና ማስፈጸም ያለበት ቆንስል መሥሪያ ቤት የሚያውቀው ነገር ስለመኖሩ ደጋግሜ ጠይቄ መልስ አላገኘሁም፡፡ ምናልባት ከላይ የጠቀስኳቸው ከበድ ከበድ ያሉ ናቸው ቢባል በሐኪሞች ስህተት 10 ዓመት የተኛው ብላቴናው መሐመድ አብድልአዚዝ ሲንገላታ ምን ዓይነት የመብት ጥበቃ ምን ተደረገ? ሌላው ቀርቶ ጤና ጥበቃ ያሳለፈውን ውሳኔ ይዞ፣ በመሳሪያ የሚንቀሳቀሰውን መሐመድ ይዛችሁ ካልወጣችሁ የተፈረደውን ካሳ አልሰጥም ያለውን ሆስፒታል ጉዳይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማስገባት ለምን አልተቻለም? ጠበቃ ቀርቦ የውጭ ጉዳይ የሕግ ምክር አልመጣም ተብሎ ጉዳዩ የሚጎተትበት እንቆቅልሽ ሊገባን አልቻለም፡፡

## የእኛስ ዲፕሎማሲ?

በሪያድ ኢምባሲ በጅዳ ቆንስል እንዳለን ይታወቃል፡፡ በቅርቡ ሳውዲ ዐረቢያን የጎበኙትን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያምን ጨምሮ እጅግ በርካታ ከፍተኛ ባለሥልጣኖቻችን ሳውዲ ዐረቢያን ተመላልሰው ጎብኝተዋል፡፡ የጉብኝታቸው ዋና ዓላማ የሁለትዮሽ ግንኙነትን፣ ለኢንቨስትመንትን ለማጎልበት ከማለት ባሻገር ሌላው ቀርቶ አንድ ሰሞን ሕጋዊ ተብሎ አሁን ሕጋዊ አልነበረም ባሉት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የመብት ጥበቃ ተነስቶ የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡ ይልቁንም የሰብአዊ መብት ጥበቃ ጎድሎብን ለምንንገላታ ዜጎች መላ አልተዘየደም ከማለት አልተሞከረም የሚለው ተስማሚ ቃል ይመስለኛል፡፡

መቼም እኛ ከላይ ወንጀለኛን ምህረት ስላስገኙት እንደ እንግሊዞች፣ ሠራተኞቻቸው ወንጀል ሠርተው እንኳን ለመብታቸው ዋቢ ጠበቃ እንደሚሆኑት እንደነ ፊሊፒን፣ ኢንዶኖዥያ፣ ሕንድ፣ ግብጽ፣ ወዘተ. ለተበደሉት በወንጀል ለተያዙት ጠበቃ ስለሚሆኑት ይሁኑልን ማለቱ ቅብጠት ሊመስል ይችላልና፣ ይህም ዛሬ ይሁንልን አላልንም፡፡ ዳሩ ግን በሰላም ከወንጀለኞች ርቀው በሚኖሩበት ቤት፣ በሚሠሩበት የሥራ ቦታ ‹‹ፈቃድ ከሌለው ጋር ተገኛችሁ!›› ተብለው እየተጋዙ በሚወሰዱት ዜጎች አያያዛዝና ቅጣታቸው በሕግና በሥርዓት ይደረግ ዘንድ ግን ተወካዮቻችን ተገን ጠበቃ ይሆኑን ዘንድ ሰሚ እስክናገኝ ሳንሰለች ብንልም አልሰሙንም፡፡

ዋና ሥራቸው የዜጎችን መብት ማስጠበቅ መርህ ያደረጉት በመንግሥት የተሰየሙት ተወካዮቻችን ዲፕሎማቶች ባልተረጋገጡ ወንጀሎች እጃቸውን አስገብተው የተያዙ ወንጀለኞችን መብት ይከራከሩና ነጻ ያውጡልን፡፡ ምህረት ያሰጡ ያለም የለም፡፡ የተረጋገጡ መረጃና ማስረጃ የተያዘባቸውን በደሎቻችን ግን ለከፍተኛ የሳውዲ ዐረቢያ መንግሥት ኃላፊዎች ያቅርቡልን እያልን መማጸናችን ግን ግድ ነው፡፡ የተለያዩ አገር ዜጎች ዜጎቻቸው ማናቸውም በደልና የመብት ጥሰት ሲፈጸምባቸው በሕግ አንጻር አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ ወስደው፣ ተበዳይ፣ በዳይ ታሳሪዎችን በማማከርና ጠበቃ ድረስ በመቅጠር መብታቸውን ሲያስከብሩላቸው ተመልክተናል፡፡ ከወራት በፊት የእንግሊዝ ዲፕሎማቶች በመጠጥ ስራ የተያዘ ዜጋቸው የተበየነበት የ350 ጅራፍ ግርፊያ እንዳይፈጸምበትና በነጻ ወደ አገሪቱ እንዲገባ እንዳደረጉ ዓይተናል፡፡ የኢንዶኖዥያ መንግሥት በበኩሉ ከአመታት በፊት ‹‹በዜጋየ ላይ ግፍ ተፈጸመ፣ ተመጣጣኝ ያልሆነ ፍርድ ተሰጠ!›› ብለው የኮንትራት ሠራተኛ እስከማገድ እንደደረሱም ተመልክተናል፡፡ ሕንዶች ያን ሰሞን ‹‹ዜጋችን ከፎቅ ወደቀች!›› ብለው ከመንግሥት ጋር ከበድ ወዳለ አምባጓሮ ገብተው ጉዳዩ የተፈታው በድርድር ነበር፡፡ ፊሊፒኖች፣ ግብጾችና የተናቁት ባንግላዲሾች ሳይቀሩ ለተገፉ፣ ለተበደሉና መብታቸውን ለተነጠቁ ዜጎቻቸው ጠበቃ ሳይቀር እያጠሩ በሕግ ማሕቀፍ እየተከራከሩ፣ እስከ ሞት ፍርድ ያለውን ከባድ ወንጀል ማቅለያ መንገድ በመፈለግ ወደ ተመጣጣኝ ፍርድ በማስቀየር ዜጎቻቸውን ይታደጓቸዋል፡፡ የሌሎች አገራት ትጋትና የእኛ መብት ማስከበር ክሽፈት ይህን ያህል የሰፋ ነው፡፡


# ኮከብ ብርሃን
## የባህል ሕክምና ማዕከል

ማንኛውም ባለጉዳይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በትህትና በማስተናገድ ላይ ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ትክክለኛ ፈውስ የተገኘላቸው በሽታዎች በከፊል፡-

- ለሆድ ሕመም
- ለእጅና ለእግር ቁርጥማት
- ለአስም
- ለሾተላይ
- ለራስ ሕመም
- ለእግር ፈንገስ
- ለሚጥል በሽታ
- ለማዲያት
- እጁን ለሚጠባ
- ለትምህርት
- ለእጅ ሰብእ
- ለጭርት ወይም ማሳከክ
- ለአይነ ጥላ
- ለወር አበባ መብዛት
- ሌሊት ለሚሸና

በተለይ የብዙ ሰዎችን ችግር የሆነውን የስንፈተ ወሲብ /በመቀባት/ ብቻ ፈውስ ይሰጣል።


አድራሻ፡-

ሐና ማርያም ቀለበት መንገድ ንግድ ባንክ ፊት ለፊት

ለበለጠ መረጃ፡- 0911 808241 /0913 778746/ 0912 635069

በእውነት ስለ እውነት እንተጋለን!!

## ታሪክና ኅብረተሰብ



ታዴዎስ ታንቱ
(የስልክ ቁጥር:- 0934996138 ፣ የመ.ሳ. ቁጥር:- 43414)

# “አብዮቱና ትዝታዬ” ሲፈተሽ
## (፪)

ጓድ ፍስሐ ደስታ ‹‹… በግቢው ውስጥ የመትረጊስ ተኩስ ጀምሮ…›› ሲል ምናልባት የወህኒ ቤት ግቢን ማለቱ ይሆን እንዴ? ይህ ደግሞ ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም ለወህኒ ቤት የጥበቃ አዛገሮችና ምድብተኛ ዘቦች በወህኒ ቤቱ ዙሪያ ተኩስ ቢሰሙም አጸፋ እንዳይሰጡ ተነግሯቸዋል:: ምናልባት የጥበቃ አዛገሮችና ምድብተኛ የወህኒ ቤት ዘቦች የተኩስ ድምጽ በድንገት ሲሰሙ እስረኛ የሚያስመልጥ አካል የመጣባቸው መስሏቸው ተደናግጠው ተኩስ ሊከፍቱ እንደሚችሉ ይገመታል:: በምክንያቱ ምክንያት ለጥበቃ ሲባል በጊዜው እንዲያውቁት ተደርጓል:: በርግጥ በቀጥታ ባለሥልጣናት፣ ጀኔራሎች፣ ከፍተኛ መኮነኖች፣ የበታች ሹማምንት እንደሚረሸኑ ላይነገራቸው ይችላል:: ነገር ግን እርምጃ የሚወሰድባቸው ሰዎች እንዳሉ በቅድሚያ ለወህኒ ቤት ተነግሮታል:: ከደርግ ጽሕፈት ቤት የተላኩ ሰዎች ቀን ወህኒ ቤት ወርደው እግረ ሙቅ ይዘው ተመልሰዋል:: ጓድ ፍስሐ ደስታ ይህንም አያውቅ ይሆን እንዴ? ይኸም ብቻ አልነበረም:: ባለሥልጣናት፣ ጀኔራሎች፣ ከፍተኛ መከንኖችና የበታች ሹማምንት ወደ ወህኒ ቤት ከመድረሳቸው ቀደም ብሎ ወታደሮች መትረጊሶችን ደግነው ባውዛ አብርተው ሲጠባበቁ የጥበቃ አዛገሮች አይተዋቸዋል:: ስለዚህ በሰዓቱ በወህኒ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሕገ ወጥ ተኩስ ፈጽሞ ሊኖር አይችልም:: በቤተመንግሥት ግቢም ውስጥ በወቅቱ በደመ ነፍስ መትረጊስ የተኮሰ አልነበረም:: በዚህ ምክንያት ‹‹… በግቢው ውስጥ የመትረጊስ ተኩስ ጀምሮ …›› በማለት ጓድ ፍስሐ ደስታ ያቀረበው ወሬ ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው:: ጓድ ፍስሐ ደስታ ከውሸት ምን ሊያተርፍ አስቦ ይሆን? አንባብያንን ለማጭበርበር መሞከር ያስገምታል:: ለምን ያጭበረብራል?

በእንዲህ ያለ አነጋገር ወጣቶችን ማሳሳት ይችል ይሆናል:: ነገር ግን በዘመኑ የነበርነው አሳምረን እናውቃለን:: ጓድ ፍስሐ ደስታም በቅደም ተከተል የሆነውን ሁሉ አልዘነጋውም:: በክህደት ቃና ጥራዝ የጻፈው ከኃላፊነት ለመሸሽ አስቦ መሆኑን ልናውቅ ይገባል:: ‹‹አልሸሸም›› እያለ ሲሸሽ ይስተዋላል:: ‹‹ከምሽቱ በሁለት ሰዓት ከወደ ወህኒ ቤት ከባድ ተኩስ ተሰማ›› ማለት ራሱ ሽሽት ነው:: ድብቅ አነጋገር ነው:: የክህደት ጠረን አለው:: አድርባይነት ነው:: ጓድ ፍስሐ የት ሆኖ ሰማ? ሒደቱን አብሮ የተሳተፈ ሰው ተኩስ መስማቱን እንዴት ይነግረናል? ጓድ ፍስሐ ደስታ የሚገደሉ ባለሥልጣናትን፣ ጀኔራሎችን፣ ከፍተኛ መከነኖችንና የበታች ሹማምንትን ያሳፈረ ተሽከርካሪ ከኋላና ከፊት የጦር መሣሪያ በደገኑ ተሽከርካሪዎች ታጅቦ ከቤተ መንግሥት ግቢ ሰወጣ አላየም? ለምን ይዋሻል? ‹‹ከምሽቱ በሁለት ሰዓት ከወደ ወህኒ ቤት ከባድ ተኩስ ተሰማ›› ሲል በሱ ቤት አማርኛ መናገሩ ነው? የቤተ መንግሥት ግቢ የጥበቃ አዛገሮችና ምድብተኛ ዘቦችስ ተሽከርካሪው በአጀብ ከግቢው ሲወጣ አላዩትም? ጓድ ፍስሐ የቅጣት ውሳኔውን በእስራት ፈጽሟል:: ታዲያ አሁን ምን አስፈራው? ያም ሆነ ይህ ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. ከቤተ መንግሥት ግቢ አንስቶ ባለሥልጣናትን፣ ጀኔራሎችን፣ ከፍተኛ መኮነኖችንና የበታች ሹማምንትን ለመግደል ስለተካሔደው ሒደት አሁንም ቀደም ሲል ከተጠቀሰው መጽሐፍ ቀንጭበናል፤ ይነበባል::

‹‹በተያዝሁ በአሥረኛው ቀን ቅዳሜ ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. በአገሬ ከተካሄዱት ግድያዎች ሁሉ ዘግናኝ ግድያ ለመመስከር ችያለሁ:: ከበሩ አጠገብ ተኝቼ ሳለሁ በበሩ ቀዳዳ ከውጭ በኩል ብርድ ልብስ ቁልቁል ሲዘረጋ ተመለከትሁ:: ከዐሥራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ በሩ ሲከፈት ደግሞ ሻለቃ ጌታቸው ሽበሺ ብጣሽ ወረቀት ይዞ ከውጭ ቁሞ ታይቷል:: ሻለቃ ጌታቸው ሽበሺ የእስረኞች ቃል አቀባይ የሆነው ዶ/ር ምናሴ ከተቀሩት ተለይቶ ወደ ፊት እንዲመጣ ጠየቀ:: ሻለቃው ቀጥሎ የሚጠራቸው ሰዎች ወደ ውጭ መውጣት እንዳለባቸው አስታወቀ:: እሱ የጠራቸውን ደግሞ ቤት ውስጥ የነበረው እስረኛ ሁሉ እንደሰማ ዶ/ር ምናሴ ይደግማል:: ሃያ ሰባት ሰዎች ተጠርተው ወጡ:: አሁንም የመዝጊያው ቀዳዳ በብርድ ልብስ የተሸፈነ በመሆኑ ከሚቀጥለው ክፍል የሚወጡን እስረኞች ማየት አልተቻለም:: እስረኞች ከዕይታችን እንደራቁ ግን በእግረ ሙቅ ታስረው ተዘጋጅቶ ይጠብቅ በነበረው በእስር ቤት ተሽከርካሪ ውስጥ እንደገቡ በኋላ ልናውቅ ችለናል:: በልዩ ልዩ እስር ቤቶችና በሆስፒታሎች ተኝተው የነበሩትን ጨምሮ በጠቅላላው 60 ሰለባዎች ወደ ዋናው ወህኒ ቤት ግቢ ተወስደው ተረሸነዋል::

‹‹Ten days after my arrest on Saturday, 23 November 1974, I was to witness the beginning of one of the most savage acts of murder ever perpetrated in my country. Lying in bed close to the door with a cold, I noticed a blanket being draped over the peephole from the outside. Fifteen minutes later the door opened to reveal Major Getachew Shibesh standing outside with a piece of paper in his hand. Major Getachew Shibeshi asked for Dr. Minasse, the spokesman of the inmates, to come forward. The Major then announced he was going to read the names of a group of people who should come out when they were called. Minasse was to repeat what he said so everybody inside could hear. Twenty-seven people were called out. The peephole had been covered so we could not see them removing people from the adjoining room. We were to discover later that as soon as they were out of our sight they were handcuffed and pushed in to a waiting prison van. They collected a total of 60 victims from various places of detention, including those who were in the hospital, and transported them to the main prison compound. There they were machine- gunned.›› (The Emperor’s Clothes page #188)

እውነታው ይህ ነው:: ይህ እውነት ነው:: ጓድ ፍስሐ ደስታ በከንቱ ይሸፋፍናል:: ወዲያውኑ እንዲያፈጽም የተመደበው ሻለቃ (በኋላ ሜጀር ጄኔራል) ጌታቸው ሽበሺ መሆኑንም አሳምሮ ያውቃል:: ሟቾች ሲወሰዱ ለግድያ መሆኑን አላቁምም ነበር:: ስለዚህ አንዳንዶቹ የሚሄዱት ወደ ዋናው ወህኒ ቤት ከሆነ ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት የተሻለ ቦታ መሆኑን በማሰብ ደስ ብሏቸው እንደነበር ታውቋል:: በኋላ ግን የተሳፈሩበት ተሽከርካሪ በቀጥታ ወደ እስረኞች መኖሪያ ማምራቱን ትቶ አቅጣጫውን ሲቀይር ከባለሥልጣናት አንዱ (ስሙን መጥቀስ አልፈለግንም) ‹‹ኸረ እባካችሁ ከመካከላችን ንጹሐንም አሉ!›› ማለቱ ተነግሯል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ከዚህ ባለሥልጣን ጋር የጋብቻ ዝምድና የነበረው (ስሙን መጥቀስ አልፈለግንም) ደግሞ ‹‹ልጆቼ እባካችሁ ጣዕራችን አታብዙ:: ቀልጠፍ ፈጠን በማለት ጨርሱን!›› ብሎ መናገሩን ተመልክቷል:: በተያያዘ መረጃ አንድ ትልቅ ባለሥልጣን (ስሙን መጥቀስ አልፈለግንም) ደግሞ ‹‹እባካችሁ ልጆቼ ሽንቴን ሽንቼ ልመለስ›› ብሎ መናገሩ በወቅቱ ሲወራ ሰንብቷል:: በተመሳሳይ መልኩ አንድ ባለሥልጣን (ስሙን መጥቀስ አልለግንም) ደግሞ ‹‹በዚህ ሁኔታ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልትገዙ አትችሉም›› ማለቱ በጥራዝ ላይ ለንባብ በቅቷል:: እንዲሁም አንድ ጄኔራል (ስሙን መጥቀስ አልፈለግንም) ‹‹ምንም አይቆጨኝም፤ በሕይወት ዘመናችን ጊዜው የፈቀደውን ሁሉ ሠርተናል›› በማለት መናገሩ በስፋት ተወርቷል::

የግድያ ሥነ ሥርዓት ተጠናቆ የደርግ አባላትና ምድብተኛ ገዳዮች ከተመለሱ በኋላ የወህኒ ቤት ፖሊሶች በሬሳዎች መካከል ሲዘዋወሩ የሚያቃስት ድምጽ ሰሙ:: ተጠራጥረው ለማረጋገጥ ጠጋ አሉ:: እንኳን ሊሞት ቀርቶ አጠገቡ ሰው መኖሩንም ለይቶ ያውቅ ነበርና ‹‹እባካችሁ ሐኪም ቤት ውሰዱኝ:: እናት የሌላቸው ሁለት ልጆች አሉኝ›› በማለት ተማጸነ:: ፖሊሶችም ከፍተሻ ተኩስ እንዴት ሊያመልጥ እንደቻለ በጣም ተገርመው ነገር ግን በራሳቸው ሥልጣን

> **ጀበወቅቱ ባለሥልጣናቱ እጃቸውን ካልሰጡ ንብረታቸው እንደሚወረስ በመገናኛ ብዙሃን ማስጠንቀቂያ በመነገሩ እጃቸውን ሰጥተዋል። ለንብረታቸው ሲሉ ተሽቀዳድመው እጃቸውን ሰጥተዋል። ይኼን አሳምረን እናውቃለን**

ለመግደልም ሆነ ሐኪም ቤት ለመውሰድ አልፈቀዱም:: ወዲያውኑ ለደርግ ጽሕፈት ቤት ስልክ መቱ:: ትዕዛዝ ተቀበሉ:: ጨረሱት::

ጓድ ፍስሐ ደስታ የኢሕዴሪ ምክትል ፕሬዝዳንትና የቀድሞ የደርግ አባል የዘውድ ሥርዓተ አገዛዝ ባለሥልጣናትን ጄኔራሎችን፣ ከፍተኛ መኮንኖችንና የበታች ሹማምንትን በወቅቱ ያለፍርድ ቤት ውሳኔ በሥነ መንግሥታዊ እርምጃ ማስወገዱ ትክክል እንዳልነበረ ከአርባ ዓመታት በኋላ በንስሐ ቅላጼ ያትታል:: ይናገራል:: ቀንጭበናል ‹‹ትልቁ ስህተት›› ይላል ጓድ ፍስሐ ደስታ ‹‹ትልቁ ስህተት ግን ጉዳያችሁ በፍርድ ይታያል ተብሎ ተደጋጋሚ ማረጋገጫ ተሰጥቶ በሰላም እጃቸውን የሰጡትን አዛውንቶች ቃላችንን አጥፈን ጉዳያቸውን በሚገባ ሳያስረዱና ሳይከላከሉ ውሳኔው ከፍርድ ውጭ መፈጸሙ ነበር›› ገጽ 129::

የጥራዙ አደራጅ በከፍተኛ ደረጃ የአማርኛ ችግር ያለበት ከመሆኑም በላይ ሁነቶችን ቅደም ተከተል ለማስያዝም በጣም ተቸግሮ ይታያል:: ለወሬ ቸኩሏል:: ይህን የታጠፈ ብርድ ልብስ የሚያህል ጥራዝ ማየቱ ብቻ ያስደስተዋል:: ታሪክ ይነግረናል:: የሁነቶችን ቅደም ተከተል መጠበቅ ግን ተስኖታል:: ጓድ ፍስሐ ለዚህ አነስተኛ ጉዳይ እንኳን የግንዛቤ አቅም ሳይኖረው ጥራዝ ለመቸብቸብ እንዴት ተነሳ? ይኼ ያስገምታል:: ያስንቃል:: በወኔ ብቻ ጥራዝ ይደራጃል እንዴ? ጥራዙን አርትኦትም የጎበኘው አይመስልም:: የትኛው ይቀድማል? ባለሥልጣናት በቅድሚያ እጃቸውን ሰጡ አይደል? ጉዳያቸው በፍርድ እንደሚታይ ቃል ተገባ:: ነገር ግን ባለሥልጣናት፣ ጄኔራሎች፣ ከፍተኛ መኮነኖችና የበታች ሹማምንት ያለፍርድ ቤት በደርግ ሥነ መንግሥታዊ እርምጃ ከዚህ ዓለም ተወገዱ:: አሁን ምን ሆነ? ቃል ፈረሰ::

ጥራዝ ቸብቻቢው ጓድ ፍስሐ ደስታ ለማለት የፈለገው ይህን ነው:: ግን ግራ ገብቶት አንባቢያንን ግራ ያጋባል:: ጓድ ፍስሐን እስኪ ጥያቄ እንጠይቀው:: ባለሥልጣናቱ እጃቸውን የሰጡት ጉዳያቸው በሕግ አግባብ እንደሚታይ ማረጋገጫ ከተሰጣቸው በኋላ መሆኑን ስትናገር ትንሽ አታፍርም? እንዴት እንደዚህ ትላለህ? ታሪክ ለምን ታሳስታለህ? እውነትን ለምን ታዛባለህ? የደርግ አባላት እኮ ሞተው አላለቁም:: አሉ:: ዘመዶችህን እያኗኗሯቸው ነው:: በወቅቱ ባለሥልጣናቱ እጃቸውን ካልሰጡ ንብረታቸው እንደሚወረስ በመገናኛ ብዙሃን ማስጠንቀቂያ በመነገሩ እጃቸውን ሰጥተዋል:: ለንብረታቸው ሲሉ ተሽቀዳድመው እጃቸውን ሰጥተዋል:: ይኼን አሳምረን እናውቃለን:: እንዲያውም አንድ ባለሥልጣን በወቅቱ የተሰጠው ጊዜ ለማለቅ ጥቂት ሰዓታት ሲቀሩ ‹‹መጣሁ! መጣሁ! ደርሻለሁ!›› በማለት ለጦር ኃይሎች፣ ለፖሊስ ሠራዊትና ለብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ (በኋላ ደርግ) ስልክ ደውሎ እንደነበር በመገናኛ ብዙሃን ተነግሯል:: እርግጥ ነው አንዳንድ ጄኔራል መኮንኖችና ሲቪል ሹማምንት ቤታቸው ተከቦ እጃቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል:: ታሪክ ማዛባት ደግ አይደለም:: ጓድ ፍስሐ ይዋሻል:: ከአብዮቱ በኋላ ለተወለዱ ዜጎች ቅጥፈትን ሲያስተምር እየሰማን ዝም ልንል አይገባም::

ጓድ ፍስሐ ደስታ ለዘውድ አገዛዝ ባለሥልጣናት፣ ጄኔራሎች፣ ከፍተኛ መኮንኖችና የበታች ሹማምንት ጉዳያቸው በሕግ አግባብ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያገኝ ማረጋገጫ የሰጠው ማነው? ለምን ሳትነግረን አለፍህ? ባልነበረ ሁነት ወሬ አደራጅተህ ለጥራዝ ችርቻሮ ገበያ እንዴት ትወጣለህ? ‹‹… ተደጋጋሚ ማረጋገጫ …›› ያልከው ፈጽሞ ሐሰት ነው:: እንኳንስ ተደጋጋሚ ማረጋገጫ ሊሰጥ ቀርቶ አንዴም ሕይወታቸው እንደማይነካ ለባለሥልጣናቱ ቃል የተገባ ነገር የለም:: ተባራሪ ወሬ ወይም የግለሰቦች አስተያየት እንደማረጋገጫ ሊወሰድ አይችልም:: ዳኞች ራሳቸው ታሳሪዎች እንደነበሩ እንዴት ረሳህ? ታሪክ ተመራማሪዎች የአንተን እንቶ ፈንቶ እንደምንጭ ሊጠቅሱ እንደሚችሉ ማሰብ ነበረብህ:: በዚህ ጊዜ ማን ለማን ማረጋገጫ ሊሰጥ ይችላል? የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አገዛዝ በመንገዳገድ ላይ ነበረ:: የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሰራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ ደግሞ የመንግሥትነት እውቅናን ገና አላገኘም:: መርማሪ ኮሚሽን በእርግጥ ተመስርቷል:: በሕግ ተቋቁሟል:: ምርመራውም ቀጥሏል:: ይህ ግን ለታሰሩ ባለሥልጣናት፣ ጄኔራሎች፣ ከፍተኛ መኮንኖችና ለበታች ሹማምንት ጉዳያቸው በሕግ አግባብ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያገኝ ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም:: ሰዎች በእርግጥ በከተማ ውስጥ በግምት ያወሩ እንደነበር ይታወሳል:: መርማሪ ኮሚሽን ስለተቋቋመ ምናልባት ለፍርድ ቀርበው ይሆናል ተብሎ እንደተወራ አንርሳ:: ጓድ ፍስሐ ደስታ ይህን መሠረተ ቢስ ወሬ ተቀብሎ በጽሑፍ አደራጅቶ በስደተኞች ማተሚያ ቤት አምርቶ በብር 250.00 (ሁለት መቶ ሐምሳ ብር) ይቸረችራል:: የወሬ ነዶ አስሮ በአሉባልታ ክምር ድርሳነ ንስሐ ይሸቅጣል:: በዘር መርህ አገዛዝ የሥነ መንግሥት ገበያ ወቅታዊ የጥራዝ አየር ባየር ነጋዴ ሆኗል:: አድርባይነት መጥፎ ቢሆንም መሰንበት ደግ መሆኑን አውቋል:: ብልጠት ይሏል ይኼ ነው!!

የቀድሞ የኢሕዲሪ ም/ፕሬዝዳንት ጓድ ፍስሐ ደስታ የቅልቡ የክቡር ዘበኛ አባል የነበረ ሲሆን የውትድርና ሙያ ዐቢይ ተልኮ የሆነውን የቀበሮ ጉድጓድ ሕይወት ለአፍታ እንኳን አይቶት የማያውቅ በዘውድ ቤተ መንግሥት በሻምፓኝ እየተራጨ እንደወሎ ፈረስ መልኩን አሳምሮ ሲጠሩት አቤት! ሲልኩት ወዴት! በማለት የንጉሠ ነገሥቱን፣ የልዑላኑንና የልዕልታትን ደህንነት እንደ ዓይኑ ብሌን ሲጠብቅ የኖረ በኋላ ደግሞ ጊዜ አይቶ ወደ ግራ በመከርበት በአብዮቱ ዋዜማ ከልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች በተወከሉ ጭቁን መለዮ ለባሾች ላይ ተጣብቆ በደርግ አባልነቱ ጓድ መኳንንት በመሆን በየሄደበት ሁሉ ወያኔ አለመሆኑን በሌኒን ስም ሲምል ዓመታትን ያስቆጠረ ዛሬ ደግሞ በለመደው የአድርባይነት ችሎታው ወደ ቀኝ ተከርብቶ የዘውድ ሥርዓት አገዛዝ ባለሥልጣናት፣ ጄኔራሎች፣ ከፍተኛ መኮንኖች እንዲሁም የበታች ሹማምንት በሥነ መንግሥታዊ ውሳኔ ጭዳ ተደርገው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ያሳነጹትን የመቃብር ቤት ተነፍገው ተሽከርካሪዎቻቸውን እንኳን በቤት ፈትል ጋቢና ቡልኮ የሚያስወለዉሉ የዚህች ምድር ጌቶች ከፈን አጥተው በኖራ ተለውሰው ከአፈር ጋር መዋሐዳቸው ትልቅ ስህተት እንደነበር በጨኸት ቃና በብዕሩ ለስሜቱ ሲናገር ሰምተን ከማፈራችን የተነሳ በትንሷ ጥፍራችን ውስጥ ለመደበቅ ተገደናል::

የጥራዙ ጸሐፊ ጓድ ፍስሐ ደስታ አሁንም ይናገራል:: ያወራል:: ያስነብበናል:: ሕዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. በሥነ መንግሥታዊ ውሳኔ የሞት ቅጣት ከተፈጸመባቸው ባለሥልጣናት፣ ጄኔራሎች፣ ከፍተኛ መኮንኖችና የበታች ሹማምንት መካከል በአምስቱ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ዓመታት ጠላትን መድረሻ ያሳጡትና አገራችንን በቅንነት ያገለገሉ እንደነበሩባቸው በእርግጠኝነት ይናገራል:: እንዲህ ይነበባል::

‹‹እርምጃ ከተወሰደባቸው መካከል በአምስቱ የጣሊያን ወረራ ዘመን በዱር በገደሉ እየተዘዋወሩ ጠላትን መድረሻ ያሳጡ አርበኞች እንደዚሁም አገራቸውን በቅንነት ያገለገሉ ንጹሓን እንደነበሩ አያጠራጥርም›› (ገጽ 129)::

ከነፍስ ግድያ ሐጢያት ራሱን ለማንጻት በንስሐ አቋም የሚናገረው ጓድ ፍስሐ ደስታ ለመናገር ያህል ከመናገሩ በስተቀር ጠላትን በአርበኝነት መድረሻ ያሳጡትንና አገራቸውን በቅንነት ያገለገሉትን በስም አልጠቀሰም:: በአርባይነት የተካነው ጓድ ፍስሐ ደስታ የደርግ አስተዳደር እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ ሥለባለሥልጣናቱ ግድያ አንዳችም ነገር ተናግሮ አያውቅም:: በአርበኝነት ያገለገሉት እነማን ነበሩ? አያ ፍስሐ ለምን አልነገርከንም? አገራችን በቅንነት ያገለገሉትስ እነማን ነበሩ? ጥቂት እስኪ እናንሳ:: በአርበኝነት በዱር በገደሉ የተንከራተቱና አገራቸውን በቅንነት ያገለገሉ ቀርተው ሌሎች ብቻ መገደል ነበረባቸው ማለትህ ነው እንዴ? አቋምህ ግልጽ አይደለም:: ለምን ታወላውላለህ? የሁሉም ጉዳይ በሕግ መታየት ነበረበት ካልህ በዚያው ጽና! የምትፈራው መንግሥቱ ኃይለማርያም አሁን በሥልጣን ላይ የለም:: ግልጽ ባለ አቋም ለምን አትወጣም?


ይቀጥላል

# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

## በሁሉም መጻሕፍት መደብሮች ያገኙታል

‹‹አገር ከፋፋዩ የዘመነ መሳፍንት አደጋ ‘በዘመነ ግንባር’ መልክ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰውና አገር የማፈራረስ እንቅስቃሴ እንደ አዲስ የተጀመረው በኤርትራ ቡድኖች ነው። እነሱን ተከትለው ሕወሐትን፣ ኦነግንና ኦብነግን ጨምሮ በርካታ የግንጠላ ቡድኖች መነሳታቸው ይታወቃል። ... የዘመናችን ሌሎች ግንባሮች የሚጓዙትም በዚሁ ዓይነቱ መንገድ ከመሆን አያመልጥም። በኤርትራ ምድር የሆነውን ሁሉ እነሱም ያደርጉታል። በ30 ዓመቱ ጦርነት በኤርትራ በረሃ ውስጥ ምን ተፈጸመ?››

መልሱን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያገኙታል። በሁሉም መጽሐፍት መደብሮችና በመጽሐፍ አዟሪዎች እጅ ያገኙታል።




ዋና አከፋፋይ ባሕሩ መጽሐፍት ቤት

ስልክ ቁጥር 09 11 63 68 15



# አዲስ የግጥም መድበል በገበያ ላይ!

## መጽሐፉን በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ባሉ የመጻሕፍት መደብሮች ያገኙታል።




የሀገር ፍቅር፣ ፖለቲካና እምነት ተሰናስለው የቀረቡበት በዓይነቱና በአቀራረቡ ልዩ የሆነ የግጥም መድበል ለገበያ ቀረበልዎ! መድበሉ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪ በሆነው መምህር ምንዋጋው ተመስገን ተዘጋጅቶ ለንባብ የበቃ ነው። “ዓለማዊ” እና “መንፈሳዊ” በሚል በሁለት ክፍሎች የተካተቱት 52 ግጥሞች እንደሀገር የገባንበትን ሞራለ ቢስነትና ሆድ አምላኩነት ፍንትው አድርገው የሚያሳዩን ናቸው።



# መንቶች የዕጽዋት (የባህል) መድኃኒት ማምረቻና መሸጫ

## MENTOCHE HERBAL MEDICINE PRODUCTION CENTER



ይህ የዕጽዋት መድኃኒት ማዕከል ሲወርድ ሲዋረድ የነበረውን የአባቶች የባህል (እጽዋት) መድኃኒት ሕክምና በማሳደግ ፍቱንነታቸዉ ተረጋግጦ በከፊል በሳይንስና ቴክኖሎጅ በማስመዝገብና ከኢንቨስትመንት ፈቃድ በመውሰድ በማምረት ላይ ይገኛል። ለዉስጥ ችግር በሚወሰድ፣ በቆዳ ላይ ለሚወጣ በመቀባት ሲሆን ከኬሚካልም ሆነ ከባዕድ ነገሮች ነጻ የሆነ ነው። ከሚመረቱት ምርቶች በከፊል

### በሚወሰድ

- ለኪንታሮት ፌስቱላ መድሀኒት በደም ዉስጥ ያለን አጥቦ የሚያወጣ ሲሆን ድርቀት፣ ወገብ ችግር፣ ጋዝና ወሲብ ችግርን ያድናል።
- ለነቀርሳ (ካንሰር) በሽታ ከደም ውስጥ አጥቦ የሚያወጣ በጭንቅላት፣ በአንገት፣ በጡትም ሆነ በአንጀት ላይ ያለዉን ያድናል።
- የደም ግፊት (ብዛት) እስከ መጨረሻዉ የሚያድን።

የኮሌስትሮል፣ የስብና የፕሮቲን ክምችትን ያቀልጣል፤ ስለሆነም ኮሌስትሮል ያጠፋል።

- ለነርቭ፣ ለሪህ፣ ለደም መወፈር (መርጋት) ለዲስክ መንሸራተት ያድናል።
- ለጉበት ሄፓታይተስ ሦስቱንም አይነት የጉበት በሽታ ያድናል።
- ለአእምሮ ጭንቀት ለሚጥል በሽታና ለሚያፈዘዉ ያድናል።
- ለቆዳ በሽታ አለርጅክም ሆነ ፈንገስ ሶራይስስ ጭምር ያድናል።
- ኤድስን የሚያባብሱ ተዛማጅ በሽታዎችን በማከም የድካም ስሜትን፣ መክሳትንና የምግብ ፍላጎት መቀነስን እንዲጨምር ያደርጋል።
- በሆድ ዉስጥ ላለ በሽታ አሜባ፣ ታይፎይድ፣ ጃርዲያ፣ አስካሪስና ውሃ ወለድ በሽታዎችን ያድናል።
- ‹‹ሽንት ለሚያስቸግረውና ለስኳ በሽታ ፍቱን መድኃኒት አለን››

### የሚቀባና በፊንጣጣ የሚገባ መድኃኒት

- ለኪንታሮት (ፌስቱላ) በሚቀባ ምንም አይነት ህመም የሌለዉ ሲሆን ሥራም የማያስፈታ ነዉ። ለቆየ የአባላዘር ለዉስጥ ኪንታሮት በፊንጠጣ የሚገባ የዉስጥን የፈንገስ ክምችት የሚያወጣ ምንም አይነት የህመም ስሜት የሌለዉ ነዉ።
- ለቆዳ በሽታ ሁሉንም አይነት ያድናል
- ያለ እድሜ ለሚመጣ የወሲብ (የብልት መፍጠን) ችግር በመቀባት የሚያድን አብዛኛዉ ሕዝብ የኪንታርት በሽታ መድሀኒት በተመጣጣኝ ዋጋ እንሸጣለን።

ቁጥር 1፡ አዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ሐና ማርያም ከጤና ጣቢያው 100 ሜትር አለፍ ብሎ

ቁጥር 2፡ ሰሜን ሸዋ መሐል ሜዳ ወርልድ ቪዥን ፊት ለፊትና ወይን መድሐኒዓለም ፊት ለፊት

ቁጥር 3፡ መገናኛ ውልና ማስረጃ ፊት ለፊት ገነት ኮሜርሻል ሴንተር 2ኛ ፎቅ የመድሐኒት መሸጫና ነጻ የመረጃ ማዕከል

ቁጥር 4፡ ጎጃም በረንዳ ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ካለበት ሕንጻ ላይ 2ኛ ፎቅ 221 ቁጥር የመድሐኒት መሸጫና ነጻ የመረጃ ማዕከል

0911 665321/ 0913 316790 / 0912 660886